UNIVERSAL STATIONERY
2 55 30    312o7

# አፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ

## (ዘ አፍሪካንስ)

ደራሲ - ዴቪድ ላምብ
ተርጓሚ - ነቢዩ ኢያሱ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

አዲስ አበባ

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ እትም ታህሣሥ 1984

ቦሌ ማተሚያ ቤት

# ማውጫ


| ምዕራፍ | ገጽ |
|---|---|
| 1. የአህጉራቱ ገፅታ | 15 |
| 2. ያለፈውና የአሁኑ አለመጣጣም | 33 |
| 3. የመሪዎች ድክመትና የሀገሮች ውድቀት | 41 |
| 4. የኢ.ዲ. አሚን አሰቃቂ ድርጊቶች | 75 |
| 5. አንድነትን ፍለጋ | 95 |
| 6. ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥታት | 109 |
| 7. የቅኝ ግዛት ውርስ | 131 |
| 8. ከሊዝበን በፍቅር | 163 |
| 9. የውጭ ኃይሎች ያጠሉበት ሁኔታ | 173 |
| 10. በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች | 191 |
| 11. የእንግዳ ባህል ተፅዕኖ | 203 |
| 12. የዜና ሳንሱር | 211 |
| 13. አቅም ያለው ይናገራል | 223 |
| 14. የገንዘቡ የመግዛት አቅም | 237 |
| 15. ናይጀርያ—አዱኛው አሁን ነው | 257 |
| 16. ለብቻ ከዓለም መጣላት | 267 |
| 17. ያለፈውን በማጤን የወደፊቱን ስንቃኝ | 281 |
| 18. እስታቲስቲካዊ ገጽታ | 289 |

★ መጽሐፉ የታተመው በ1985 ሲሆን የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

# ከተርጓሚው

ይህ መጽሐፍ በቀድሞው መንግሥት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ እንኳን ተከልክሎ የቆየ ነው ። አሁን ግን ተተርጉሞ ሊቀርብ ችሏል ። ይህም የዲሞክራሲ ጮራ መፈንጠቁን ያመለክታል ።

ይህ አስደናቂ መጽሐፍ የሚተነትነውም ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አገሮች ዴሞክራሲ በምን መልኩ ታፍኖ እንደኖረና ምን ያህል አሰቃቂ ግፎች እንደተፈጸሙ ነው ። ለዚህ አሳዛኝ ሕይወት አፍሪካውያንና የአምባገነን መሪዎቻቸው ባህርይ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ተዘርዝሯል ። የየሀገሮቹ የፖለቲካ ሕይወት አስደንጋጭና ዘግናኝ ነው ።

ያለፉትን ስህተቶችና ችግሮች ምንጮች ከመመርመር ባሻገር ለዘለቄታው ዴሞክራሲና ፍትሕ ይሰፍን ዘንድ ለጋራ ጥቅሞች መጠበቅ የአስተዋይ ሕዝቦች እርምጃዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ብዙ የሚያስተምርና የሚመክር መጽሐፍ ነው ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ ምዕራፎች ብዙ አስገራሚ ታሪኮች ተዘርዝረዋል ። ትናንትን ፣ ዛሬንና ነገን የምናይበት መጽሐፍ ነው ። ነግ በእኔ ነውና በየሀገሩ የደረሱት ምስቅልቅል ሁኔታዎች በጥሞና ሊጤኑ የሚገባቸው ናቸው። የሀገራችንን አቅጣጫና የየራሳችንን አስቸጋሪና ለመተንበይ የሚያስችግር ግራ የሚያጋባ ባህርይ የምንመለከትበት መስተዋት ነው ።

# አፍሪካውያን

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዘራቸው ምክንያት ብቻ የሚገደሉበትን እህጉር እንዴት አድርጎ መግለጽ ይቻላል? የእንግሊዝን ሊቀጳጳስን ጨምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያንን የጨፈጨፉት ኢዲ አሚን ለዓመታዊ ስብሰባ አፍሪካ አዳራሽ ሲገቡ በከፍተኛ አድናቆት እያጨበጨቡ የሚቀበሏቸው መሪዎች ያሉበትን አህጉር ምን ብሎ መግለፅ ይቻላል ? በደቡብ አፍሪካ ከታሰሩት የሚበዙ የፖለቲካ እስረኞችን ያጎሩትንና በትርፍ ጊዜያቸው የሼክስፒርን መጽሐፍ የተረጎሙትን የታንዛኒያ ፕሬዚደንት ጁሊየስ ኔሬሬ ምን ትሏቸዋላችሁ? እንዲያም ሆኖ አሚንን የመሰሉ ማይም መሪዎች በአፍሪካ የመኖራቸውን ያህል በሥነ ጽሑፍ የኖቤል ሽልማት ተወዳዳሪ የነበሩትን የሴኔጋል ፕሬዚዳንት ሊዎፖልድ ሴዳር ሴንጎርን የመሰሉ ምሁር መሪዎች አሉ። ምዝበራና የሕዝብ ሰቆቃ የማይሰማቸውና በስዊዝ ባንክ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚያከብቱ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች የመኖራቸውን ያህል በወር ስድሳ ዶላር ብቻ እያገኙ የሚያስተምሩና የነገዋ አፍሪካ ተስፋዎች የሚሆኑ ወጣቶችን በማስተማራቸው የሚኮሩ ብዙ አፍሪካውያን መምህራን አሉ።

ይህ መጽሐፍ ስለዛሬዋ አፍሪካ ነው። በጦር ሜዳ ትግልና በሰላማዊ ድርድር ነፃነታቸውን የተጎናጸፉ ሕዝቦች ታሪክ ነው። እንዲያ ታግለው ነፃ በወጡ ማግስት የተገነዘቡት ግን ፡ ነጮች ቅኝ ገዥዎቻቸው የተተኩት ይሉኝታ በሌላቸውና ከብሔራዊ ልማትና ከብዙኃን ፍላጎት ይልቅ የግል ሥልጣንና ሀብት በማካበት ላይ ያተኮሩ ጥቁር የእጅ አዙር ቅኝ ገዢ መሪዎች መሆናቸውን ነው።

ብዙ አንባቢዎች ይህን መጽሐፍ እዚህና እዚያ የሚረግጥ አድርገው ሊወስዱት ይችሉ ይሆናል። ምክንያቱም የ1980 ዎቹ አፍሪካ ደስተኛና ተስፋ ያላት አይደለችም። በመላ አህጉሪቱ ኢኮኖሚዎች እየተንኮታኮቱ ናቸው ፤ የሕዝብ ብዛት ልቅ እንደተተወ አረም እየፈላ ነው። ማይም ሃምሳ አለቆች መንግሥታትን እየገለበጡ ናቸው ፣ እሥር ቤቶች እየተጨናነቁ የእርሻ ቦታዎች ባዶ ቀርተዋል ፣ በአፍሪካ

የስደተኞች ቁጥር ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ አምስት ሚሊዮን ደርሷል ። ከትውልድ ሀገራቸው በአምባገነን መሪዎች ፣ በጦርነትና በድህነት ምክንያት የተሰደዱ ሕዝቦች በስደተኞች ካምፖች የመከራ ኑሮ ይገፋሉ ።

ነገር ግን አፍሪካ ከነፃነት በኋላ በነበሩት በእነዚህ ዓመታት የተመሳቀለች ብትሆንም ለዘለቄታው አስተማማኝ ባልሆነ ሁኔታ የምትቀጥል አይሆንም ። ሕልሟ ሁሉ በአምባገነኖች አቅጣጫውን ሳተ እንጅ ጨርሶ ያለቀለትና የተበላሸ ጉዳይ አይደለም ።

> “ጥንታዊቷ አህጉራችን . . .ዛሬ በውድቀት አፋፍ ላይ ናት ፤ መጨረሻ ወደሌለው ፍጥጫ ጭልጥ ብላ እየወረደች ነው ፤ በግጭት ተተብትባ ወደ ሞትና ደም መፋሰስ ጨለማ እየሰመጠች ነው ።”
>
> ኤዶም ኮጆ—የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ

አፍሪካ የደረስነው በ1976 የድርቅ ዘመን ነው ። ሜዳው ሁሉ ቡናማ ቀለም በመያዝ ተሰነጣጥቋል ። ከብቶች እያለቁ ነበር ። ሕፃናት ሆዳቸው ድርቅ ባስከተለው በሽታ እያበጠ ነበር ። እነዚህ አስከፊ የመከራ ደመናዎች በሕይወት ሂደት ጥሩውንና ሰይጣናዊውን የሚያዝዙ ኃያል መናፍስት የሚኖሩበት የሚባለውን የኬንያ ተራራ ሸፍነውታል ። እነዚህ አማልዕክት በመቆጣታቸው ለዓመት ያህል አንድ ጠብታ አልዘነበም ። ጉስቁል ሕዝቦች ሕይወታቸው በማያውቁትና ሊለውጡትም ባልቻሉ ኃይል ተቀፍድዶ የተሻለ ጊዜያትን ሲመኙ ቆዩ ።

ባለቤቴ ሳንዲና እኔ በአፍሪካ እስከ 1980 ድረስ ቆየን ። እኔ በ“ሎስ አንጀለስ ታይምስ” ጋዜጣ ወኪልነት ፣ ባለቤቴ ደግሞ በፊልም አዘጋጅነት ስንሰራ ቆየን ። በእነዚህ የአራት ዓመታት ቆይታችን በአህጉሪቱ ሁለት ሀገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ ወጡ ፤ አሥራ አንድ መንግሥታት በመፈንቅለ መንግሥት ተወገዱ ። ድርቅ ተመላለሰባት፣ የስደተኞች ቁጥር ወደ ሚሊዮኖች አሻቀበ ፤ ጦርነቶችም እንደሰደድ እሳት ተስፋፉ ። በዚህም ውስጥ አልፈው መላው አፍሪካውያን በምዕራብ በማይታሠብ ሁኔታ አገገሙና ወደነበሩበት ተመለሱ ። የዕድል ጉዳይ ነው በሚል አመለካከት መልካም እድልንም ፣ እድለቢስነትንም በመቀበል እንደገና ቀጠሉ ።



ከናይሮቢ ዋና መቀመጫችን እየተወረወርሁ ለሥራ በአርባ ስምንት የአፍሪካ አገሮች ተዘዋወርሁ ። በድምሩ ሦስት መቶ ሺህ ማይልስ በአውሮፕላን ፣ በመኪናና በባቡር ዞሬአለሁ ። ባለማቋረጥ ጦርነት ካለበት መፈንቀለ መንግሥት ወደተካሔደበት ስወረወር ፤ አንዱ ሕዝብ በሌላው ላይ የሚፈፅመውን አሰቃቂ ድርጊት አስተውያለሁ ። እነዚህ ዘራፍ የማለት የእብደት ወቅቶች ጋብ ሲሉና አፍሪካ ከራሷ ስትታረቅ ከተሞችንና መንደሮችን ለመጎብኘትም ሆነ ሰዎችን ለማነጋገር ፤ በቀድሞውና በአሁኑ መካከል ተሰንቅረው የሚገኙትን ገና ነፃ የወጡ ሕዝቦች ደስታና ብሶት ለማጣጣም ጊዜ ነበረኝ ።

ፕሬዚዳንቶችን ፣ ጠንቋዮችን ፣ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮችን ፣ የደፈጣ ተዋጊ መሪዎችን ፤ ነጋዴዎችንና ገበሬዎችን አነጋግሬአለሁ ። በኡጋንዳ የኢዲ አሚን እሥር ቤት ውስጥ የሲ.አይ.ኤ ሰላይ ወይም ቅጥረኛ ነህ በሚል ታጉሬ ጥቂት አስደንጋጭ ሰዓቶች አሳልፌአለሁ። በጠራ ሰማይ የከዋክብት ብርሃን በሚያምሩ ፣ ፀጥታውና ሰላሙ ዘላለማዊ በሚመስልባቸው ውብ የአፍሪካ መስኮች አያሌ የማይረሱ ድንቅ ጊዜዎች አሳልፌአለሁ ። ከጅቡቲ በረሃማ ምድር እስከ ናይጄርያ የነዳጅ መስኮች በመቶ የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ስለሕይወታቸው ፣ ስለሀገሮቻቸው ፣ ስለምኞታቸው አነጋግሬያቸዋለሁ ። ይህ መጽሐፍ በጉዞየ የተረዳሁትን በከፊል የፖለቲካ ገፅታቸውን ፣ በከፊል የአህጉሩን ወቅታዊ ታሪክ የሚዘግብ ሲሆን አፍሪካውያንን ሳይቀር ግራ ያጋቡ ሁለት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር ነው ። አፍሪካ ምን ድናት? አፍሪካውያንስ ማን ናቸው?

ከሰሀራ በረሃ በታች (ደቡብ) ያሉ የጥቁር አፍሪካ አገሮች ታሪክ ነው ። ከዚያ በላይ የሚገኙ አምስት የአረብ አገሮች ከእነዚህ ጋር የሚመሳሰሉበት ጥቂት ነው ። እንደ አፍሪካ ያለአግባብ የተስተናገደ፣ በሚገባ ያልታወቀና በተዛባ ሁኔታ የተገለጠ አህጉር የለም ።

የ1980ዎቹ አፍሪካ እንዳለፈው ወደጎን የምትተው አይደለችም። አፍሪካ ዛሬ ከዋሽንግተን እስከ ሞስኮ ባሉ ዋና ከተሞች ክስተቶችና ፖሊሲዎችን ለማስለወጥ ተፅኖ የምታደርግ አህጉር ናት ። የራሷ ፕሬዚዳንቶች ሊቆጣጠሩትም ሆነ ሊያገናዝቡት በማይችሉት ሁኔታ ያልተጠበቁ ለውጦች ወደ መጨረሻው አድሏ እየቀዘፏት ነው ። እነዚህ ለውጦች ወደሚወስዷት አቅጣጫ አፍሪካ ተፅዕኖ የማድረግ አቅም ይኖራታል ፣ ምናልባትም የሃያ አንደኛውን ምዕት ዓመት የአለማችን አቅጣጫ ትወስን ይሆናል ። አፍሪካ የተፈጥሮና የሰው ኃይሏን መግራት ከቻለች የሶስተኛው ዓለም ታላቅ ስጦታ ነች ።

ዛሬ በአፍሪካ ሃምሳ አንድ ነፃ ሀገሮች አሉ። በቅኝ ግዛት ዘመን የረጋች፣ ሥርዓት የነበራት፣ የብሔረተኝነት ስሜት ቀዝቃዛ የነበረባት የቀድሞዋ አፍሪካ ዛሬ መተንበይ የምታስቸግር፣ አመፅ ሊፈነዳባትና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ሊከሰትባት የሚችል አስፈሪ አህጉር ናት። የቀድሞዎቹ ወግ አጥባቂዎች ዛሬ በተራማጆች ተተክተዋል። እነዚህን ለውጦች የሚቀርፁና የቀረፁ ሁኔታዎች ከሕዝብ አመፅ መገንፈል የማይተናነሱ ናቸው።

አፍሪካ ዛሬ ብዙ ቢወራላት አይደንቅም። አህጉሪቱ ትልቅ የመሆኗን ያህል የተለያየ መልክና የተወሳሰበ ሁኔታ ያላት በመሆኗ ነው። አፍሪካ ከዩናይትድ እስቴትስ በቆዳ ስፋት አራት እጅ፣ በሕዝብ ብዛት ሁለት እጅ ትልቃለች። ሁለት ሺህ ጎሳዎችና ብሔረሰቦች ይኖሩባታል። በእንግሊዝ የተማሩ፣ ምዕራባዊ አለባበስ የሚያዘወትሩና ስለቦውሊንግ ውድድር የሚያወጉህ ሰዎች ታገኛለህ። ጥቂት ኪሎ ሜትር ከከተማ ወጣ ስትል ጠቦት አርዶ የሚጋብዝህ፣ በጦርና ቀስት የሚያድን፣ የወረቀት ገንዘብ አይቶ የማያውቅ፣ ፈረንጅ ሁሉ ሐኪም ወይም ሚስዮን የሚመስለው ገጠሬ ታገኛለህ። አፍሪካ በዓለም ኅብረተሰብ ያላትን ሥፍራ ቸል እንዳንል የሚያስገድዱ ምክንያቶች አሉ።

አንደኛ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ አንድ ሦስተኛ ድምጽ አላት። ይህም ከሌሎች አህጉሮች ይበልጣል። ሁለተኛ ገና ያልተነኩ ድንግል መሬቶችና ለምሥራቁም ለምዕራቡም በሰላምም በጦርነትም አስፈላጊ የሆኑ ማዕድናት አሏት። ሦስተኛ ጠም የሚያድሩ የእርሻ መሬቶቿ ራሷን መግበው መላውን ምዕራብ አውሮፓ ሊመግቡ የሚችሉ ናቸው። ሌላ መሬት መንጥሮ መጨመር ሳያስፈልግ አሁን ባለው ለም አፈርዋ ብቻ ዛሬ የምታመርተውን መቶ ሰላሳ ጊዜ የበለጠ ማምረት ይቻላል። አራተኛ ወደፊት ልሰለኃያላን ሊጋጩባት የሚችሉ (እንደዛሬዋ መካከለኛ ምሥራቅ) የጦር ሜዳ ናት። አምስተኛ ሥራ ላይ ያልዋለ 455 ሚሊዮን ሕዝብ አላት። ከዚህ ሕዝብ ግማሹ ገና ከአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በታች ስለሆነ ከበሽታ፣ ከድህነት፣ ከጭቆና፣ ነፃ መሆንን የሚሻ ለዚህም የሚታገል ነው። ይህ መጽሐፍ ስለነዚሁ ሕዝቦችና ሕይወታቸውን ስለሚቀርፁት ክስተቶች ነው። ስለዛሬዋ አፍሪካ የሚያብራራ ነው።

ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን ሁኔታ ለጥፋት እንዲያመች አድርገው ቀየሱት ፣ አፍሪካውያንም ይህንን ለማስፈጸም በተቻላቸው ሁሉ የሚሯሯጡ ይመስላል። ለአፍሪካውያን ከቅምጥ ሀብት ይልቅ በተቃ



ራኒው ችግርና ሰቆቃ ደጃፋቸው ላይ ነው። አፍሪካ አስደናቂ ምድር ናት። ምንም ነገር እንደነበረ አይቆይም፣ ምንም ጉዳይ እንደታሰበው አይዘልቅም። የፖለቲካ አቅጣጫዎች ይለዋወጣሉ፣ መሪዎች ይገደላሉ፣ ይታሰራሉ፣ ይሰደዳሉ፣ አገሮች ስማቸውን ይለውጣሉ። በአፍሪካ የፖለቲካ ነክ ጉዳይ ብዙ ሳይቆይ ይለዋወጣል፣ ሕዝቡ ግን ሁልጊዜም ይኖራል።



ሞሮኮ
አልጄሪያ
ሊቢያ
ግብፅ
ሞሪታኒያ
ማሊ
ኒጀር
ቻድ
ሱዳን
ኢትዮጵያ
ናይጄሪያ
ዛየር
ኬንያ
ታንዛንያ
አንጎላ
ዛምቢያ
ናሚቢያ
ቦትስዋና
ደ. አፍሪካ
ኮሞሮስ
ማዳጋስካር
አትላንቲክ
ውቅያኖስ

ምዕራፍ አንድ

# የአህጉሪቱ ገጽታ

“በባህል ግጭት ናውዘን የአውሮፓውያን የአኗኗር ዘይቤን ከራሳችን ጋር አዳቅለን ለአፍሪካ ኅብረተሰባችን ለማላበስ ሞከርን ። እስከ አሁን ውጤቱ ታላቅ ውድቀት ነው ። አን ዱንም ሳንይዘው ቀረን ።”

— ሌተና ጀኔራል ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ
የቀድሞው የናይጀርያ መሪ

የቀድሞው የደፈጣ ተዋጊ ካርሎስ ሚራንዳ ከጓደኞቹ ጋር ቅዳሜ ከቀትር በኋላ ጊዜ ለማሳለፍ በአንዲት ቀልካሻ ቡና ቤት ተቀምጦ የፖርቱጊዚ ቢና እየጠጣ ያወራል ። ምንም የሚሠራ ነገር የለም ። ካቸው በጊኒ ቢሳው የምትገኝ ትንሽ ከተማ ናት ። የቀኑ ሙቀት ያደ ብናል ። ስለዚህም በአንድ የቀጣመመ የእንጨት ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀ ምጠው ያለሥራ ዝንባቸውን እሽ እያሉ ያወጋሉ ። ለስላሳም ሆነ ቢና የሚሸጠው ሳይቀዘቅዝ ነው ። እንደ ካቸው የመብራት ኃይል አገልግሎት ማቀዝቀዣውም ከተበላሸ ቆይቷል ። አሳላፊው ማቀዝቀ ዣውን ተደግፎ ቆሞ ላቡ ይንቆረቆራል ። ጠርሙስ ከእጁ እምልጦት ወደቀና ተከሰከሰ ፤ ስባሪውን በእግሩ ወደ መደርደሪያው ገፋና ያላ በው እጁን በለበሰው ካናቴራ ላይ ጠረገ ። ሚስቱና ሰባት ልጆቹ ወለሉ ላይ ተኝተዋል ።

“ፍራንችስኮ ሌላ ጠርሙስ ሰበረ” አለ ሚራንዳ ፤ “ምን ያድርግ የሚጠጣው አልቋል ።” ፍራንቺስኮ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ውድ ጠርሙሶች ሰብሯል ፤ ግዴለሽነቱም የሚያናድድ ሆኗል ።

ካርሎስ ሚራንዳ በፖርቱጊዞች ቅኝ ገዢነት ዘመን ወታደር ነበር ፤ በኋላም የጦር ምርኮኞቸው ሆነ ። ከ1961 እስከ 1974 በቆየው የነፃነት ተጋድሎ የደፈጣ ውጊያ እንቅስቃሴ አሥር ሺህ ያህል ተዋጊዎች ነበሩ ። በሶቪየትና በኩባ ርዳታ ውጊያውን በማፋፋም የኋላ ኋላ ሰላሳ አምስት ሺህ የሚሆኑትን የፖርቹጊዝ ወታደሮች ከገጠሩ አካባቢ አሳደው በዋና ዋና ከተሞች እንዲመሽጉ አስገደዷቸው ። ይህ ድላቸው በፖርቹጋል ያለውን አምባገነን አመራር በሚያዚያ 1974 ለማስወገድ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የሰላሳ ስድስት ዓመቱ ሚራንዳ ብርጭቆየን ቢራ እየሞላልኝ "በቅኝ ግዛትና በነፃነት መካከል ያለው ልዩነት ትልቅ ነው" አለኝ። "አንደኛ የስለላ ፖሊሶችን ሳልሰጋ ሌሊት ያለሀሳብ እተኛለሁ ። ከፈረንጅ ጋር ያለፍርሀት አወራለሁ ። በፊት ግን ነጭና ጥቁር አያወሩም ነበር ። ዛሬ ሰው ሆኜ ከአንተ ጋር እኩል ተቀምጬ አወጋለሁ ። የተዋጋንለትም ይኸው ነው ፤ ክብራችንን ለመቀዳጀት ። የፖርቱጋል ሕዝብን አልጠላንም ። የጠላነው መንግሥቱን ነው ። አንተም የእነሱ ዜጋ ብትሆን ኖሮ አብሬህ ለመቀመጥና ለማውራት ቅር አልሰኝም ፤ ምክንያቱም አሁን እኩል ሆነናል ።"

ሚራንዳ በወር ሃምሳ ዶላር የሚከፈለው የጉምሩክ ሠራተኛ ሲሆን ዘጠኝ ልጆች አሉት ። በነፃነት ተጋድሎ ዘመን ተራ ወታደር ነበር ። ጦርነቱ የተካሄደውም እሱን ለመሰሉ ሕዝቦች መብት ሲሆን ነፃነትም በገንዘብ የማይተመን ታላቅ ዋጋ አጎናጽፎታል ፤ የዜግነት ክብር ። ለጊኒ ቢሳው ነፃ መውጣቱዋ በቅፅበት እድገት አላስጨበጣትም ። እንዲያውም ከሩዝ እስከ ሳሙና የመሠረታዊ ሸቀጦች እጥረት ተፈጠረ ። አንድ ቀን አንድ ነጋዴ ጫማዎች አስመጣና ሊገዛ የመጣው ሕዝብ ከመብዛቱ የተነሳ በፖሊስ መበተን ነበረበት ። አንድ ሚሊዮን ከማይሞላው የጊኒ ቢሳው ሕዝብ የመንግሥት ሥራ የያዘው 24000 ብቻ ነው ። ሀገሪቱ ምንም ያህል የተፈጥሮ ሀብት የላትም።

እንደሌሎቹ የፖርቱጊዞች ቅኝ ግዛት እንደነበሩት ሞዛምቢክና አንጎላ ፣ ጊኒ ቢሳው የነጭ ሠፋሪዎች ቅኝ ግዛት አልነበረችም ። ይልቁንም ፖርቱጋሎች እንደማረፊያና ገንዘብ መቆጠቢያ ቦታ ነበር



የቆጠሩዋት ። ስለዚህም ነፃ እንደወጡ ከሶስት መቶ ሃምሳ ፖርቱጋሎች በስተቀር ሌሎች በሙሉ ያለቅሬታ በፍጥነት ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። ሶስት መቶ ዓመት ሙሉ በቅኝ ግዛት ለያዟት ሀገር የተውላት ነገር ቢኖር አሥራ አራት የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ፤ ዘጠና ሰባት በመቶ ማይም የሆነ ሕዝብ ፤ ሁለት መቶ ስድሳ አምስት ኪሎሜትር አስፋልት መንገድ ብቻ ነበር ። በጊኒ ቢሳው አንድ ዘመናዊ ፋብሪካ ብቻ ነበር ። እሱም ለፖርቱጋል ወታደሮች ቢራ የሚያመርት ነው ። በመጨረሻም ፖርቱጋሎች ሲወጡ ይባስ ብለው ብሔራዊ መዝገብ ቤቱን አውድመው ሄዱ ።

በብዙ መንገዶች ጊኒ ቢሳው የአህጉሪቱን ሁኔታ መመልከቻ ምሳሌ ናት ። ከስተቶች ሁሉ እድገትን የሚያደናቅፉ ፣ መጭው ዘመን ያለፈው ሁኔታ ምርኮኛ የሆነበት ሲሆን ፤ በዚህ ሁሉ ችግር ተጠቂ ኢላማዎችም እንደ ካርሎስ ሚራንዳ የመሰሉ የአፍሪካ ልጆች ናቸው ። አንዱን ውድቀት ሌላው ውድቀት ሲታከልበት ፤ እርምጃው ሁሉ ውጤት አልባ ሲሆን ፣ ጥቁር አፍሪካ የራሷ ማንነትና ዓላማዋ ዋገርቀባት ፤ ስለራስዋ እርግጠኛ መሆን አልቻለችም ። በርዕዮተዓለም ተከፋፍላና በግል ጥቅም ተበታትና ፤ በሀገራዊ ጥያቄ ግራ ተጋብታና ልክ እንደቅኝ ተገዢነትዋ ዘመን በወታደራዊና በኢኮኖሚ የውጭ ኃይሎች ጥገኛ ሆና ቀረች ። በ1980ዎቹም እንዲሁ በቀውስ የተመታች፣ የሁከትና የአደጋ ተጠቂ አህጉር ሆና ቀጥላለች ። የአብዮት ፍቅር የአፍሪካን ኅብረተሰብ ያስተሳሰረውን ሺህ ድር ከሚበጥስ ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት እህጉሯን ሊደብቅ ተሳነው ።

አፍሪካ የሚለው ስም አፕሪስ(ፀሐያማ) ከሚለው የላቲን ቃል ወይም አፍሪኬ (ብርድ አልባ) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ይመስላል ። አፍሪካ ከዓለም ሃያ በመቶ የሚሆነውን ምድር ታጠቃልላለች ። ይህም ስፋት አሥራ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን እስኩዌር ማይልስ ነው ። ከአፍሪካ የሚሰፋ አህጉር እስያ ብቻ ነው ። አፍሪካ ከሰሜን እስከ ደቡብ አምስት ሺህ ማይልስ ርዝማኔ አለው ። እግዚአብሔር ከረገመው የሰሜን በረሃ እስከ ታደለው የደቡብ የወይን ዘለላ አምራች ድረስ ማለት ነው ። ከምሥራቅ ምዕራብ የአህጉሩ

ስፋት ደግሞ 4.600 ማይልስ ይደርሳል ። የባህር ጠረፉ ርዝማኔ ፥ 18.950 ማይልስ ሲሆን ብዙ ወጣ ገባ የባህር ወሽመጦች ስለሌሉት ርዝመቱ ከአውሮፓ ያነሰ ነው ። የምድር ወገብ መስመር የሚያልፈው በአህጉሩ ወገብ ነው ። የአህጉሩ የአየር ጠባይ የተለያየ ነው ። ከንዳዱ በረሃ እስከ በረዶአማ የተራራ ጫፎች ሁሉም ዓይነት የአየር ጠባይ ይገኝበታል ።

የአፍሪካ የባህር ጠረፍ ጠባብ ሲሆን ወደ መሀል ሲገባ የሚታየው ተራራማ አካባቢ ከፍተኛ ዶፍ የሚዘንብበት ጥቅጥቅ ደን ነው። ከዚሁ ጋር አልፎ አልፎ ዛፎች ያሉበት የግጦሽ መስክም በብዛት ይገኛል ። በሰሜን የሚገኘው የሰሀራ በረሃ በዓለም ከፍተኛ ነው ። ይህም የአህጉሩን አንድ አራተኛ የሚያካትትና የዩናይትድ እስቴትስን የቆዳ ስፋት (አላስካን ሳይጨምር) የሚያክል ነው ። በደቡብ ደግሞ ካልሀሪ በረሃ የሚባል በዓለም ሰባተኛ የሆነው ይገኛል ። ትልቁ ተራራ በታንዛኒያ የሚገኘውና አናቱ ላይ በረዶ የማይለየው ኪሊማንጃሮ ሲሆን 19340 ጫማ ከፍታ አለው ። ከሌሎች አህጉሮች ጋር ሲነፃፀር ከሁሉም የላቀ ሜዳማ ነው ።

በእነዚህ ባዶ ሜዳዎች ስታቋርጥ የሚመጣልህ ሀሳብ ፥ አሥር ሺህ የአሜሪካ አራሾች ቢሰማሩበት በአጭር ጊዜ የቱን ያህል ሊለውጡት እንደሚችሉ ነው ፤ የራሳቸውን ሀገር እንዳደረጉት ሁሉ ። ቀላል ይመስላል ። ነገር ግን የአፍሪካ እርሻ አሁንም ከዶማና ከማጭድ አልወጣም ። ከየትኛውም የዓለም ክፍል ኋላቀር ነው ። ለምሳሌ ለሃያ አምስት ሺህ ጋሻ የእርሻ መሬት በአማካይ ሰባት ትራክተሮች ብቻ አሉ ። በዚሁ ያህል የታረሰ መሬት ስናነፃፀረው በእስያ አርባ አምስት ፥ በደቡብ አሜሪካ ሃምሳ ሰባት ፥ በዩናይትድ እስቴትስ ሁለት መቶ አርባ ትራክተሮች ተሰማርተዋል ። አፍሪካውያን በአንድ ጋሻ መሬት ሁለት ኩንታል ማዳበሪያ ብቻ ሲጠቀሙ ፥ በእስያና ደቡብ አሜሪካ አሥር እጥፍ ፥ በዩናይትድ እስቴትስ ሃያ ጊዜ እጥፍ ይጠቀማሉ ። በረሃማነት በየዓመቱ እየተስፋፋ ስለሚሄድ አፍሪካውያን በየዓመቱ የሚያርሱት መሬት እያነሰ ነው ።

የሰሀራ በረሃ በየዓመቱ 250'000 ጋሻ መሬት ስፋት እየጨመረ



በአንድ ወቅት የሮማውያን የዳቦ ቅርጫት የነበረው አካባቢ ሁሉ ወደ በረሃነት ተለውጧል ። ከአንድ ትውልድ በፊት የሞሪታንያ ዋና ከተማ ኖዋክቾት ከሰሃራ በረሃ የብዙ ቀናት መንገድ ይርቅ ነበር ። ዛሬ ግን የበረሃው አካል ሆኗል ። ሕይወትም ከዚሁ ጋር ተለውጧል ።

ሳይንቲስቶች እንደሚናገሩት የበረሃዎች መስፋፋት በአፍሪካ ብቻ የሚታይ አይደለም ። በስድስቱም ሰው በሚኖርባቸው አህጉራት በረሃዎች እየተስፋፉ ናቸው ። አንዳንዶቹ ለአየር ጠባይ መለወጥና ለድርቅ መከሰት ተፈጥሮን ይኮንናሉ ፤ ሌሎች ደግሞ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት በአግባቡ ባለመያዙና አካባቢውን በማበላሸቱ የተከሰተ አድርገው ይመለከቱታል ። በተለይ ደንን መጨፍጨፍና የሳር መሬቶችን ከሚገባ በላይ በከብቶች ማስጋጥ ከላይ ላለው ለም አፈር መሸርሸር ዋናዎቹ በር ከፋች ድርጊቶች እንደሆኑ ይናገራሉ ። ያም ይሁን ይህ አሁን የሚታየው የአየር ሚዛን መዛባት ለአፍሪካ እጅግ አስፈሪ ነው ። በሳይንቲስቶች የሳተላይት መረጃ መሠረት ከመሬት ላይ ያለው ለም አፈር በነፋስ እየተጠረገ አህጉሩን ጥሎ እየወጣ ነው ። ይህን አፈር ለመተካት—ሺህ ዓመታት ይጠይቃል ።

አፍሪካ የሰው ልጅ የመነጨባት ፥ የባህልና የሥልጣኔ ማዕከል ስለነበረች እንዲህ እድለቢስ መሆንዋ ያሳዝናል ። ሶስት ሚሊዮን ዓመታት የሚሆናቸው የሰው ልጅ አጽሞች በተመራማሪዎች በማሪ ሊኪና በባለቤትዋ በሉዊስ መገኘታቸው የሰው ልጅ የመጀመሪያዎቹ ዝርያዎች በምሥራቅ አፍሪካ እንደኖሩ ይጠቁማል ። በኢትዮጵያ ምርምር የሚያካሂዱ የአሜሪካና የፈረንሳይ ሳይንቲስቶች ሁለት ተኩል ሚሊዮን ዓመታት የሚሆናቸው ከድንጋይ የተቀረጹ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች አግኝተዋል ። እንደምላጭ የተሳሉና እንደመሮ የሾሉ የድንጋይ መፈልፈያዎች እንስሳትን ለማረድና ለመግፈፍ ያገለግሉ የነበሩ ሳይሆኑ እንደማይቀር ተገምቷል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓመተ ዓለም በናይጀርያ የዳ ረጀ ባህል ነበረ ፤ ብረት ለማቅለጥ ,የሚጠቀሙበት ልዩ ምድጃ

ሥርተው ነበር ፤ በ1486 ቤኒን ከፖርቱጋሎች ጋር አምባሳደር ተለዋውጣ ነበር ። በዚያ ዘመን በማሊ በምትገኘው ቱምቢክቱ ዓለም አቀፍ ዝና ያተረፈ የንግድ ማዕከል ነበር ። በዚያ አካባቢ የነበሩት አገሮች እድገት በዘመኑ በአውሮፓ ከነበረው ሥልጣኔ የሚወዳደር እንደነበረ ታሪክ ፀሐፊዎች ዘግበዋል ። በ1600 የደች መንገደኛ አካባቢውን ተዘዋውሮ በመመልከት እንደፃፈው ፤ "ገና ስትገባ ከተማው ትልቅ መሆኑን ትመለከታለህ ፤ አስፋልት ያልለበሰ ሰፊ አውራ ጎዳና ታገኛለህ ፤ ይህም ከአምስተርዳም ሰፊው የዋርምስ ጎዳና በብዙ እጅ ይተልቃል ፤ የቤቶቹ አሠራር ያምራል ፤ ልክ እንደሆላንድ ቤቶች አሠራር ፤"በማለት ዘግቧል ። ኮለምበስ ወደ አሜሪካ ከመቅዘፉ በፊት በናይጀሪያ አይፌ አስተዳደር ክልል ከብር የተሰሩ ቅርፃቅርጾች ይመረቱ ነበር ። በ1100 ዓመተ ምህረት በአፍሪካ የብረት ዘመን በዚምባብዌ አካባቢ እጡብ ድንቅ የሆኑ የድንጋይ ሕንፃዎች ይታነፁ ነበር። በአሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት ነጋዴዎች ዘገባ መሠረት ደግሞ በአፍሪካ በዚያን ዘመን የሚሠራው ጨርቃጨርቅ በአውሮፓ ከሚመረተው ከየትኛውም የላቀ ደረጃ እንደነበረው ጽፈዋል ።

የጥንቷ አፍሪካ ታሪክ በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ስለ ነበረ የጥንቱ ሥልጣኔ ፍንጭና የመክሰሙ ሁኔታ ደብዝዞና ምስጢር ሆኖ ቀርቷል ። የሚፃፍ ቋንቋ ያላት የጥቁር አፍሪካ አገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት ። ለማንኛውም የአፍሪካ የጥንቱ ሥልጣኔ የወደመው በአካባቢው አገሮች የእርስ በርስ ጦርነት እንጅ በአውሮፓውያን እንዳልሆነ ይነገራል ። የጋና ሥልጣኔ ቅርሶች የተደመሰሱት በአሥራ ሶስተኛው ምዕት ዓመት በሴኔጋል አልሞራቪድ ተዋጊዎች ነበር ። በ1430 የማሊ ግዛት ቱዋሬግ በተሰኙ ዘላኖች ተንኮታኮተ ። በ1591 የሴኔጋል ግዛት በሞሮኮ ተዋጊዎች ተደመሰሰ ። የሚፃፍ ቋንቋ ሳይኖር መረጃዎችን ዘግቦ ማስተላለፍ አይቻልም ፤ አፍሪካ ለሥልጣኔ የሚያስፈልጓት የመሠረት ድንጋዮች አልነበሯትም ፤ በኋላም ከሰሜን ለመጣው አዲስ ጠላት መከላከያ አልነበራትምና የፈረንጆች ቅኝ ግዛት መሆን ተገደደች ።

ፖርቹጋሎች አፍሪካን በማወቅና በመጎብኘት የመጀመሪያ አውሮፓውያን ነበሩ ። የፖርቹጋል ጎብኝዎች ለባርያ ንግድ በር ከፈቱ ። ከዚያም ሚሲዮኖች ወደ አፍሪካ በመግባት የቅኝ አገዛዝ ወኪሎች ሆነው መስራት ጀመሩ ። እያንዳንዱ ወራሪ (ባሪያ ነጋዴ ፣ ሚስዮን ፣ ቅኝ ገዢ )ዓላማው መመዝበርና መለወጥ ነበር ። እያንዳንዱ የመጣው አፍሪካውያንን ለማገልገል ሳይሆን ራሱን ወይም እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር ። በአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት የኢንዱስትሪ አብዮት አውሮፓውያን አዳዲስ ገበያዎችና ጥሬ ዕቃ በመሻት የአውሮፓ ኃያላን አፍሪካን በመቀራመትና ሰው ሰራሽ ድንበሮችን በማስመር የሕዝቡን የቋንቋ ፣ የሃይማኖትና የጎሳ ሁኔታ ያልተከተሉ ድንበሮችን መቀየስ ጀመሩ ። በ1920 ከኢትዮጵያ ፣ ከላይቤሪያና ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር የአፍሪካ ምድር በሞላ አንድ ስንዝር ሳይቀር ለአውሮፓ አገሮች ቅርጫ ሆነ ።

የቅኝ ገዥዎች የአገዛዝ ዘይቤ የአፍሪካን ወደ ነፃነት ሽግግር ውድቀት የተሞላበት አደረገው ። "ከፋፍለህ ግዛ" የሚለው መመሪያቸው ፤ አንዱን ጎሳ በማቅረብ ሌላውን የማግለል አሠራራቸው ፣ አፍሪካን ለምዕት ዓመታት ሲያተራምሳት የነበረውን በዘር የመከፋፈል በሽታ አባባሰው ። ከነፃነት በፊት የአፍሪካውያን የጋራ ጠላታቸው ቅኝ ገዢው ፈረንጅ ነበር ፤ እሱ ለቆ ሲሄድ በየአገሩ ያሉት ብሔረሰቦች ለሥልጣን መፋጠጥ ጀመሩ ፤ ከብሔራዊ ስሜት ይልቅ የጎሳ ስሜት ባየለበት የአፍሪካ አህጉር አዲሱ የአፍሪካ ጠላት እራሱ አፍሪካዊ ሆኖ አረፈው ።

ዘረኝነት ግራ የሚያጋባ አፍሪካውያንን በሰፊው የተጠናወታቸው አንድ ከባድ በሽታ ነው ። ስለአፍሪካውያን ለማወቅም ማጤን ካለብን ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ነው ። የዘመኑ የአፍሪካ የፖለቲካ ሰዎች በይፋ ያወግዙታል ። የኬንያው ፕሬዚዳንት አራፕ ሞይ "የአገራችን ሕዝቦች የተሳሰሩበትን ድርና የቆሙበትን ዋና መሠረት እንደ ምስጥ በመቦርቦር ላይ ያለ ነቀርሳ (ካንሰር) ነው " በማለት ገልፀውታል ። እንዲያም ይበሉ እንጅ እያንዳንዱ የአፍሪካ መሪ የሚሠራው በዘር ላይ የተመሠረተ ነው ፤ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ከሀገር መሪነት ይልቅ የጎሳ መሪነት ይበልጥ ይጎትታቸዋል ። ምናልባትም በዕለት

ከዕለት የአፍሪካዊ ሕይወት ትልቁ የሚሰበው ኃይል ይኸው ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም ። ለጦርነቶችና ለሥልጣን ትግሎች ዋናው ጉዳይ እሱው ነው ። ብዙውን ጊዜ ሥራ ለማግኘት ፣ በሥራ ላይ ዕድገት ለማግኘት ፣ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ለማግኘት ወሳኝነት አለው ። ለወንዝ ልጅ ሥራ መስጠት እንደ አድሉም አይቆጠርም ፤ እንደ ግዴታ የሚታይ ነው ። ለፖለቲካ ሰዎችና ለከፍተኛ የጦር መኮንኖች የቅርብ ረዳቶቻቸውንና አማካሪዎቻቸውን እንዲሁም ጠባቂዎቻቸውን ከራሳቸው ጎሳ ማድረግ የተለመደ ስለሆነ እንደወግናዊነት አይታይም ። እንዲያውም ይህን ማድረግ የሥልጣን ዋስትና ሆኖ ቀጣይነቱን ያረጋግጣል።

የላይቤሪያ ፕሬዚዳንት የነበሩትና የተገደሉት የዊሊያም ቶልበርት ዘር ማንዘሮች የነበራቸውን ሥልጣን ብንመለከት የአፍሪካ የፖለቲካ ሰዎች የሥልጣን ደረጃዎችን ሁሉ ለዘመድና ለአምቻ ጋብቻ እንደሚያድሉ በግልጽ ያሳየናል ። የቶልበርት ወንድም ፍራንክ የመወሰኛው ምክር ቤት ፕሬዚደንት ነበር ፤ ሌላው ወንድማቸው እስቲፋን የገንዘብ ሚኒስትር ነበር ፤ እህታቸው ሉሲያ የቤንቶል ከተማ ክቲባ ፤ ወንድ ልጃቸው ኤቤ አምባሳደር ፤ ሴት ልጃቸው ዌልሄልሚና የፕሬዚደንቱ ቤተመንግሥት ሐኪም ፤ ሌላዋ ሴት ልጃቸው ክርስቲና የትምህርት ም/ሚኒስትር ፤ የእህታቸው ልጅ ቱላ የፕሬዚደንቱ ቤተመንግሥት የምግብ ዘርፍ ኃላፊ ፤ ሶስት የወንድማቸው ልጆች በፕሬዚደንቱ ጽ/ቤት ምክትል ሚኒስትር ፤ በሮማ አምባሲያቸው የእርሻ ጉዳይ አማካሪ ፤ የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዢ ፤ አራቱ የልጆቹ ባለቤቶች የመከላከያ ሚኒስትር ፤ የኮንስትራክሽን ምክትል ሚኒስትር ፣ የኤሚግሬሽን ኮሚሽነርና የላይቤርያ አየር መንገድ የቦርድ አባል ፣ የሶስቱ እህቶቻቸው ባሎች አንዱ በጊኒ አምባሳደር ፣ ሌላው የምክር ቤት አባል ፣ ሌላው ደግሞ የሞንሮቢያ ከንቲባ ነበሩ።

በዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሳካ አንድ የማውቀው የዩኒቨርስቲ ተማሪ የሥራ መጠየቂያ ደብዳቤ አቅርቦ የፔርሶኔል ዋና ሥራ አስኪያጁን እንዲያነጋግር ተነገረው ። ታዲያ ሥራ መሪው ከየትኛው ጎሳ እንደሆኑ ጸሐፊያቸውን ጠየቀና እሱ ከተወለደበት ጎሳ ያለመሆናቸውን ሲረዳ “አይቀጥሩም” አለኝ ። እውነትም ሳይቀጥሩት ቀሩ ።



ናይሮቢ እንደደረስሁ አንድ ምግብ አብሳይ ፣ አንድ ዘበኛና አንድ አትክልተኛ ቀጠርሁ ። በየቀኑ የማያቸው ሲጨቃጨቁ ነው ፤ እየተካሰሱ ጦርነት ሆነ ። በኋላ አንዱን አባርሬ ሌላውን ረጅም ፈቃድ ስጠሁትና ሌሎች ቀጠርሁ ። ያባረርኋቸው እየተነታረኩ ስላወኩኝና አንዱ በመርዝ ሊገድለኝ ነው ሲል ፣ ሌላው ደግሞ መተት አዞረችብኝ ብሎ ወጥቤቷን ስለከሰሳት ነው ። እነዚያ ሠራተኞች ከተለያዩ ጎሳዎች (አንዱ ኩኩዩ ፣ ሌላው ሉዎ ፣ ሌላው ደግሞ ዲሹን) ነበሩ ። በኋላ የቀጠርኋቸው ሶስቱም ኩኩዩ ስለሆኑ ሰላም ወረደ፤ጸጥታ ነገሠ።

የኡጋንዳ ዜጎች ከየት እንደሆኑ ሲጠየቁ ኡጋንዳዊ ነኝ ሳይሆን የጎሳቸውን ስም በመጥራት ወይም አኮሊ ያለዚያም ሌላ ነኝ ነው የሚሉ ። በጥቁር አፍሪካ ሶስት አገሮች ብቻ አንድ ቋንቋ የሚናገር ብሔረሰብ አላቸው ። ሶማሊያ ፣ ሌሶቶና ስዋዚላንድ ፤ የብሔራዊ መታወቂያ ስሜት እነዚህ ብቻ ቢሆኑም ውስጥ ውስጡን ጎጠኝነትና የጎሳ ስሜት አለባቸው ። እንደ ዛየር ባሉት ሁለት መቶ ጎሳዎች ባሏቸው ግን ዘረኝነትን ማስወገድ አልተቻለም ፣ሥልጣን መካፈልም አይታይም ፣ አንዱ ሌላውን ጨቁኖ መኖር እንጅ ።

ከቅኝ አገዛዝ መወገድ ጋር ጎሰኝነት አብሮ ሊከስም ያልቻለባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው ። አንደኛ በተለያዩ ጎሳዎች መካከል በጋብቻ መተሳሰር በጣም ውሱን ነው ። ሁለተኛ መገናኛ መንገዶች በገጠሩ ስላልተስፋፉ ከአንዱ ወደሌላው የመመላለሱና የመገናኘቱ እንቅስቃሴ ደካማ ነው ። ሶስተኛ የጎሳና የቤተሰብ መተሳሰር ለአፍሪካ ኅብረተሰብ እጅግ አስፈላጊው ዋስትና ነው ፤ ልክ እንደ አሜሪካውያን ማኅበራዊ ዋስትና ፣ የሕዝቦች ደህንነትና የፖሊስ ጥበቃ ማለት ነው ። አራተኛ ለአፍሪካዊ ዓይነተኛ የማንነቱ መታወቂያ ጎሳው ስለሆነ ያንን መግፈፍ ማለት ከሃይማኖቱ ውጭ የማድረግ ያህል ነው ። አምስተኛ ብሔራዊ ስሜት ለአፍሪካ እንግዳ ነገር ነው ። ከአወቁት ገና ሠላሳ ዓመት ቢሆን ነው ። ስለዚህም ፅንሰ ሀሳብ በውልና በጥልቀት አልገባቸውም ፡ ስድስተኛ የአፍሪካ መሪዎች ከጎሰኝነት ይልቅ ብሔራዊ አመለካከትና እምነት የላቀ ዋጋ እንዳለው ለሕዝቦቻቸው ለማሳመን ያደረጉት ጥረት አነስተኛ ነው ።

የጎሰኝነትን አስቀያሚ ገፅታ ለማየት በብሩንዲ የተከሰተውን ማውሳት ተገቢ ነው ። በዚህች የባህር ጠረፍ በሌላት ደሀ አገር የተለ ያዩ ጎሳዎች ይኖራሉ ። የቆዳ ስፋትዋ አነስተኛ በሆነው ብሩንዲ አራት ሚሊዮን ሕዝቦች ተጨናንቀው ይኖራሉ ። ቅኝ ገዢ ቤልጅጋውያን ከመሠረቷቸው ሁለቱ ከተሞች ቡጅምቡራና ጊቲጋ በስተቀር ፣ቀሪው የሕዝቡ አሰፋፈር በትናንሽ የቤተሰብ መንደሮች ነው ።

በብሩንዲ ሶስት ዋና ዋና ጎሳዎች አሉ ። አንዱ ሁቱስ ፣ ሌላው ቱትሲ ወይም ዋቱሲ ፣ ሶስተኛው ደግሞ ትዋ ይሰኛሉ ። ከአጠቃላይ ሕዝቡ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆኑት ሁቱስ ናቸው ። ዋቱስ የተሰ ኙት ደግሞ አሥራ አራት በመቶ ይሆናሉ ። እነዚህ ጠይምና ፈካ የሚል ቀለም ያላቸውና ረጃጅም ምናልባትም ከኢትዮጵያ ፈልሰው የሄዱ የሚባሉ ናቸው ። ትዋ የሚባሉት ድንክየዎች ሲሆኑ በዋቱሲ ጎሳ ወደደረቅ መሬቶች የተባረሩ ናቸው ። ለአያሌ ዘመናት ዋቱሲዎች ብዙኃኑን ሁትስ በፊውዳል ከበርቴነት ረግጠው ሲገዙዋቸው ኖረ ዋል ። ለብዙ ትውልዶች ዋቱሲዎች የበላይ ሆነው በመኖር ራሳቸውን እንደአዋቂና የበላይ ቆጥረው ይኩራሩ ነበር ።

ቤልጅየም በ1962 ነፃነታቸውን ሰጥታ ስትወጣ ብርቱ ፉክክር ተነሳ ። በዚህም የበላይ ሆነው የኖሩት ዋቱሲዎች ስጋት አደረባቸው ። ሥልጣናቸው ወደብዙኃኑ መዛወሩ እንደማይቀር አሳሰባቸው ።

በ1972 ዋቱሲዎች ብዙኃኑን ሁቱዎች መጨፍጨፍ ፈለጉ ። በተለይም የተማሩትን ሁቱዎች እያሳደዱ መግደልና ከሥራ ማባረር ጀመሩ ። በሶስት ወራት ውስጥ ብቻ 200 000 ሁቱስ ተገደሉ ። በወቅቱ በዚያ የነበረው የሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጠኛ ሜስለር ስለሁኔታው ሲገልጽ ፣ "የቀሩት ጥቂት ሁትስ ብቻ በመሆናቸው ተገረ ምሁ ፤ ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማለቂያ በዋርሶ ጥቂት አይ ሁዶች ብቻ ከጭፍጨፋ የዳኑትን ዓይነት ነው" ብሏል ።

ብዙ ሁቱዎች የተገደሉት በሌሊት ከቤታቸው እየተወሰዱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ሪፖርት እንዲያደርጉ እየተጠሩ ነበር ። ለግድያ መጠራታቸውን እያወቁ ሁቱዎች ትዕዛዙን አክብረው



ይሄዱ ነበር ። ፖሊስ ጣቢያው በሬሳ ሲሞላና መግደል ሲሰለቻቸው ተራ የሚጠብቁትን ሁቱዎች ለነገ ተመለሱ በማለት ያሰናብቷቸዋል ። ከዚያም የሞቱትን አስከሬን በግልጽ መኪና ጭነው በአውሮፕላን ጣቢያው ወደተዘጋጀ መቀበሪአቸው ያግዛሉ ። ኮታ ሞልቶ የተመለሱት ደግሞ በተከታዩ ቀን እንደገና ሪፖርት ያደርጋሉ ። ማምለጥ የሞከ ሩትንም ድንበር ጠባቂ ዋቱሲዎችና ዉዙሪያው የተመደቡት ይመልሷ ቸዋል ። በቀን ያን ሁሉ የመቅበሩ ሂደት ስላጋለጣቸው መንግሥት ቀብሩን በሌሊት በመብራትና በቡልዶዘሮች እንዲካሄድ አደረገ ።

በሩዋንዳም ተመሳሳይ ሁኔታ ታፈጽሟል ። በ1959 ብዙሃኑ ሁቱስ ዋቱሲ መሪዎችን በመገልበጥ የእነሱን ዘሮች እያሳደዱ መግደል ጀመሩ ። በጥቂት ቀናት 100,000 ገደሉ ። ይህንን ሁኔታ የተመለከ ቱት እንግሊዛዊ ፈላስፋ ራስል "እጅግ አስፈሪና ሥልት የተከተለ የዘረኝነት ጭፍጨፋ በመሆኑ ከአይሁዶች በናዚ መጨፍጨፍ ወዲህ ያን የመሰለ አሳዛኝ እልቂት ያየንበት ሁኔታ ነበር" በማለት ገልጠ ውታል ። እኒህን ፈላስፋ ከመሰሉ ጥቂት ሰዎች ተቃውሞ በስተቀር ከአፍሪካም ሆነ ከዓለም ዙሪያ ተቃውሞ ያሰማ አልነበረም ። ከአፍ ሪካ አንድነት ድርጅት የሄደው ተወካይ በጭፍጨፋው ወቅት ተልኮ ከተመለከተ በኋላ የሩዋንዳን ፕሬዚዳንት ሚኬምቤሮ በማድነቅ አገራቸውን በሥርዓት በማስተዳደር ላይ መሆናቸውን ሪፖርት አደረገ ። በዚያ የነበሩ ሚሲዮኖችና የክርስትና ሃይማኖት መሪዎችም ያለአንዳች ተቃውሞ በእግዚአብሔር ስም ሥራቸውን ቀጠሉ ። አንድም ሀገር ዲፕሎማቲክ ግንኙነቱን እንኳ አላቋረጠም ። አለም አቀፍ የዳኞች ኮሚሽን ለምርመራ ሲሄድም በከፍተኛ ሪሰፕሽን ተቀበሉት ፤ ከግብዣው ቦታ በመቶ ሜትር ርቀት ግን ሃያ ሁቱዎች በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እስኪሞቱ እየተደበደቡ ነበር ።

የደቡብ አፍሪካ ጥቂት ነጮች መንግሥት ይህን የመሰለ ነገር ቢያደርግ ኖሮ የአፍሪካውያን መንግሥታት ጩኸት እንደሳተ ገሞራ አህጉሩን ባናወጠው ነበር ። ነጮች በጥቁሮች ላይ በደል ከፈጸሙ በአፍሪካ ዘረኝነት ነው ። ጥቁሮች የራሳቸውን ጥቁር ሕዝብ ቢበድሉና ቢገድሉ ግን በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አለው።

በብሩንዲ ሕይወት አሁንም እንደዚያው ነው ። 150 000 ሁቱሲዎች ወደ ጎረቤት ዛየር ፣ ታንዛኒያና ሩዋንዳ ተሰደዋል ። የቀሩትም በፍርሃትና አቅም በማጣት በጭሰኝነት ዋቱሲዎችን እያገለገሉ ይኖራሉ ። በአገሪቱ ጦር ሠራዊት ውስጥ አንድ ሁቱሲ ዘር የለም ። በትምህርት እንዲገፉም ሆነ ሀብት እንዲያፈሩ ፣ አይፈቀድላቸውም ። ሥልጣን ሁሉ በዋቱሲዎች እጅ ሆኖ ቀረ ። ጎሰኝነት በአፍሪካ ይህን የመሰለ መልክ አለው — ሥልጣን ።

በአፍሪካ ብዙ ብሔረሰቦች የመኖራቸውን ያህል የቋንቋዎች ብዛትም ያንኑ ያህል ነው ። አፍሪካውያን ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎቻቸው ከወረሱት ግማሽ ደርዘን ቋንቋ ሌላ 750 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች አሏቸው ። ካናዳ በሁለት ቋንቋዎች መኖር ምክንያት አንድነትዋ የላላ ሆኗል ፤ ቤልጅግም እንዲሁ ናት ። በአፍሪካ ግን ከሚሊዮን የማያንሱ ሕዝቦች የሚናገሩዋቸው ቋንቋዎች ብቻ ሃምሳ ይደርሳሉ ። በምሥራቅ ስዋሂሊ፣ በምዕራብ ሀውሳ ቋንቋ ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ይናገራቸዋል ። አፍሪካ በቋንቋዎች ልዩነት ከራስዋ ጋር የማትግባባ ራሱዋን የማትረዳ ሁናለች።

በአፍሪካ ካሜሩን ብቻ ሁለት የመንግሥት የሥራ ቋንቋዎች አሏት ፤ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ። ነገር ግን በእነዚህም ለመግባባት ችግር ስላለ ስብሰባዎች እንደተበጣበጡ ነው ። ስለዚህ ሁሉም የሚቀናቸው ሁለቱንም ትተው ፒጅን እንግሊዝኛ መናገር ነው ። የሚግባቡትም በዚህ ብቻ ነው ። ይህ ፒጂን እንግሊዝኛ የተፈጠረው በባሪያ ሽያጭ ዘመን ሲሆን ፤ ስዋሂሊም እንዲሁ ነው ። ለባርያ ገዢዎች ፣ ነጋዴዎችና ሻጭ ለሆኑ አፍሪካውያን መግባቢያ ሆኖ ተፈጠረ ። ዛሬ ይህ ቋንቋ በጽሁፍ የሚገለፅ ቋንቋ ሆኖ ብዙ እንግሊዝኛ ቃላት በአፍሪካውያን ሰዋሰው ተቀይጠው የሚቀርቡበት ነው ።

የአፍሪካ በቅኝ ግዛት መውደቅ ስድስት ያህል ቋንቋዎችን አመጣላት ። እነዚህም እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ጀርመንኛ ፣ እስፓንኛ ፣ ጣሊያንኛና ፖርቱጋልኛ ናቸው ። እነዚህም አፍሪካውያን ከውጭው ዓለም እንዲግባቡበትና እርስ በርሳቸውም እንዲነጋገሩበት ረድተዋቸው ። ነገር



ግን ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን አገሮች ድንበሮች ሲወስኑ የቋንቋ አንድነት እንዲኖር ያደረጉት ጥረት ኢምንት ነው ።

በኬንያ የፓርላማው መነጋገሪያ ቋንቋ ስዋሂሊ እንዲሆን በ1975 ጆሞ ኬንያታ ወስኑ ። ከጥቂት ወራት በኋላ ሁኔታው ስላላዋጣ እንግሊዝኛ እንዲሆን ተደረገ ። በኬንያ እንግሊዝኛና ስዋሂሊ በስፋት ይነገራሉ ። ራቅ ባሉ ገጠሮች ያለው ከብት አርቢ ግን ከጎሳው ቋንቋ ሌላ አይችልም ። ኬንያንም ሆነ ሌሎችን አገሮች ወደ እውነተኛ ሀገራዊ አንድነት ስሜት እንዳይጎለምሱ የሚያግዳቸው ይኸው የቋንቋ ልዩነቶች የሚያስከትሉት ችግር ነው ። የሚያስተባብራቸው ቋንቋ ሳይኖር ኬኒያውያን እንዴት አንድ ሕዝብ ነን ብለው ሊያምኑ ይችላሉ ? ለሀገር ግንባታና ለአንድነት ትልቅ ኃይል ያለው አንዱ ጉዳይ ቋንቋ ነው ።

ከአፍሪካ ሕዝብ ግማሹ ገና ከታዳጊ ወጣት እድሜ በታች ያለ ነው ። የወሊድ ብዛት በአንዳንድ ቦታ እያደገ ነው ። እንደ ሩዋንዳ ያሉ አገሮች በሕዝብ ብዛት ተጨናንቀዋል ። ሆኖም የአፍሪካ ችግር የሕዝብ መብዛት ሳይሆን አሰፋፈሩ በአንዳንድ ቦታዎች ከሚገባ በላይ የተጨናነቀ መሆኑ ነው ። ለምሳሌ ዛምቢያ ከካሊፎርንያ ሁለት እጅ ትበልጣለች ፤ የሕዝቧ ብዛት አምስት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብቻ ነው ። ሩዋንዳ በተቃራኒው ሜሪላንድን ብቻ የምታክል ስትሆን የሕዝቧ ብዛት አራት ሚሊዮን ተኩል ነው ። የአፍሪካ የቆዳ ስፋት ትልቅና ከሕዝቡ ብዛት ጋር ሲነፃፀርም እንደ ሶቪየትና ሰሜን አሜሪካ ቢሆንም የአህጉሩ አንድ ሶስተኛው ሰው ሊኖርበት የማይችል በረሃ በመሆኑ ልዩነት አለው ። ለምሳሌ በኬንያ ለእርሻ የሚሆነው መሬት ሁሉ ለምቷል ። ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር ሕዝቡን ሊመግብና በቂ አገልግሎት ሊያቀርብ የቻለ አገር የለም ።

በአፍሪካ የሕዝብ ብዛትን ለመግታት የወሊድ ቁጥጥር ማድረግ አወዛጋቢ ስለሆነ ብዙ የአፍሪካ አገሮች አይሞክሩትም ። ያን ማድረግ የጎሳዎችን እድገት እንደማፈን የሚታይ ነው ፣ ወላጆችን በስተእርጅና አርሶ የሚያበላቸው ማሳጣት ነው ፤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እምነቶችን ማንኳሰስ ነው ። አንዳንድ መንግሥታት ሞራላዊ እንደማይሆን ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ኢምፔሪያሊዝም የሶስተኛውን ዓለም ሕዝብ ለመ

ቀንስ የሚያቀርበው መሠሪ ሻጥር ነው ይላሉ ። ይህ ሁሉ ምክንያት ግን አፍሪካ ዛሬ በሕዝብ ብዛት እየሰመጠች እንዳትሄድ ለማዳን የሚደረገውን ጥረት የሚያንኳስስ ነው ። አፍሪካ በወሊድ ብዛት ከሌሎች አህጉሮች ሁሉ የላቀና ፈጣን የሕዝብ እድገት የሚታይበት ነው ።

የአፍሪካ መንግሥታት እየተዳከሙ ፣ የሕዝቡ አመፅ እየተቀጣጠለ ፣ ስደት እየበዛ ፣ ግጭትና ጦርነት እየበረከተ ፣ ምርቱ ከሕዝቡ ቁጥር በእጅጉ እያነሰ ፣ የውጭ መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ግጭቶችን እያባባሱ ፣ አንዱ ከምዕራብ ሌላው ከምሥራቅ ወግኖ እየተቆራቆሰ አህጉሪቱ ከራሷ ጋር የተጣላች ሆናለች ።

የእስልምና ሃይማኖት በሚከተሉት አፍሪካውያን አራት ሚስቶች ማግባትና ከሃያ ልጆች በላይ መውለድ የተለመደ ሆኗል ። ሌላው ቀርቶ በኬንያ እንኳን ብዙውን ጊዜ ለአንድ ሚኒስትር ሁለት ሚስቶች ማግባት የተለመደ ነው ፤ አንዷ ገጠር ትቀመጥና በሳምንት አንድ ቀን ይጎበኛታል ፤ ሌላዋ ከተማ ሆና በየግብዣው ታጅበዋለች ።

በ1977 ጆን ቤዴል ቦካሳ በዚያን ጊዜ የማዕከላዊ አፍሪካ መሪ ፅላሳኛ ልጃቸው ሲወለድ ብሔራዊ በዓል እንዲሆን አወጁ ። የመጀመሪያውን የደስታ መግለጫ የላኩት የዩጋንዳው ፕሬዚዳንት የነበሩት ኢዲ አሚን ራሳቸው ሰላሳ ሁለት ልጆች እንዳሏቸው ጠቅሰው “እግዚአብሔር መርቆህ ተጨማሪ ልጆች ይስጥህ” ሲሉ ተመኝተውላቸዋል ።

ገበሬው ቤተሰቡን መደገፍ ሲሳነው ሥራ ፍለጋ ወደ ከተማ ይጎርፋል ። በዚያም ሥራ ሊያስገኝለት የሚችል ሙያ እንደሌለው ሲረዳ እንዲሁ መባዘንና መንገዶችንና ሻይ ቤቶችን በማጣበብ ዝንቡን ሲያባርር ይውላል ። የሥራ አጡን ብዛት ይ ጨምራል ፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያጣብባል ፤ በዚህም የተነሳ የትራንስፖርት እጥረት ይፈጠራል ፤ ሆስፒታሎች ይጨናነቁና በሆስፒታል አልጋዎች ለሁለት መተኛት ይመጣል ፤ በየጊዜው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ይቋረጣል ፤ በየማዕዘኑ ወንጀል መፈጸም የተለመደ ችግር ይሆናል ፤ ከጨለመ መዘዋወር በክርስቲያን የአፍሪካ አገሮች አደገኛ ሆኗል ። እስልምናን በሚከተ



ሉ አገሮች ግን የሃይማኖታቸው ሥነ ምግባር ስለሚያዝዛቸው በጨለማ መዘዋወር አስጊ አይደለም ። በዛንዚባር ፡ በሞቃዲሾ ፡ በሌሎችም የእስላም አገሮች ከተሞች ዘረፋ የለም ።

ከተሞች በሕዝብ ብዛት በተጨነቁ ቁጥር መንግሥታት የገጠሩን ልማት ቸል ብለው ለከተሞች አገልግሎት የላቀ በጀት ይመድባሉ ። ለምሳሌ በኬንያ ዋና ከተማ በናይሮቢ በሚገኘው ኬንያታ ሆስፒታል 452 ዶክተሮች ሲኖሩ በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍለ ሀገር ግን ያለው አንድ ዶክተር ብቻ ነው ።

አፍሪካ ከፍተኛ ቅምጥ ሀብት ቢኖራትም የሚታየው ድህነቷ ነው ። በዓለም ከሚገመተው በውሃ የኤሌክትሪክ ማመንጨት ቅምጥ ኃይል አርባ በመቶው በአፍሪካ የሚገኝ ነው ። አህጉሪቱ አያሌ የአልማዝና ክሮሚየም ሀብት ፣ በካፒታሊስቱ ዓለም ካለው የዩራንየም ሀብት ሰላሣ በመቶ ፤ ከዓለም ሃምሳ በመቶ የሚሆነው የወርቅ ክምችት ፤ ከዓለም የኮባልት ክምችት ዘጠና በመቶ ፤ በፎስፌት ሃምሳ በመቶ ፤ በፕላቲኒየም አርባ በመቶ ፤ በከሰል ሰባት ተኩል በመቶ ፤ በነዳጅ ዘይት የዓለም ስምንት በመቶ ክምችት ፣ በተፈጥሮ ጋዝ አሥራ ሁለት በመቶ ፤ በብረት ማዕድን ሶስት በመቶው ፤ በሚሊዮን ጋሻ የሚቆጠር ድንግል የእርሻ መሬት የሚገኘው በአፍሪካ ነው ። እንዲህ በተለያዩ ቅምጥ ሀብቶች በብዛት የታደለ አንድም አህጉር የለም ።

የወጣቶች መብዛትና የቅምጥ ሀብት መብዛት ግን ለልማትና ለግስጋሴ ምንም መሠረት አልጣለም ። ነዳጅ ዘይት የማይሸጡ አራት አገሮች ማለትም ኬንያ ፡ ካሜሩን ፡ አይቮሪኮስትና ማላዊ ትርጉም የሚሰጥ ልማትና የፖለቲካ መረጋጋት የታየባቸው ሲሆኑ የተማሩ ሰዎችም እየበረከቱባቸው ነው ። በቀሩት አገሮች ግን የሚታየው ውድቀት በመሆኑ በአጠቃላይ አፍሪካ ወደ አራተኛ ዓለምነት እያዘቀጠች ናት ።

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ምክር ቤት ዘገባ መሠረት የጥቁር አፍሪካ ነዳጅ አልባ አገሮች ከነፃነት በኋላ የባሰ እየቆረቆዙ ናቸው ። የምግብ እጥረት ተባብሶ ብዙዎቹ ተመጽዋች ሆነዋል ። የጥሬ ምርታቸው ዋጋ በዓለም ገበያና በአገር ውስጥም ማቆልቆሉና የሚገ

ዙት ሸቀጥ ዋጋ መጨመር ሌላው ማጣጣም ያልተቻለ ጉዳይ ነው ።

በአውሮፓ ለ580 ሰዎች አንድ የሕክምና ዶክተር ሲኖር የተሻ
ለች በተባለችው ኬንያ ለ25600 ሰዎች አንድ ሐኪም ብቻ አለ ።
እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ወጣቶች በአፍሪካ ለመማር የቻሉት
አሥራ አንድ በመቶ ብቻ ናቸው ። በእስያ ሰላሳ አምስት በመቶው ፤
በደቡብ አሜሪካ አርባ አምስት በመቶው የትምህርት ዕድል አግኝ
ተዋል ። የከፍተኛ ትምህርት እድልም እንዲሁ ከሌሎች በብዙ ያነሰ
ነው ። በአፍሪካ የማይማን ቁጥር ሰባ አምስት በመቶ ይደርሳል ።

የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት ሲጀምሩ አህጉሪቱ
ከሚያስፈልጋት የምግብ እህል ዘጠና አምስት በመቶ ተመርቶ ነበር።
ዛሬ ግን ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር ሁሉም ሸማች ሆኗል ። በ2000
ዓ.ም. አፍሪካ ግማሹን ሕዝብ ለመቀለብ የሚያስፈልገውን ከውጭ
መግዛት ይኖርባታል ። በ1976 ኬንያ ስገባ ሁሉም ነገር በሽበሽ ነበር ፤
በ1980 ልመለስ አካባቢ እንደ ቅቤ ፣ ወተት ፣ በቆሎና ዱቄት የመሳሰሉ
መሠረታዊ ሸቀጦችን ለመግዛት በሰልፍ መደርደር ግድ ሆነ ።

አህጉሪቱን ይህ ሁሉ ችግር ከቧት እያለ የአፍሪካ መሪዎች ድክ
መታቸውንና መጥፎ ባህሪያቸውን ለመመርመር ጥረት ባለማድረግ
ችግሮችን ሁሉ የሚያሳብቡበት ይፈልጋሉ ። ለአፍሪካውያን በራስ ላይ
ሂስ ማካሄድ አይዋጥላቸውም እንጅ የተዝረከረከ አሠራር ያላቸው
መንግሥታት ፣ የተናገሩትን በተግባር የማይተረጉሙ መሪዎች በሽበሽ
ናቸው ።

በሶማሊያ አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በአማካይ ስምንት
መቶ ሠራተኞች አሉት ። ብዙዎቹ ባለሥልጣኖች እንደሚሉት ግን
በቀን ከስድሳ ሠራተኛ በላይ ሥራው ላይ አይገኝም ። በዛየር የከተማ
አውቶቡሶችን ለመጠገን በአንድ ወቅት ከተገኘው አንድ ነጥብ
ስምንት ሚሊዮን ዶላር የርዳታ ገንዘብ በየደረጃው ሲቀናነስለት ለመ
ገናኛ ሚኒስቴር የደረሰው ሁለት መቶ ሺህ ብር ብቻ ስለሆነ ምንም
መጠገን አልተቻለም ። በኬንያ ቤቴ እየተዘረፈ ነው ብሎ ለፖሊስ
ጣቢያ የሚደውል ሰው የሚያገኘው መልስ መኪና ስለሌለን መኪናህን



ይዘህ ናና ውሰደን የሚል ነው ። በዛምቢያ የሚጠግናቸው ያጡ
በመቶ የሚቆጠሩ የመንግሥት መኪናዎች ያለሥራ ቆመው በመጋ
ላይ ናቸው ። የተበላሹትን ጠግኖ ከመገልገል ይልቅ አዲስ መኪናዎ
ችን በስጦታ ወይም በብድር ማስመጣትን ይመርጣሉ ።

አንድ ወቅት በሕዝቡ ስንፍና የተናደዱት የዛምቢያ መሪ ኬኔት
ካውንዳ "በሚቀጥለው ዓመት ሁሉም አምስት ሚሊዮን ሕዝብ እንደ
አሁኑ ሰነፍ የሚሆኑ ከሆነ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣኔን እለቃለሁ ፤
የሰነፎች መሪ መሆን አልፈልግም" ሲሉ አማረው ነበር ። ይሆን
ቃል ፈረንጅ ቢናገረው ኖሮ ዘረኝነት በተባለ ነበር ።

አንድ የአፍሪካ መንግሥት የፈለገውን ያህል ሰው ቢያስገድልና
"ለማኅበራዊ ግንባታ" ነው ቢል ተቀባይ አለው ። የምዕራብ ዲፕሎ
ማት ይህን ተግባር አረመኔያዊ ነው ቢለው ግን ከዘረኝነት የመነጨ
ሂስ ነው ይሉታል ።

አፍሪካ በኢኮኖሚ እያሽቆለቆለችና በፖለቲካ እየባዘነች አህጉ
ራቱዋ ዛሬም ከመቶ ዓመት በፊት እንደነበረችው ለብዝበዛ የተጋለ
ጠች ናት ። ምሥራቅና ምዕራብ አንዱ ከአንዱ አገር ሌላ ጊዜ ከሌላው
እየተወዳደ የጦር መሣሪያና የልማት ርዳታ በመለገስ ጭራ ሊያደር
ጓቸው ጥረዋል ። በዚህም አፍሪካ በውጭ ተፅዕኖ ሥር ወድቃ በራ
ሱዋ ጉዳይ ላይ ያላት ቁጥጥርና ወሳኝነት እየተዳከመ መጥቷል ።

የቶጎ ፕሬዚዳንት ኤቲኔ ኢያደማ ሲናገሩ "አፍሪካን ለአፍሪካ
ውያን መተው የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ፤ ለአፍሪካ ችግ
ሮች መፍትሄ ማግኘት እንችላለን ፤ ምሥራቅና ምዕራብ በውስጥ ጉዳ
ያችን ጣልቃ መግባታቸውን ማቆም አለባቸው" ብለዋል ።

ይህ አባባል በአፍሪካ የተለመደ ቢሆንም ከልብ የሚሰነዘር
ስላልሆነ ባዶ ነው ። ምሥራቅና ምዕራብ ጦር መሣሪያ ፣ ገንዘብና
ቴክኖሎጂ ባይልኩላቸውማ ከምላ ኃይል ሁሉም መንግሥታት በወራት
ውስጥ ይንኮታኮታሉ ። አፍሪካ እንደ አሁኑ የውጭ ጥገኛ ሆና አታ
ውቅም ። ናይጀሪያ ነዳጅ ሽያጭዋ በ1980 በቀን ስድሳ ሚሊዮን
ዶላር በመድረሱ ከዚህ ጥገኝነት ወጥታለች ። ቢሔራዊ ደሞንታቸው

የተደፈረ ሲመስላቸው ሁሉም የአፍሪካ አገሮች ከአሁኑ ውጭ ርዳታ ይጠይቃሉ ፤ ራሳቸውን መከላከል ስለማይችሉ ። አንጎላና ኢትዮጵያ ማርክሲስት አገሮች በመባል ከሶቪየት ያጋበሱትን ታንክና መድፍ እንዲሁም ሮኬት ወንጫፊ በማሰለፍ ለጦርነት ያሰፈስፉሉ ።

አፍሪካውያን የተካኑት በደፈጣ ውጊያ ነው ። ምክንያቱም የሚገባቸው ነፃነት የሚለው ቃል ነው ። በትልቅና በተደራጀ ጦር ኃይል ሲሰባሰቡ ግን ውጤታማነታቸው ይዳከማል ፤ ምክንያቱም የሀገር ስሜቱ ከጎሳ ስሜቱ ያነሰ ስለሆነ ነው ። ጦሩ ከመዋጋት ይልቅ ዝርፊያ ይቀናዋል ።

የቅኝ አገዛዝ መወገድ ለአፍሪካ ሐቀኛ ነፃነት አላመጣላትም ። የውጭ ብድር እዚያ ላይ ተከምሮባትና በርዳታ ሰጭዎች ብርታት ነፍሷ ቆይቶ በምፅዋት የሚኖሩ አገሮች ስብስብ ሆና ቀርታለች ።

በአፍሪካ የተፈጥሮ አደጋዎችም እጅግ የበዙ ናቸው ። የፀሐይ ሙቀት ፣ በሽታ የሚያመጡ ነፍሳት መብዛት ፣ የመስራት አቅምን የሚያዳክሙ ናቸው ። በተለይ በሽታ ከተነሳ በአሥር ሺዎች ሳያዳርስ መቆሚያ የለውም ። የአንበጣ መንጋ የሚያደርሰው ጥፋት ልክ የለውም። ድርቅ ይመላለስባታል ፤ ዝናቡም ያለቅጥ የሚያይልበት ጊዜ አለ ። ተፈጥሮም እንደ ሰው ክፉኛ ሕዝቡን ተፈታትኖታል ፤ ከአገሩ አፈና ቅሎታልም ።

ጥቁር አፍሪካ በ1980ዎቹና በ1990ዎቹ እንዳለፈው ሁሉ ተስፋ ስታደርግ ፣ ወሬዋን ስትጠርቅ ፣ መጋፈጥ ያለባትን የሞትና ሽረት አቢይ ጉዳዮች ቸል ብላና የሚያጋጥማትን ሁሉ "ከአቅም በላይ" እያለች ትቀጥል ይሆናል ። ወይም ምናልባት ከእንቅልፍ ነቅታና ተጨባጩን እውነታ ተረድታ በተገቢ ዕቅድና በመልካም ዕድል የራሷን ዕድል በእጅዋ አድርጋ ችግሩን ለመወጣት ትጣጣር ይሆናል ። ያም ሆነ ይህ ያለፉት ሃያ ዓመታት ልምድ ያስገነዘበን ትምህርት ግን እድገት አይቀርም የሚል አይደለም ።



ምዕራፍ ሁለት

# ያለፈውና የአሁኑ አለመጣጣም

"ወደኋላ መመለስ የለም ። በየመንደሩ ያሉት አዛውንቶች ነገሮች ሁሉ እየተለወጡ መሆኑን ማወቅና በእነሱ የወጣትነት ዘመን የነበረው ወግና ባህል እየከሰመ መሄዱን መቀበል አለባቸው" ።

አሊቨር ሊቶንዶ
የኬንያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ

ከመጋቢት እስከ ግንቦት ባሉት የኬንያ የዝናብ ወራት የማታሬ ሸለቆ መንገድ ጭቃ እስከ ቁርጭምጭሚት ይውጣል ። በነዚያ ቀዝቃዛ ወራት አካባቢውን ከሩቅ ሲመለከቱት የወረቀት ብጥስጣሽ ፣ የእንጨት ስብርባሪውና ሁሉ ዓይነት ውዳቂ ተዝረክርኮ ትልቅ የቆሻሻ ማራገፊያ ሸለቆ ይመስላል ። በናይሮቢ በስተሰሜን ከአንድ ኪሎ ሜትር በላይ የሚሆን ሥፍራ ላይ የተዘረጋው ይህ ሠፈር ፀጥታ የነገሠበት ሆኖ ምንም ሕይወት አይታይበትም ። በማታ በዚያ አካባቢ በመኪና ለሚያልፍ ሰው ምንም ሰው የሚኖርበት አይመስልም ።

ይሁን እንጂ ይህ ሸለቆ ከመቶ ሺህ የሚበልጡ ሰዎች መኖሪያ ነው ። በዚህ የሚኖሩት ሰዎች በከተማ የተሻለ ኑሮ እናገኛለን ብለው በገጠር ያሉ የትውልድ ቦታቸውን ጥለው የመጡ ናቸው ። ነገር ግን ከተማው ሥራም ሆነ መጠለያ ሊያስገኝላቸው አልቻለም ። ስለዚህም ከናይሮቢ ከተማ ውጭ ባለው የድሆች ሠፈር ተጨናንቀው ይኖራሉ ። እንደ ማታሬ ሸለቆ የመሰለው ኤሌክትሪክና ውሃ የሌለው መኖሪያ ፣ የትውልድ መንደራቸውን ትተው ወደ ከተማ ለሚጐርፉ አፍሪካውያን ተስፋቸው የተቀበረበት ሥፍራ ሆኗል ።

አንድ ቀን ወደዚህ ሸለቆ ሄድሁና ጭርንቁስ ሠፈሮችን ስጐበኝ የወጣትዋ ማሪል ድምፅ አልፋ ሬልዎ የሚል መልእክት ። ማሪያው ጨርቃዋ በተባለ ቤት ውስጥ የምትኖር አንዲት ሴት ደጃፉ ላይ በቆሎ ትቀቅላለች ። የማሪያው ዝናብ እንዳይገባበት ጉንበስ ብላ ሽፍንፍ ላች ። ላነጋግራት ፈልገሁና ለማወራላት ጊዜ ትንሽ ቆንቋም ለሰማት ተቋማዎችን መወያየት ጀመርን ። ከዚያ አንድ የተበጣጠሱትና የተጫጨረች ወረቀት አወጣችና በቀስታ እየዘረጋች እንድመለከተው ሰጠችኝ ።

"ይኸውልህ ሆና ሁልጊዜም በትምህርት የምታገኘው ማርክ እጅግ በጣም ጥሩ (ሌ) ነበር" አለችኝ ። ወይዘር ኔሊ አርባ ዓመቷ ቢሆን የአሥራ ሰባት ልጆች እናት ናት ። የልጆችዋን ሪፖርት ካርድ ተቀብላችኝና ከአልጋዋ ሥር ያለው የእንጨት ሳጥን ውስጥ ወረወርችው ። ሆና ትምህርት ማጽረጧንና ይሆች የአሥራ አምስት ዓመት ልጅዋ አሁን የት እንዳለችም እንደማታውቅ ነገረችኝ ። ሌሎችም ልጆችዋ ሁሉ ትምህርታቸውን አቋርጠዋል ፤ ሆና ግን ያቋረጠችው በተለይዋ ዓመታዊ የትምህርት ቤት ክፍያዋን በሰባ ሺልንግ (ሰባት ዶላር) ሊከፍሉላት ስላልቻሉ እንጅ ጉበዝ ተማሪ እንደነበረች እናትየዋ አጫወተችኝ ። ሌሎች ልጆቿ ግን ማግኘቹ በናይሮቢ ጉዳናዎች የሚንከራወዱ ለማኞችና መኪና አጣቢዎች ሆነዋል ። ማግኘቹ ደግሞ ሌሳንት ባይጀምሩ እንዲለቀሩ ሥጋት አላት ። ባለቤትዋ በየቀኑ ወደ ናይሮቢ በመጓዝ የቀን ሥራ ቢፈልግ እየዋለ ባይቀናው ይመለሳል ። በዓመት ውስጥ ለድስት ቀን ያህል የቀን ሥራ ቢያገኝ ነው ። ዛሬም ምንም ጥሩ ዜና ወይም ገንዘብ ይዞ እንደማይመጣ ታውቃለች ።

"በሕወትን ምን እንደምናደርገ አላውቅም ፤ ኑሮ አይደለም ። ሰዎች ቢታመሙ ሐኪም ቤት ሄደው መታከም አይችሉም ፤ እዚሁ መሞት ብቻ ነው ። ገጠርም ብንመለስ ያው ነው ። እዚያም ቢሆን ገንዘብ የለም ፤ ሥራ የለም ፣ ሐኪም የለም ። እኛ የሚያስፈልገን ሆናን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ነው ። እሷ ጉበዝ ስለሆነች ተምራ ሥራ ለማግኘትና እኛን ለመርዳት ትችላለች ።" አለችኝ ።



የናይሮቢ ከተማ ምክር ቤት በዚያ ሸለቆ የሚኖሩትን ያለሕጋዊ ፈቃድ የሰፈሩ ናቸው በሚል በየጊዜው ቡልዶዘር እየላከ የካርቶን ቤታቸውን ይጠራርግባቸዋል ። ስለዚህም በየጥዋቱ ነዋሪዎቹ ዳሶቻቸውን አፈራርሰው ካርቶኖቹን ይደረድሩና ማታ እንደገና ገጣጥመው ይተኛሉ ። ይህን ለማድረግ የሚወስድባቸው ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው ። የዶዘር ድምፅ ከሰሙ ወዲያው ካርቶኖቻቸውን ይዘው ይሸሻሉ ። ዶዘሮቹ ካፈራረሱት በኋላ ሸለቆው ያለሰው የሚሰነብተው ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው ። ወዲያው ነዋሪዎቹ ይመለሱና መልሰው ካርቶኖቻቸውን በማደጋገፍ ያንኑ ጭርንቁስ ሰፈር ይመሠርታሉ ። ምንም እንዳልተደረገ ሁሉ ሕይወትም እንደቀድሞው ይቀጥላል ።

በዚህ ሸለቆ ስላለው ሕይወት ለሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ሪፖርት ጻፍሁ ። ታሪኩን ያነበቡት ሰዎች የወይዘሮ ኔሊን ልጅ ሆናን ወስደው ለማስተማር ወይም በናይሮቢ ትምህርቷን ለመቀጠል እንድትችል ለመርዳት ፍላጎታቸውን ገለጹልኝ ። እኔም ኔሊን ፍለጋ ወደ ማታሬ ሸለቆ ሄድሁ ። ሸለቆው እንደገና በዶዘር ታርሶ መንደሩ እንደገና በመቆም ከመቶ ሺህ ሕዝብ መሀል ኔሊን ፈልጌ ማግኘት አቃተኝ ። ነገሩ ልክ ስታዲየም ውስጥ ገብቶ ከተጠቀጠቀው ሕዝብ አንድ ሰው ፈልጎ የማግኘት ያህል ሆነብኝ ፤ አልቻልሁም ። ሁለት ሰዐት ሙሉ ስፈልግ ቆይቼ ለመልካም ነገር ያልታደሉ ብዬ ወደ ቢሮዬ ተመለስሁ ።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ከኬንያ እስከ አይቮሪኮስት ፣ ከኒጀር እስከ ቦትስዋና የሕይወት ጉዳናቸው ያው እንደ ኔሊ ነው ። ከእርሻው ይልቅ በከተሞች የተሻለ ኑሮ እናገኛለን ብለው በማሰብ የጐረፉ ናቸው ። የዚህ ፍልሰት ውጤት የከተማ ቅዠት ፣ ወንጀል ፣ ድህነት ፣ የሥነልቦና ቀውስ ሆን ። በዚህ መልኩ የናይጀሪያ ዋና ከተማ ሌጎስ በ1970 የሕዝቡ ብዛት 300 000 ብቻ የነበረ ቢሆን በአሁኑ ጊዜ ከሰባት ሚሊዮን በላይ ነው ። በ1960 ከግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርባት የጥቁር አፍሪካ ከተማ የዛየር ኪንሻሳ ብቻ ነበረች ። በአሁኑ ጊዜ ግን አሥር ከተሞች አሉ ።

በኬንያ ዝቅተኛው የወር ደመወዝ አርባ ሦስት ዶላር ሲሆን ፥ ሥራ ያልያዘው ቁጥር ግን አርባ አምስት በመቶ ነው ። በሁሉም የአፍሪካ አገሮች እንደሆነው ሁሉ ሥራ ሳጡ የሚሰጥ ድጎማ የለም ። ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ በየዓመቱ ከሚመረቁ 1800 ተማሪዎች አሥራ ሦስት በመቶው ሥራ ለማግኘት ቢያንስ ሶስት ዓመት ያህል ይጉላላሉ ። ለምሳሌ ከላይኛው ቮልታ ሕዝብ 600,000 የሚሆነው ወደ ጎረቤት አገሮች እየሄደ ጉልበቱን በመሸጥ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ተሰማርቶ ይመለሳል ። በጅቡቲ ደግሞ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነው ሥራ ስለሌለው በቅርብ ሊያገኝ የሚችለው የሥራ ቦታ በባህረ ሰላጤው አገሮች ነው ።

በኬፕ ቬርዴ ከሚኖሩ ዓሣ አስጋሪዎች አብዛኛው የሚኖሩት በማሰቹሰትስና በሮድ ደሴት ነው ። በኢትዮጵያና ታንዛኒያ ወደ ከተሞች ለሥራ የሚመጣውን ገጠሬ መንግሥት እያፈሰ ይመልሳል ፥ ወይም ለሚሊሽያነት ይወስዳቸዋል ። በቦትስዋና ፥ በማላዊ ፥ ሌሶቶ ፥ ስዋዚላንድ ፥ ዚምባብዌና ሞዛምቢክ ሥራ አጦቻቸውን ወደ ደቡብ አፍሪካ ማዕድናት ይልኳቸዋል ።

እንደምንም ተፍጨርጭረው ራሳቸውን በገንዘብም ፥ በትምህርትም ትልቅ ደረጃ ያደረሱ ሰዎች ዛሬ በተራቸው ልጆቻቸውን በማስተማር ከእነሱ የተሻለ እድል እንዲኖራቸው ይሻሉ ። ነገር ግን የዛሬ ልጆች በግዴለሽነት ሲዘባነኑ ያናድዳቸዋል ። አባቶቻቸው ያዩትን መከራ አልቀመሱም ። ለመማር እንኳ ብዙ ጉትጎታና ግፊት ይፈልጋሉ ። ሕይወት በወርቅ ሳህን እንዲቀርብላቸው የሚጠብቁ ይመስላሉ በማለት የሚያማርሩ ብዙ ናቸው ። እነዚህ በመፍጨርጨር በትምህርትና በዕድል ራሳቸውን ከድህነት ያወጡ የመካከለኛው መደብ አባላት ጥሩ አመለካከት ስላላቸው ቢበራከቱ በአሜሪካ እንደሆነው አገራቸውን ወደተረጋጋ ፖለቲካና ትርጉም ወዳለው የኢኮኖሚ እድገት በማራመድ ረገድ ሊያግዙ የሚችሉ ናቸው ።

አፍሪካውያን የትምህርት ዕድልና የውጭውን ዓለም ለማየት ዕድል ቢያገኙ እንደ ማንኛውም አውሮፓዊ የተማሩ ፥ የነቁ ፥ አስተዋይ ፥ ብልህና የሰለጠኑ መሆን አይሳናቸውም ። የኢኮኖሚያዊ ማበረ



ታቻና የሥራ ግብ ቢቀየስላቸው ደከመኝ የማይሉ ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው ። ግን አብዛኛው የትምህርትም ሆነ የኢኮኖሚ ማበረታቻ አላገኙም ፤ ስለዚህም ግፋ ቢል በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በጦር ኃይሉ ውስጥ ተወስነው ቀርተዋል ። በዚህ ላይ ዛሬ የተማሩትም ባለሥልጣን ወገን ከሌላቸው ርቀው ሊሄዱ አይችሉም ። አፍሪካ ልጆቿን በአግባቡ አልተጠቀመችባቸውም ።

የወደፊቱ እድልስ እንዴት ነው? መልሱ የአፍሪካ ልጆች ነው ። ሕይወታቸው ፈተና የሞላበት ቢሆንም ከየትኛውም አህጉር ወጣቶች በበለጠ መከራ ቻይ ናቸው ። በተባበሩት መንግሥታት ዘገባ መሠረት ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ሕፃናት አርባ በመቶው የተመጣጠነ ምግብ አያገኙም ። ይህም የአዕምሮና የአካል ጉድለት ሊያስከትልባቸው የሚችል ነው ። በዓለም ባንክ ዘገባ ከእነዚህ የአፍሪካ ሕፃናት ሶስት በመቶው ሠርተው የሚያድሩ ናቸው ። ይህ በአውሮፓና በአሜሪካ የተለመደ አይደለም ። ከስምንት ሕፃናት አንድ በሕክምና ሊወገድ ይቻል በነበረ በሽታ ይቀሰፋል ። ከአፍሪካ ሕፃናት ሁለት ሚሊዮን ያህሉ በተባበሩት መንግሥታት ጥናት መሠረት ስደተኞች ናቸው ።

የአፍሪካ ሕፃናት አራትና አምስት ዓመት ሲሆናቸው በከብት እረኛነት ወይም ከእነሱ ያናነሱ ሕፃናትን በመንከባከብ ያገለግላሉ ። ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው ቅርበት ብዙ መጫወቻዎች አሏቸው ። አሻንጉሊት ግን ተገዝቶላቸው አያውቅም ። እንደተወለዱ ፥ ለዓመት ያህል የእናታቸውን ጡት እየጠቡ ከጀርባዋ ሳይወርዱ ከፍተኛ ፍቅርና እንክብካቤ ያገኛሉ ። ወዲያው ሌላ ልጅ ስለሚወለድባቸው ቸል ይባላሉ ። የአፍሪካ ወላጆች ትልቁ ምኞት ልጆቻቸው ተምረው ሥራ በመያዝ የኑሮ ዋስትና ማግኘታቸው ነው ። የእውቀትን ጥም ማርካት በራሱ ግብ አይደለም ፥ ዋናው ነገር ሥራ ማስገኘቱ ነው ፣

የአፍሪካ ሴቶች እጅግ ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው ። ከመላው ዓለም ሴቶች የበለጠ የሥራ ጫናና ኃላፊነት አለባቸው ። በመላው አፍሪካ ከሚመረተው ሰባ በመቶውን የሚያመርቱት ሴቶች ናቸው ። ይህም በተባበሩት መንግሥታት ዘገባ የተረጋገጠ ነው ። ለረጅም ሰዐት

ጠንክረው በመስራት ከባሎቻቸው የላቀ ተግባር ያከናውናሉ ። በጎጠሩ የቤተሰቡ ምሰሶ ፥ የገቢያቸው የጀርባ አጥንት ፥ የለውጥ ኃይልና በቤተሰብ ጉዳይ ወሳኝ ሚና ያላቸው የኅብረተሰቡ አንቀሳቃሾች ናቸው ። በኬንያ ገጠሮች ስትዘዋወር የምታየው ሴቶች ውሃ ተሸክመው ፥ ወገብ የሚያጎብጥ እንጨት ተሸክመው ፥ የመገበያያ ቦታዎችን ሞልተው ሲዋትቱ ነው ። በእርሻ ቦታዎች አካፋና ዶማ ፥ እንዲሁም ማጭድ ይዘው የምታገኛቸው ሴቶች ናቸው ።

“ከወንዶች ልጆቻችን ይልቅ በዛሬ ጊዜ ጠቃሚዎቻችን ሴቶቹ ናቸው ፤” በማለት በታንዛኒያ ያገኘሁዋት አንዲት የአሥራ ሶስት ልጆች እናት አወጋችኝ ። “ሴቶቻችን ሥራ አልረሱም ፤ ወንዶቹ ግን አይረቡም ። ከቤት ወጥተው ሲጠጡ ይውሉና ጨርቅ ሆነው ይመጣሉ ።”

የአፍሪካ ሴቶች አስጨናቂ ስሜት ተፈጥሮባቸዋል ። ለቤተሰባቸውና ለኅብረተሰቡ የሚያገለግሉት ከወንዶች የላቀ ቢሆንም ከሁለተኛ ዜጋነት ከፍ ሊሉ አልቻሉም ። ዛሬም አፍሪካ የወንድ የበላይነት የሚታይበት ነው ። ሴቶች የቱን ያህል ቢማሩ አብዛኛዎቹ ከፀሐፊነት ፥ ከነርስነትና ከመምህርነት ሊያልፉ አልቻሉም ።

በኬንያ ዩኒቨርስቲ የሴት ተማሪዎች ቁጥር አሥር በመቶ ብቻ ነው ። ከሠራተኛው ቁጥር ሴቶች አሥራ ስድስት በመቶ ሲሆኑ ፥ በማይማን ብዛት ግን ከወንዶች እጥፍ ናቸው ። በዓመት ከአራት መቶ ዶላር በላይ ከሚያገኙት ተቀጣሪዎች የሴቶች ቁጥር ስድስት በመቶ ብቻ ነው ። ሴቶች ገቢያቸውን ሁሉ ለቤተሰቡ ጥቅም ያውላሉ ፤ ወንዶች ግን በብዙው ይዝናኑበታል ። ሚስትን መደብደብም የተለመደ ነው ።

በድሮ ጊዜ በአፍሪካ የወንዱ ሚና በጦርነት መዋጋት ነበር ። አደን ፥ ጫካ መመንጠር ፥ ቤት መሥራት ፥ ሌሎች የወንዱ ተግባሮች ነበሩ ። የሴቶች ድርሻ ደግሞ እንጨት መስበር ፥ ውሃ መቅዳት ፥ እህል ማጨድና ልጆች ማሳደግ ነበር ። ትርፍ እህል ካለ መሸጥ የሴቷ መብት ስለነበር ሙሉ መብት ያላትና ለገጠሩ ልማት ወሳኝ ኃይል ነበረች ።



በአይቮሪ ኮስት የገበያውን ኢኮኖሚ የሚያካሂዱት ሴቶች ሲሆኑ ፤ በኬንያ ደግሞ የተሰካላቸው የገበሬዎች የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚካሄዱት በሴቶች ነው ። ነገር ግን አፍሪካ ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ ስታመራ የተወሳሰቡ ማህበራዊ ኃይሎች የወንድና የሴት ግንኙነቶችን በማዛባት የትምህርትና የገቢ ዕድልን ለወንዶች እንዲያመዝን አድርገዋል ።

ይህን ግንኙነት ለማዛባት የመጀመሪያው ሚሲዮኖች ሲሆኑ ተከታዮቹ ቅኝ ገዢዎች ናቸው ፡ ሚሲዮኖች የአፍሪካውያንን የግብረ ሥጋ ባህል ሞራልን ያልተከተለ ነው በማለት ፤ ቅኝ ገዢዎች ደግሞ ሴቶች ትምህርት አያስፈልጋቸውም በማለትና ትʻቤቶችን ለወንዶች ብቻ በማድረግ ነው ። ከዚያም ወንዶች የሚቆጣጠሩት ገንዘብ የሚያስገኝ የቡናና የካካዋ እርሻ በማቋቋም የሴቶችን የኢኮኖሚ የበላይነት አናጉት ። የወንዶቹ የአዳኝነትና የተዋጊነት ሚና ቀረና ወጣት ወንዶች ወደ ከተማ መጉረፍ ጀመሩ ። በነፃነት ጊዜም ዋና ተዋናይ ሆኑ ።

“ማኅበራዊ ለውጥ ፥ የኢንዱስትሪ መስፋፋትና ዘመናዊ ሥልጣኔ ሴቶችን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ዝቅ የሚያደርግበት ምክንያት አይገባኝም ፤ በአፍሪካ ግን ይህን እያየን ነው” ሲል ለኬንያ መንግሥት በአማካሪነት የሚያገለግለው አሜሪካዊ የማህበረሰብ ሊቅ አውድሪ አስምክ አጫወተኝ ። “የአፍሪካ ሴቶች በየጊዜው ወደኋላ በመቅረት ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት ምዕራባውያን ሴቶች ያጋጠማቸው ዓይነት ችግር ላይ ወድቀዋል ።

ኬንያ የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድ ሕጎች አውጥታለች ። በ1977 የሴቶች የወሊድ ፈቃድ ስድሳ ቀን እንዲሆን አዘዘች ። በተጨማሪም ሴቶች ሌሊት ለሥራ እንዳይመደቡ የሚለውን ሕግ ሰረዘች ። በ1975 ሶማሊያ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው የሚል ድንጋጌ አወጣች ። የሚያስገርመው ግን እስላም “ሁራን ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬን በመቃወም (ቁራንን ተቃውመዋል በሚል) አጥላሉ ። በዚህም ምክንያት ባሬ አሥሩን ምሁራን በመግደልና ሃያ ሶስቱን እስከ ሰላሣ ዓመት በሚደርስ እሥራት በመቅጣት ክርክሩን እልባት ሰጡት ። ውሣኔው ለሴቶች ለውጥ አላመጣም ፤ አንድ ያስገኘው ጥቅም ቢኖር ስለፆታ እኩልነት ጉዳይ የሚካሄደው ክርክር እንዲቆም ማድረጉ ብቻ ነው ።

## ምዕራፍ ሶስት

# የመሪዎች ድክመትና የሀገሮች ውድቀት

"ራሳችንን ለማስተዳደር ዕድሉ ቢሰጠን በፍጥነት ምድራዊ ገነት እንደምንፈጥር አስመስለን አወራን ፤ በተቃራኒው ያስፈነው ግን የፍትህ መጓደልና ብሎም ፈላጭ ቆራጭነት ነው"

ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ (ታንዛኒያ)

የቴሌቪዥኑ መስታወት በሰማይ ደመና ሥዕል ይሞላና ከበስተ ጀርባ የሕብረት መዝሙር ይሰማል ። የመዝሙሩ ድምጽ እየጐላ ሲመጣ ደመናው እየገለጠ በመሄድ ከአቦ ሸሜኔ ቆዳ የተሰራ ዝጉርጉር ቆብ ያደረገ መልከመልካም ጥቁር ሰው ሥዕል ብቅ ይላል ። ካሜራው ሥዕሉን ጠጋ በማድረግ የቴሌቪዥኑን መስታወት ይሞላውና ለብዙ ደቂቃ ይቆያል ። የፈገግታ ስሜት የሚታይበት ይህ ጉርድ ፎቶግራፍ ድምፅ ባይኖረውም ጥንካሬ ፣ ጥበብ ፣ፍቅር ፣ ይፈነጥቃል ። ተመልካቹም ሞትን ያቸነፈ መልአክ አድርጐ ይመለከተዋል ። የሚታየው ምሥል የሞቡቱ ሴሴሴኮ ነው ። የስማቸው ትርጉም " በጥንካሬውና በፍላጐቱ ድል እየመታና እየቀጠለ የሚሄድ ኃያል ጦረኛ " ማለት ነው ። የእሳቸው ምስል በቴሌቪዥን በዚያ መልኩ የሚቀርበው በኪንሻያሳ የሁለት ሰዐት ዜና ሊጀመር ሲል ነው ።

ሞቡቱ በ1965 የዛየር ፕሬዚዳንት ሆኑ ። ከቀውስ ወደ ቀውስ እየተሸጋገሩ የደም መፋሰስና አለመረጋጋት ታሪክ ያላትን ሁለት መቶ ጐሳዎች ያቀፈች ሀገራቸውን ሳትገነጣጠል ማቆየት ችለዋል ። እንደ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች እንደጣሉትም እንደ ጐሣ መሪም

እየተመሰከ ሲገዙ ኖረዋል ። የማይወቀሱ ፣ የማይገሰሱ የሀገሪቱ አርማና ፈላስፋ አድርገው ራሳቸውን በማወጅ ይመራሉ ። በሕዝባቸው ላይ ሲቃዪ ያስከትሉ ቢሆኑም ትዕዛዛቸው ሲደርሰው ሕዝቡ በአሥር ሺዎች በመውጣት ስታዲየሞችንና አደባባዮችን በማጥለቅለቅ እሳቸውን የሚያሞግሱ መዝሙሮችንና መፈክሮችን ያዥጎደጉዳል ። በአጭሩ ሞቡቱ ከፕሬዚዳንት በላይ ናቸው ። የግል ገናናነትን የገነቡ ፣ ሁሉን አድራጊ ፈጣሪ ናቸው ።



ሞቡቱ ሴሴሴኮ

ፍልስፍናቸው ሞቡቱኢዝም በራሳቸው ትዕዛዝ የአገሪቱ ብሔራዊ ፍልስፍና ሆኗል ። ፎቶግራፋቸው በሕዝብ መሰብሰቢያዎች ሁሉና በሆቴሎች አሳንሰሮች (ኤሊቬተርስ) ውስጥ ሳይቀር ተሰቅሏል ። ሕዝባቸው ምስላቸው ያለበትን ፒን በደረቱ ላይ ያደርጋል ። ምስላቸው ያለበትን ካናቴራና የሞቡቱ ዩኒፎርም እየተባለ የሚጠራውን የቻይናው ማኦሴቱንግ ዓይነት ልብስም ይለብሳል ። ሕዝቡ ስማቸውን በመዝሙር እያወደሰ ከንግግራቸው ይጠቅሳል ። አንዱ ዝነኛ ጥቅሳቸው "ሀብታም ሆኖ በቅኝ አገዛዝ ሥር ከመኖር በረሃብ መሞት ይሻላል" የሚል ነው ። ይህ ሁሉ ግን ሃያ ስድስት ሚሊዮን ሕዝባቸው ይወዷቸዋል ማለት አይደለም ።እንደታዘዙ መፈጸም ስላለባቸው ብቻ ነው ። አንድ ቀን ከሥልጣን ሲወርዱ ሐውልታቸውን ያፈርሳል ፣ ምስላቸውን ያቃጥላል ፣ ስማቸውን ይኰንናል ፣ ለተከታዩ መሪ ደግሞ ታማኝነቱን ይገልጻል ።

ሞቡቱ አባካኝ መሪ ናቸው ። የሚሰነዘርላቸው አክብሮት በቃል እንጂ ከልብና በተግባር አይደለም ። የእሳቸው ዓይነት የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች የአፍሪካና የአውሮፓ ወግና ባህል የተደባለቀባቸው ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ ናቸው ። በውጭ ሀገር የባንክ ሂሳብ ደብተራቸው በቢሊዮኖች ጣራ የነካ ፣ ታማኝነታቸውና ጭንቀታቸው ሁሉ ለግላቸው ብቻ የሆነ ፣ ለሀገር እድገት ቅንጣት የማይጨነቁ ናቸው ።



ሞቡቱ የምዕራብ ካፒታሊዝም የፈጠራቸው ናቸው ። የሀገራቸው ሕመም ምልክት ናቸው ። ነፃነት እንደተገኘ ከአውሮፓ የተወረሰው የአሠራር ሥርዓት ፈረሰ ፤ በቦታው የተተካው የአፍሪካ አሠራር ዘይቤም ተንኮታኰተ ። እንደ ሞቡቱ ያሉ መሪዎች አገራቸውን የአሠራር ዘዴዎች መሞከሪያ አደረጓት ። በተጨባጭም የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች ሆኑ ፣ የአኗኗር ዘይቤአቸውም ፣ አሠራራቸውም እንደቀድሞዎቹ ነጮች ጌቶቻቸው ሆኖ አረፈ ። የአፍሪካውያኑ ሕዝቦቻቸው ደህንነት ጉዳይም ብዙ አያስጨንቃቸውም ፤ ለሚታቸው ልክ እንደ ቅኝ ገዢዎች ነው ።

ሞቡቱ ሥልጣን ሲይዙ ዛየር( የቀድሞ ቤልጅየም ኮንጎ) በእድገት ላይ የነበረች ሀገር ናት ። የመዳብ ማዕድኖችዋ ፣ የእርሻ ማሳዎችዋ ሁሉ ለልማት የተዘጋጁ ነበሩ ። በ1970 መዳብ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ዋጋ ስለነበረው ፣ የቀድሞው ሃምሳ አለቃ ሞቡቱ በትልቅ ሀብት ላይ ተደላድለው የተቀመጡ ሆነው አገኙት ። ስለዚህም ካለመጠን ገንዘብ ማባከን ጀመሩ ። በዚህም ኢኮኖሚስቶች አንጐላቸው ዞረ ። ቅድሚያ የሰጡት ለብሔራዊ ልማት ሳይሆን ለግል ዝናና ለብሔራዊ ጉራ ነበር ።

ሞቡቱ አሥራ አንድ ቤተመንግሥቶችን በመገንባት አንዳንዶቹ ከከተማው ጋር በሰፋፊ መንገዶች እንዲገናኙ አደረጉ ። የራሳቸውን ሐውልቶች አሳነፁ ፣ ሕዝብ ሰብስበው የሚያነጋግሩባቸው እስታዲየሞች አስገነቡ ። አሜሪካን በመጐብኘት በዚያ የተመለከቱትን የዓለም የንግድ ማዕከል ሕንፃ በኪንሻሳ እንዲገነባ አደረጉ ። ጠላቶቻቸውን በገንዘብ በማባበል ፣ ወዳጆቻቸውን በተለይ ከራሳቸው ባንዶ ጐሣ የሆኑትን በቅጽበት የናጠጡ ከበርቴዎች አደረጓቸው ። የሚያማምሩ የጥንት ዛፎች የነበሩበትን የኪንሻሳ ከተማ ዋና አውራ ጐዳና ለማስፋትና ለጦር መጓሪያ ሠልፍ እንዲያመች ለማድረግ ብለው ዛፎችን በሙሉ አስቆረጧቸው ። በ1974 የዓለም የቦክስ ሻምፒዮና የነበረውን የመሐመድ አሊና የጆርጅ ፎርማንን ውድድር በአገራቸው በማዘጋጀት አሥራ አምስት ሚሊዮን ዶላር አጠፉ ። ከአሥር ዓመት በፊት ምንም የሌላቸው ሃምሳ አለቃ የነበሩት ሞቡቱ ዛሬ

በትንሹ ሶስት ቢሊዮን ዶላር በውጭ ባንኮች እንዳካበቱ ይነገራል ።
በአገራቸው የወደፊት ዕድል እምነት ስለሌላቸው ባካበቱት ገንዘብ
ዛየር ውስጥ ልማት ለማቋቋም አይፈልጉም ። እንደሌሎቹ የአፍሪካ
ፕሬዚዳንቶች ሁሉ የእሳቸው የወደፊት እድል በአውሮፓ ያካበቱት
ሀብትና በአውሮፓ ያቋቋሟቸው የንግድ ተቋሞች ናቸው ።

ዛየር ከውጭ ከምታገኘው የርዳታ ገንዘብ ወይም ብድር ወይም
የልማት ኮንትራት ገንዘብ ውስጥ ባለሥልጣኖቹ ሃያ በመቶውን ሹራሳ
ቸው ይከፋፈሉታል ። በ1977 ዛየር ከቡና ሽያጭ 400000000
ዶላር አገኘች ። ነገር ግን ሁሉም ባለሥልጣን ተቦጫጭቆት በውጭ
ሀገር ባለው የባንክ ሂሣቡ ስላስገባው ወደ ሀገሪቱ ካዝና የገባው 120
000000 ዶላር ብቻ ነው ። በዛየር ከበርቴ ሆነህ ለመኖር የሚያስፈ
ልገው ወሳኝ ባለሥልጣን ማወቅና በጥቅም መተሳሰር (ጉቦ መስጠት)
ነው ።

ሞቡቱ አገር ወዳድና ባህላቸውን አክባሪ ለመምሰል ሁሉም
አፍሪካዊ ስሙን ወደ አፍሪካዊ ስሞች እንዲቀይር በማዘዝ በቅድሚ
ያም የራሳቸውን ስም ማለትም (ጆሴፍ ዲዛየር) የሚለውን በመቀየር
ሴሴሴኮ የሚለውን መረጡ ። የሀገሪቱን ስም ኮንጐ ከሚለው ዛየር
ወደሚለው ለወጡ ። ዛየር ማለት ወንዝ ማለት ነው ። የምዕራባውያን
ዓይነት አለባበስ እንዲከለከልና የማኦ ሴቱንግ ዓይነት ዩኒፎርም
እንዲለበስ አዘዙ ። የገና በዐል አከባበርን ሰርዘው በየቤተክርስቲያኑ
የራሳቸው ፎቶ እንዲሰቀል አደረጉ ።

የውጭ ባለሀብቶችን ተቋሞች በመውረስ በዛየር ውስጥ በንግድና
ልማት ተሰማርተው የነበሩ የእስያ ነጋዴዎችን ከአገር አስወጡ ።
ብዙዎቹ የቤልጅግ የእርሻ ልማት ባለንብረት የነበሩትና ነጋዴዎችና
ቴክኒሽያኖች ሳይቀር ተባረሩ ። ተቋሞቻቸውን የተረከቡት አዲሶቹ
ሥራ መሪዎች ስላላወቁበት ብዙዎቹ ጨርሰው ተዘጉ ።

የዛየር ሕዝብ ስለሞቡቱ ትክክል ያልሆነ አሠራር ይንሾካሾ
ካል ፣ ግን አገሪቱን ያጥለቀለቀውን የጆሮ ጠቢዎች መንጋ በመፍራት
በግልጽ የሚናገር የለም ። በአሜሪካ ምክር ቤት ስለሁለቱ አገሮች



ሽርክናና ስለዛየር አስተዳደር መበላሸት ተደጋግሞ ተወስቷል ። ነገር ግን
ሞቡቱ ምንም ያጥፉ ፣ ሕዝባቸውንና አገራቸውንም ቢበድሉ ፀረ-
ኮምኒስት ጠንካራ አቋም እስካላቸውና በማዕከላዊ አፍሪካና በአንጐላ
በኩል የሚታየውን የሶቪየቶች የተጽእኖ ክልልና ርዕዮተዓለም የማስ
ፋፋት ፖሊሲ ለመግታት እስከጠቀሙ ድረስ ግዴለም ። በዚህም
ምክንያት በ1970 የካርተር አስተዳደር ለጥቁር አፍሪካ ከመደበው
ዓመታዊ ርዳታ ግማሹ ለዛየር ተሰጠ ። አሜሪካ ይህን በማድረግ አገ
ሪቱ እንድትለማ አልረዳችም ፣ ይልቁንም አውሮፓ በቅኝ ግዛት ዘመን
ታደርግ እንደነበረው የመሪውን ታማኝነት በገንዘብ ለመያዝ የተደረገ
ነው ። የፈጠረው ሁኔታም ለአብዮትና ለሶቪዬት ተጽዕኖ መስፋፋት
የሚገፋፋ ነበር ።

በሞቡቱ አርቆ አለመመልከት ምክንያት ዛየር ብዙ ኪሣራ ላይ
ወድቃለች ። የመዳብ ዋጋ አዘቀጠ ወረደና በ1980ዎቹ ዋጋ አጣ ። ዛየ
ርም ኢኮኖሚዋ ተሽመደመደ ፣ ማህበራዊ ቀውስም ተከተለ ፣ ሞቡቱም
የማይቀረው ሀፍረት ላይ ወደቁ ። ጭራሽ አገሪቱን የመምራቱን ጉዳይ
ለውጭ ዜጎች ሰጡ ። በ1970 ንብረታቸውን ወርሰው ያባረሯቸውን
ቤልጅጎች ጠሩ ። የግል ደህንነታቸውን የሚጠብቁ የክብር ዘቦችና
አጃቢዎች ከሞሮኮ ቀጥረው አመጡ ። ብሔራዊ ባንኩን የዓለም የገ
ንዘብ ድርጅት እንዲያስተዳድረው አደረጉ ። የጉምሩክ ዘርፍንም የቤ
ልጅግ ዜጎች እንዲያካሂዱት ወሰኑ ። ሌሎች አውሮፓውያን የገንዘብ
ሚኒስቴሩን ፣ የገቢ ታክስ ቢሮዎችና የትራንስፖርት ሥርዓቱን እንዲ
ያካሂዱ ተደረገ ። ይህም አዲስ ሙከራ ከኢኮኖሚ ውድቀት ለመዳን
የተቀየሰ የሞቡቱ ፕላን ተባለ ። ስሙ ተገቢ ነበር ፣ ምክንያቱም ዕቅዱ
ሞቡቱን ለማዳን እንጂ ዛየርን ለማዳን አልነበረምና ።

የሞቡቱ ፕላን አልሠራም ፣ በመጨረሻ ሂጂ እንደተመለከትኩት
ሀገሪቱ በፍጥነት እየተንኮታኮተች ነው ። በሞቡቱ እናት ስም በሚጠ
ራው ማማ ጆሞ ሆስፒታል እንክብካቤ ያጡ ብዙ በሽተኞች እየሞቱ
ነበር ። በሆስፒታሉ የቁስል ማሰሪያ ፣ ማደንዘዣ ፣ ኦክሲጂንና ሌሎች
መሣሪያዎች የራጅ መነሻ ፊልሞች ሳይቀር ስለጠፉ በሽተኛን ማዳን
አልተቻለም ነበር ። የአስከሬኑ ቤት እየሞላ የሞቱትን አስከሬን ወደ

ራሱ ቤት የሚወስዱት ከብዙ ሰዐት በኋላ ቦታ ሲገኝ ነበር ። ዩኒቨርሲቲ የነበሩት ክሊኒኮች መድኃኒታቸው በድብቅ እየተወሰደ እየተሸጠ (በጥቁር ገበያ) አገልግሎታቸውን አቋርጠው ተዘጉ ። ምግብ በመጥፋቱ የዩኒቨርሲቲው ምግብ አዳራሾች ሥራ አቆሙ ። የገንዘቡ የመግዛት አቅም መቶ በመቶ ስለቀነሰና የዋጋ ንረት ስለተባባሰ አንድ ስልቻ በሎቆ ወደ ሰላሳ ዶላር አሻቀበ ። ይህም የአንድ ወዝአደር የሁለት ወር ደመወዝ ነው ። የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ስለተሰነካከለና የገበሬዎችን ምርት ለገበያ ማድረስ ባለመቻሉ እህሉ እየበሰበሰ ገበሬው ለራሱ የሚበቃ የምግብ እህል ብቻ ማምረት ጀመረ ። ዛየር ነፃ ስትወጣ 31.000 ማይልስ ርዝመት ያላቸው ዋና ዋና መንገዶች ነበሯት ። ከሃያ ዓመት በኋላ ግን3.700 ማይልስ ርዝማኔ ያላቸው መንገዶች ብቻ ነበሩ መኪና ሊያስኬዱ የሚችሉት ።

በ1981 የዛየር የውጭ ዕዳ ሜና አራት ቢሊዮን ደረሰ ፣ የምግብና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ ። የመንግሥቱ የዜና አገልግሎት በወረቀት እጥረት ተዘጋ ። ነዳጅ ያጡ 350 አውቶቡሶች ያለሥራ አውሮፕላን ማቢያው አቅራቢያ ተደርድረው መዛግ ጀመሩ ። የዛየር አየርመንገድ የነበረው ነዳጅ ከአራት የአገር ውስጥ በረራዎች አንዱን ብቻ ለመሸፈን የሚያስችል ነበር ። የአገሪቱ ቦይንግ 747 እና ዲሲ 10 የተሰኙ አውሮፕላኖች እዳቸው ሊከፈል ስላልቻለ ኩባንያዎቹ መልሰው ወሰዷቸው ። በዚሁ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሞቡቱ ዛየርና ሕዝቧ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳሉ አስመስለው ይደሰኩሩ ነበር ። የምዕራብ ጋዜጠኞች የሚፅፉት የድክመት ወሬ በሌለ ችግር ላይ የተሰነዘረና በአፍሪካ ላይ ባላቸው የንቀት አመለካከት የተመሠረተ ነው ሲሉ መክሰስ ጀመሩ ።

ፕሬዚዳንቶች ያለእስተዋፅኦ የግላቸውን ገናና ስም መገንባት (ከልቲዝም) ለአፍሪካ አዲስ አይደለም ። በአሜሪካም ጆን ፣ ኤፍ ፣ ኬኔዲ ስማቸው እንዲሁ ገኖ ነበር ፣ ይበልጡንም ከተገደሉ ወዲያ ። የአፍሪካ መሪዎች ግን ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ገናናነትን መገንባት በመማር መለኮታዊና የማይከሰሱ የማይገሰሱ ሆነው መታየት ጀምረ



ዋል ። እንደ እውነቱ ከሆነ አፍሪካዊነት ባለው ለሕዝብ አሞካሽቶ የማቅረብ ዘመቻ ፣ ከመሪነት በላይ ልዩ ፍጡርና የሀገሪቱ ተምሳሌት ሆነው ተስለዋል ። ለሠለጠነው ዓለም ግራ የሚያጋባ ቢሆንም በአፍሪካ ሁኔታው የተለመደና ያልተማሩት ብዙሃን ለጠንካራ ማዕከላዊ ሥልጣን አሜን ብለው መገዛትን ተገቢ አድርገው ወስደውታል ። መንግሥቶቻቸው እንዲዘባነኑባቸው አይሹም ፣ ግን ልክ እንደ ጉማሬና እንደ ቅኝ ገዢዎች ፈላጭ ቆራጭ የመሆናቸውን ጉዳይ የተቀበሉት ይመስላል ። ከዚህ ለስለስ ካሉ የደካማነት ምልክት ይሆናል ።

ሞቡቱ ምናልባት አብዝተውት እንደሆነ ነው እንጅ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች በተለያየ ደረጃ በስማቸው ዙሪያ ገናናነትን የመገንባትና ይህንንም በተምሳሌት የሚያንፀባርቅ የቅጽል ስም ማበጀት የተለመደ ሆኖአል ። ሞቡቱና የቶጎው መሪ ኢቴኔ ኢያደማ ሁለቱም “መርሐ ብሔር” በሚለው ስም እንዲጠቀሱ ይመርጣሉ ። ሟቹ የኬንያ ፕሬዚዳንት ጆሞ ፣ ኬንያታ “ሙዜ” በሚል ቅጽል ስም ይታወቁ ነበር ። በስዋሂሊ ቋንቋ ትርጉሙ “ብልሁ አዛውንት” ማለት ነው ። የታንዛኒያው ጁሊየስ ኔሬሬ “መምህር” በመባል ሲቆለጳጰሱ ፣ የማላዊው ካሙዙ ባንዳ ደግሞ “የመሪዎች መሪ” በመባል ይጠሩ ነበር። የአይቮሪ ኮስቱ ፌሊክስ ሁፌት ቧኚ የገበሬ ቁንጮ እየተባሉ ሲሞካሹ ፣ የኢኩዌቶሪያል ጊኒው ማሲያስ ቢዮጎ ደግሞ “ብሔራዊ ታምር” ተብለው ይጠቀሱ ነበር ። የኡጋንዳው ኢዲ ፣ አሚን ዳዳ ራሳቸውን “የእንግሊዝን ቅኝ ግዛት ድል የመቱ” ብለው ይጠሩ ነበር ።

የቶጐው ኢያደማ በየስብሰባው የሚያሞካሹዋቸው አንድ ሺህ ሴቶች የተሰባሰቡበት በዘፈንና መዝሙር የሠለጠነ የሙገሳ ዘርፍ ነበራቸው ። ያለእነዚህ በአደባባይ ቀርበው ንግግር አያደርጉም ። የሴቶቹ ተግባር ባህላዊ ጨዋታዎች ማሳየትና መሪውን የሚያሞካሹ መዝሙሮች ማዜም ሲሆን ፣ መሪውም ይህ እንዲህ መሆኑ ብሔራዊ ስሜትንና ማንነትን ያዳብራል ብለው ያምናሉ ። የቶጐ ሕዝብ በሃያ ዶላር እንዲገዛ የቀረበለት ሰዐት በየአሥራ አምስት ሴኮንድ የመሪው ፎቶግራፍ ብልጭ ድርግም የሚል ምስል ያለበት ነው ። በሎሜ የራሳ

ቸውን ከመዳብ የተሠራ ሐውልት አስተክለዋል ። የማይሸነፉ ጀግና
አድርጐ የሚያቀርባቸው የኩምክና መጽሐፍ አሳትመዋል ።

በማላዊ ከዩኒቨርሲቲው ስም ጀምሮ እስከ እያንዳንዱ መንገድ
ባንዳ በሚል የተሰየመ ነው ። ሴቶችም የመሪው ምስል ያለበትን
ቀሚስ ይለብሳሉ ። ትንሽ ነቀፌታ የሰነዘረ ሰው ወደ ወህኒ መወርወር
ሲያንሰው ነው ። የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት የሆኑት ባንዳ "ሁሉ ሰው
ይወድሃል ይሉኛል ፤ አይሆንም ማለት የዋህነት ይሆንብኛል" በማለት
ይኩራራሉ ።

በየዕለቱ የየሀገሮቹ የዜና ማሠራጫዎች በአፍሪካ ሬዲዮና ቴሌ
ቪዥኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ዜና ከፍተኛ ብሔራዊ ጉዳይ
የሆነውን ሳይሆን በዕለቱ ፕሬዚዳንቱ የተናገሩትን ወይም የሰሩትን
ነው ። የተለመደና የሰለች (የደስታ መግለጫ ላኩ) ዓይነት ቢሆንም
እንኳን የእሳቸው ስም ሳይጠቀስ ወደሌላ ዜና አይሄድም ። ጆሞ
ኬንያታ ሊሞቱ አቅራቢያ ሳይቀር የኬንያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በየ
ቀኑ ስለእሳቸው ሳያወሩ ሌላ ዜና አያስከትሉም ። መራመድ ተስኗ
ቸው በቤተመንግሥታቸው ውስጥ እያጣጣሩ "በጠረፍ አውራጃዎች
የሥራ ጉብኝት ሲያደርጉ ዋሉ" እየተባለ ይነገርላቸው ነበር ። ሁለቱ
ዕለታዊ ጋዜጠችም ፎቶግራፎቻቸውን ከቅድሞ ፋይሎች እየፈለጉ
አንደኛ ገጽ በማተም ፕሬዚዳንቱ "ሥራ በዝቶባቸው" መዋላቸውን
እንዲገልጡ ይደረግ ነበር ። ሕዝቡ ልዩነቱን አያውቅም በሚል ነበር ።
ግን ሕዝቡ በእርግጥ ያውቅ ነበር ፤ ምክንያቱም አንድ ቀን ዜናው ከመ
ቅረቡ በፊት በሬዲዮ የሃዘን ማርሽ ሲዜም ሁሉም ሰው ኬንያታ መሞ
ታቸውን ገመተ ። በነሐሴ 1978 ኬንያታ የመጨረሻውን "የሥራ ጉብ
ኝት" ለማድረግ ሄደዋል ።

የኬንያታ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ሞይ የኬንያታን ፎቶ
ግራፎች ከየተሰቀሉበት አስወርደው የራሳቸውን ለመተካት የቆዩት
አርባቸው እስኪወጣ ድረስ ብቻ ነው ። ወዲያው የአራፍ ሞይ ንግግር
የጋዜጦች መክፈቻ መሆን ጀመረ ። ሰፊው ሕዝብም እንደበፊቱ አዲሱ
ፕሬዚዳንት ከቤተመንግሥት ብቅ ሲሉ እየተሰበሰበ እንዲያጨበጭ




ብላቸው ተደረገ ። የመጀመሪያውን ፕሬዚዳንት ገናናነት የማስተጋባት
ተግባር ተፈጽሞ ሁለተኛውን የማጋነን ዘይቤ ተጀመረ ። የኬንያታ
እንኳን ይሁን እንበል ፤ ከቅኝ ገዢዎች የተዋጉ የመጀመሪያው መሪና
የሚስብ አንደበት ስለነበራቸው ፤ በተመሳሳይ የመቀበሉ ጉዳይስ?
(ኬንያታ በአፍሪካ ታሪካዊ መሪ መባል ይገባቸዋል ።)

አራፍ ፤ ሞይ ወዲያው ኬንያን ወደ አንድ ፓርቲ አመራር በማ
ሸጋገር የተቃወሙአቸውንና ጋዜጠኞችን ሳይቀር ማሰር ጀመሩ ።
በዓለም ኤኮኖሚ መቃወስ ምክንያት የኬንያ ኤኮኖሚ እያቆለቆለ
ሲሄድ የቀድሞው አስተማሪ ሞይ እና የገዢው መደብ አባላት በተለ
ያዩ የንግድ ስምምነቶች እየከበሩ ሄዱ ። በ1982 ነሐሴ ወር ላይ የፈ
ሩት ደረሰ ። የአየር ኃይል መኮንኖች ሬዲዮ ጣቢያውን ያዙና መን
ሥት ገልብጠናል ሲሉ አስታወቁ ። ለአራፍ ሞይ ታማኝ የሆኑ ወታ
ደሮች ሙከራውን እስኪያከሽፉ ድረስ አንድ መቶ ሃያ ሰዎች ሞቱ ።
የኬንያ ጦር ሠራዊትም በናይሮቢ ከተማ በመተኮስ ፤ በመዝረፍና
ሴቶችን በመድፈር ሥርዓት አልባ ድርጊት ፈጸመ ። መፈንቅለ መን
ግሥቱ በተሞከረበት ሰሞን በኬንያ የሚታየው ማህመራዊ ችግር ፤
የባለሥልጣኖች ይፋ ምዝበራ ፤ በከተማ የሚፈጸመው ወንጀል ፤ (የቱ
ሪስቶች መገደል ጭምር) የኤኮኖሚ ማዝቀጥና የመንግሥት ነቀፌታን
ያለመቀበል ተባብሰው ነበር ። በዚያ ወቅት ሞይ የንቅናቄውን ምንጭ
ለመመርመርና አመራራቸውን ለማስተካከል ዕድል ሰጥቷቸው ነበር ።
ነገር ግን በተቃራኒው እንዴት ተደፈርሁ በሚል የበቀል ርምጃ ወሰዱ።
የአየር ኃይል ሠራዊቱን በሙሉ በማባረር ዩኒቨርሲቲውንም ለዘጠኝ
ወራት ዘጉት ። ኬንያን የአንድ ፓርቲ ብቻ አመራር ይዛ እንድትቀ
ጥል በማድረግና አንድ ዕለታዊ ጋዜጣ በመግዛት የፓርቲው ልሣን
አደረጉት ። ነባር ጋዜጠኞችንና ሂስ ሰንዛሪዎችን በማሰር በካቢኔው
ውስጥ "ከሃዲ" ብለው የሚገምቷቸውን በምሥጢር ማሰለልና ማደን
ጀመሩ ። በአፍሪካ የተለመደ አሳዛኝ አሠራር ነው ፤ የሚያስገኘውም ጦፍ
ትሄ የለም ። ነቀርሳው መሰራጨት ጀምሯል ፤ ሞይ የሚፍጨረጨሩት
የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ብቻ ነው ።

እንደ ፕሬዚዳንት ሞይ ሁሉ ዲፕሎማቶች በአውሮፕላን ጣቢያ

እንዲሰለሉ ሳያስጠሩና ሕዝቡ ከቤተመንግሥት እስከ አየር ማረፊያ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተደርድሮ እንዲያጨበጭብ ሳያዝዙ ለሥራ ጉብኝት የሚሄዱ መሪዎች በጣም ጥቂት ናቸው ። በዚህ መልኩ በሺ የሚቆጠሩ አፍሪካውያን በፀሐይ እየተንቃቁ ራሳቸው ሊያገኙ የማይችሉትን መፈክር ይዘው ታዛዥነታቸውን ፣ አክብሮትና ፍቅራቸውን እንዲሰጡት የሚያስገድዳቸውን ግለሰብ ለማሞገስ ሥራ ፈትው ለሰዓቶች ሲጉላሉ ማየት ሁልጊዜም ያሳዝነኝ ነበር ። የአንድ ሀገር ዜጎች መሆናቸው የሚገለፅበት ሌላ ብዙ የጋራ እንቅስቃሴ የሌላቸው ቢሆንም ፣ የዚህ መሰሉ ሰልፍ ዓይነተኛ ዓላማ ግን በራሳቸው እምነት ያጡና ተቀባይነትን የሚሹ ባለሥልጣኖችን ሞራል ለመስጠት ነበር ።



አሪፍ ሞይ

እስቲ አሁን ደግሞ ወደ አፍሪካ እምብርት ወደ ባንጉዊ ወንዝ ዳርቻ እንዝለቅና አንድ ሰው ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉትን እንመልከት ። ጃን ፣ ቤዴል ፣ ቦካሳ ለውጭ ሰው ሁሉ ነገር የተትረፈረፈለት ይመስላሉ ። ሀብት ፣ ሥልጣን ፣ ጌጣጌጥ ፣ ዘጠኝ ሚስቶችና ሠላሳ ሕጋዊ ልጆች ያሏቸው ሰው ነበሩ ።

በ1960 የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ነፃነቷን ከተቀዳጀች ጀምሮ ቦካሳ ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ የራሳቸውን ሐውልቶችና ቤተመንግሥቶች በመገንባትና የዕድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ነኝ በማለት ሥልጣን ሲያግበሰብሱ ኖሩ ። በውጭ ሀገር ታላቅ አክብሮት ተሰጣቸው ፣ ቻይናን ለመጎብኘት ሲሄዱ ሮማንያዊ ሚስታቸውን አስከትለው ነበር የተጓዙት ። ማንነታቸውን እንደዘለጉ ቢገመትም ጋዜጠኞች ከንግግራቸው ይጠቅሳሉ ፣ ሕዝቡም አክብሮቱን ይገልጥላቸዋል ።

እኒህ የሃምሳ አለቃ የነበሩ ሰው በራሳቸው መተማመን ስለተሳናቸው ተቀባይነትና አክብሮት ያጡ መሰሉ ታያቸው ። አረመኔያዊ



ጭካኔ ማሳየት ጀመሩ ። የሀገራቸውን ችግሮች ማጤን አቅቷቸው ራሳቸውን እንደ ናፖሊዮን ቦናፓርት ማድረግ አማራቸው ። ናፖሊዮን በ1804 በለየሴት አብሬት በፓሪስ ከተማ ኖተርዳም ካቴድራል ዘውዱን ከጳጳሱ በመንጠቅ ራሳቸው ላይ ደፍተው ንጉሠ ነገሥት ነኝ በማለት ማወጃቸውን አስታወሱ ።

ቦካሳም ይህን የናፖሊዮን ታሪክ በማንበብ እኔስ ለምን አላደርገውም አሉ ። ሁሉን ባስገረመና ሁለት ሚሊዮን ሕዝባቸውን ባስደነቀ ሁኔታ አገራቸው በንጉሥ የምትመራ እሳቸውም ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ቦካሳ መሆናቸውን አወጁ ። ቦካሳ ጳጳሱን ከፈረንሣይ ጋብዘው በጀ ባይሏቸውም ፣ የውጭ ጋዜጠኞችንና ፊልም ቀራፂዎችን ጋብዘውና የንግሥ ልብሳቸውን (ሁለት ሚሊዮን እንቁ ፈርጦች ያሉበትን) በ145,000 ዶላር አሠርተው አዘጋጁ ። በንግሥ በዓላቸው ላይ የሚገኙ ልዑላንና መስፍኖችን ዝርዝር አወጡ ። ከቤልጂግ ጋሪውን እየጎተቱ ወደ ካቴድራሉ የሚወስዱ ነጫጭ ፈረሶች አስመጡ ። አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ካራት አልማዝ እናቱ ላይ ያለበት የወርቅ ዘውድ በ2,000,000 ዶላር አሠሩ ።

ይህ ሁሉ ወጭ በሚደረግበት አገራቸው አስፋልት የለበሰ መንገድ አንድ መቶ ሰባ ማይልስ ብቻ ነው ። የዜጎቻቸው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 250 ዶላር ነው ። ለማንኛውም ለንጉሡ ያስፈለገው ዝግጅት ጠቅላላ ወጭ 20,000,000 ዶላር ደረሰ ። የፈረንሣዩ ፕሬዚዳንት በቀድሞዋ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ላይ አገራቸው ያላትን ቁጥጥር ለመቀጠል በመፈለግ ሂደቱን በፀጥታ በማለፍ ላልተከፈለው ዕዳ ፈረንሣይ ታሚላለች አሉ ። አንድ ጊዜ ራሳቸው ቦካሳ እንደተናገሩት ፣ "ሁሉ ነገር በፈረንሣይ መንግሥት የተዘጋጀ ነው ፣ ፈረንሣይን ገንዘብ እንጠይቃለን ፣ ሲሰጠን እናጠፋዋለን" ብለዋል ።

በ1977 ታህሣሥ 4 ቀን በባንጉዊ አቧራማ የሩብ ሚሊዮን ሕዝብ መኖሪያ ከተማ ጥሪ የተደረገላቸው የየሀገሩ ባለሥልጣኖች ተሰብስበዋል ። በንግሥ በዓላቸው ላይ ለመገኘት የመጣ መሪ ግን የለም ። ሙቀቱ ኃይለኛ ስለሆነ እንግዶቹ በላብ እየበሰጡ ቦካሳ ናፖሊዮናዊ ክብር ሲቀዳጁ ለመመልከት ይጠባበቃሉ ። በመጨረሻ በድምፅ ማጉ

ያዎች የሚያንባርቅ ድምፅ "ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ቦካሳ" በማለት በፈረንሣይ ቋንቋ አስተጋባ ።

ቦካሳ ወደ ስታዲየሙ ታጅበው ገቡ ። የስታዲየሙ ስም ቦካሳ ስታዲየም ሲሆን ፣ በዙሪያው ቦካሳ ዩኒቨርሲቲ ፣ ቦካሳ ጐዳና ፣ የቦካሳ ሐውልት ይገኛሉ ። ወርቃማ ጨርቅ አናታቸው ላይ አድርገው አሞራ የሚመስል ቅርጽ ባለው የወርቅ ዙፋን ጉብ አሉ ። ወዲያው ልክ ናፖሊዮን እንዳደረገው ዘውዱን ራሳቸው ጫኑና ከአሥር ዓመት በፊት ያገዱትን ሕገመንግሥት ለማስከበር ቃለ መሀላ ፈጸሙ ። የሁለት ዓመት ልጃቸው ጆን ፣ ቤዴል ፣ ጆርጅ ነጭ የወታደር ዩኒፎርም ለብሶ ከጐናቸው እንደተቀመጠ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1974 ከሥልጣን ተወግደውና በኋላም ተገድለው ወደ አልታወቀ መቃብር ከወረዱ ወዲህ አፍሪካ ሌላ አንድ ንጉሠ ነገሥት አገኘች ። ስለሁኔታው አንድ የሴኔጋል ጋዜጣ "አፍሪካ ኖቬል" በርዕስ አንቀፁ እንዳሰፈረው "ክስተቱን ጠጋ ብሎ መመርመር ይገባል ፣ ምክንያቱም አፍሪካ ገና ማንነቷን ለማወቅ በመባዘን ላይ መሆኗን በሚያሳዝን ሁኔታ ያረጋግጣል" በማለት አስተያየቱን ሰንዝሯል ። ፣

በተጨማሪም በአፍሪካ ያለውን አመራር ጥልቀት ማጣትና ባዶነት ፣ ብሎም ሕዝቡ በፍርሃት የማይረቡት መሪዎችን ሁሉ በዝምታ መታዘዝ እንደተገደደ ያመለክታል ። ብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በውስጣቸው ሌላ ሌላ ሊሉ ቢችሉም የቦካሳን በዐለ ንግሥ የተቹ ግን የሉም ። አንዳንዶቹ እንዲያውም እንደእሳቸው ለማድረግ ሳይመኙ አይቀሩም ፣ የውጭውን ትችት ባይፈሩም ያደርጉት ነበር ። በመሠረቱ ብዙዎቹ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ባይነግሱም ከስሙ በስተቀር ከነገሥታቱ ያላነሰ ፈላጭ ቆራጭ ናቸው ። ቦካሳ የሚነቀፉት በይፋ ስላደረጉት ብቻ ነው ። ቦካሳ ውሎ አድሮ ስለአፍሪካ መሪዎች ለጋዜጠኛ በሰጡት አስተያየት "ቀንተውብኛል ፤ ምክንያቱም እኔ የንጉሠ ነገሥት ግዛት ነበረኝ ፣ እነሱ ግን አልነበራቸውም" ብለዋል ።

ጆን ፣ ቤዴል ቦካሳ በ1921 ተወለዱ ። የአንድ የጎሳ መሪ አሥራ ሁለተኛ ልጅ ሲሆኑ ፣ አባታቸው በ1927 ተገደሉ ። ወዲ



ያው ብዙ ሳይቆዩ እናታቸው በብስጭት ራሳቸውን ገደሉ ። ቦካሳ ሊረሱት ያልቻሉት አሰቃቂ አጋጣሚ ነበር ።



ጆን ቤዴል ቦካሳ

ቦካሳ አጭር ናቸው ። ሚሲዮን ት/ቤት ተማሩ ። በ1939 ለፈረንሣይ ጦር ሠራዊት ተመልምለው በሁለተኛው የዓለም ጦርት ተዋግተዋል ። አገራቸው ነፃ ስትወጣ የጦሩ ኤታማዦር ሹም ሆኑ ። አጐታቸው ቦጋንጋ የፕሬዚዳንትነቱን ሥልጣን ያዙ ። ከአምስት ዓመት በኋላ ፕሬዚዳንቱ በአውሮፕላን አደጋ ሲሞቱ የቦካሳ የአጐት ልጅ ዴቪድ ዳኮ የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ ወሰዱ ። በ1966 ቦካሳ የአጐታቸውን ልጅ ገልብጠው አመራሩን ጨበጡ ። የገለበጧቸውን የአጐታቸውን ልጅ ለጥቂት ጊዜ በእሥር ቤት ካቆዩ በኋላ መክረውና አስመክረው በመፍታት አማካሪያቸው አደረጓቸው ።

የቦካሳ አመራር ሊተነበይ የማይችል ሆኖ በእሳቸው አመራር ዘመንም አገራቸው በኤኮኖሚ እያቆለቆለች በመውረድ ሕዝቡ ወደ ባሰ ድህነት ወደቀ ። የሀገሪቱ መሠረተ ልማቶችና ተቋሞች አንድ በአንድ ተንኮታኮቱ ። ቦካሳ ቅጥ ባጡ ቁጥር ችግሩ እየተባባሰ ሄደ ።

በ1971 የእናቶችን ቀን በማክበር በእሥር ቤት የነበሩ ሴቶችን በሙሉ እንዲፈቱ አዘዙ ። እናቶቻቸውን በገደሉ ሁለት ሰዎችም ላይ የሞት ቅጣት እንዲፈጸም አዘዙ ። በዓመቱ ደግሞ የወንጀል ሥራን የሚገቱ መስሏቸው በሌብነት ሁለት ጊዜ የተወነጀሉ ሰዎች ጆሮአቸው እንዲቆረጥ በመደንገግ በሶስተኛው እጃቸው እንዲቆረጥ አዘዙ። ይህም የታሰበውን ውጤት ስላላስገኘ ሌቦቹ ሲገረፉና ሲወገሩ ራሳቸው እስር ቤት እየተገኙ ይመለከቱ ጀመር ። በዚህ ድብደባ ሶስት

ሌቦች ሲሞቱ አርባ ሶስቱ አካለ ጎደሎ ሆኑ ። በሕይወት የተረፉት በአደባባይ ለሕዝብ እንዲታዩ አደረጉ ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ኩርት ቫልድሃይም ድብደባውን በመንቀፍ አወገዙ ።ቦካሳ በበኩላቸው ቫልድሃይምን “አታላይ ፤ የቅኝ ገዢዎች ሹም” በማለት መልስ ሰጡ ። የውጭው ዓለም ቦካሳን ማውገዝ የነበረበት አመች ጊዜ ነበር ። ነገር ግን የአፍሪካ መሪዎችም አላገለሏቸውም ፤ ምዕራባውያንም ርዳታ አላቋረጡባቸውም ፤ ቤተክርስቲያንም የተቃውሞ ድምፅ አላሰማችም ፤ በጭራሽ የተቃወመ የለም ። የአፍሪካ መሪዎች መነቃቀፍ አይፈልጉም ፤ ምዕራባውያንም አንድ መሪ ፀረ—ኮሚኒስት እስከሆነ ድረስ በአጠቃላይ ይደግፉታል ፤ ክርስቲያን ሚሲዮኖችም አፍሪካውያን ያልሰለጠነ ባህርይ ማሳየታቸው የተለመደ ነው ባዮች ናቸው ። ስለዚህም ቦካሳ ቀጠሉ ።

በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ለሃያ ሶስት ዓመታት የቆየች አንዲት የአሜሪካዊ ሚሲዮን ባለቤት የቦካሳ ጭካኔ ከብዙዎቹ አፍሪካውያን አይብስም በማለት እንዲህ ስትል ገልጣለች ። “ቦካሳ የፈረንሳይ ተናጋሪ አፍሪካ ክፍል ኢዲ ፤ አሚን ናቸው ሲባል ይገርመኛል ። ይህን ያህል መጥፎ አይደሉም ፤ እንዲያውም የሰውን ሕይወት የዝንብ ያህል ሳይቆጥሩ እርስ በርስ የሚተላለቁትን ብዙ የአፍሪካ አገሮች ስንመለከት ይህ ቦታ የተሻለ ነው ። ከዚህም በላይ እዚህ ሙሉ የሃይማኖት ነፃነት አለ ። ቦካሳ ትንሽ ያጠፉት ነገር ቢኖር ያን ጊዜ ጥቂት ጆሮዎች መቁረጣቸው ነው ። ያም ቢሆን ጥንት በማዕከላዊው ዘመን በእንግሊዝ አገር የተደረገ ነው ።”

ቦካሳ የሃይማኖት ነፃነት የፈቀዱበት ምክንያት ግልጽ ነው ፤ ራሳቸውም ሁለት ጊዜ ሰልመው እንደገና ሁለት ጊዜ ወደ ክርስቲያንነት ተመልሰዋል ። በ1976 የሊቢያው መሪ ሙአመር ጋዳፊ በሁለት ሚሊዮን ዶላር ስጦታ አባብለው ቦካሳን አሰለሟቸው ። ቦካሳም ገንዘቡን ኪሳቸው አደረጉና የጋዳፊ አውሮፕላን ከባንጉዌ ለመመለስ ሲነሳ እንደገና መጠመቃቸውንና ክርስቲያን መሆናቸውን አስታወቁ ።



በ1973 ቦካሳ የልደት በዓላቸውን ለማክበር የአገሪቱን የመጀመሪያ ቴሌቪዥን ጣቢያ አቋቋሙ ። በዚያን ጊዜ በአገሪቱ አርባ የቴሌቪዥን መመልከቻዎች ብቻ ነበሩ ። ሃምሳ አምስተኛ ዓመታቸውን ሲያከብሩ እያንዳንዱ ዜጋ ሁለት ዶላር ተኩል እንዲያዋጣላቸው ጠየቁ ። ለንግሳቸው የወጣውን ወጪ ለመሸፈንም ሕዝቡ የተቻለውን እንዲያዋጣ በማዘዝ “አንድ ሕዝብ ያለመስዋዕትነት ታሪክ ሊሰራ ስለማይችል ይህን መስዋዕትነት ይቀበላል” ሲሉ ገልጠውታል ።

በ1979 ቦካሳ ባወጡት ድንጋጌ መላው የሀገሪቱ ተማሪዎች የእሳቸው ምሥል ያለበትን ልብስ እንዲገዙና እንዲለብሱ አዘዙ ። እነዚህን ዩኒፎርም ልብሶች የሚሠራው ፋብሪካና የሚሸጠው ሱቅ የራሳቸው ነበር ። ትንሽ ማጉረምረም ሲጀምሩ ተማሪዎቹ በሙሉ ታፍሰው እሥር ቤት ተወሰዱና በራሳቸው በቦካሳና በፖሊሶቻቸው ተደበደቡ ። ከሰማንያ በላይ ሞቱ ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ዓለም አቀፍ ድርጅት ጭፍጨፋውን አጋለጠ ። ፈረንሣይም አሁንስ በቃ በማለት ግማሹን የአገሪቱ ዓመታዊ በጀት መደጐም አቋረጠች ። ወዲያውም በሌሊት የፈረንሣይ አየር ወለዶች በአውሮፕላን መጡና አንድ ጥይት ሳይተኩሱ ቦካሳን ከሥልጣን አውርደው ዳካ ወደ ሥልጣን እንዲመለሱ አደረጉ ። ቀን መቁጠሪያው አሥራ ሶስት ዓመታ ወደኋላ ተመልሶ ፤ አገሪቱ እንደገና ሀ ብላ ጀመረች።

ቦካሳ መገልበጣቸውን የሰሙት ሊቢያ ሆነው ነው ። ጋዳፊን ገንዘብ በመለመን ላይ ነበሩ ። ከሥልጣን መወገዳቸውን እንደሰሙ ከሃያ ስድስት ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ወደ ፓሪስ ሄዱ ። እዚያም እንደደረሱ ከአውሮፕላን እንዳይወጡ ተከልክለው ሃምሳ ስድስት ሰዐት ከተጉላሉ በኋላ ሌላዋ የቀድሞ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት አይቮሪ ኮስት ጥገኝነት ልትሰጣቸው ተስማማች ። ቦካሳ ለጋዜጠኛ ቃለመጠይቅ ላይሰጡ ፤ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይካፈሉ ፤ ሕዝብ በተሰበሰበበት ላይታዩ ቃል ገብተው ጥገኝነቱን ተቀበሉ ። ወደፈረንሣይ የሄዱት በዘረፉት ገንዘብ ብዙ ኩባንያዎች ያቋቋሙበት ከተማ ስለሆነ ነበር ። ስደተኛው ንጉሠ ነገሥት ከንቱ ሆነው ቀሩ ። በአይቮሪኮስት በገዙት ቤት ግቢ ከውሾቻቸው ጋር ሲጫወቱ ይውላሉ ።

ምንም እንኳን የበካሳ አመራር አሳፋሪና የተበላሸ ቢሆንም በሌሎቹም የአፍሪካ አገሮች ያለው ከዚህ ያልተሻለ ሁኔታ ነው ። አፍሪካ በተሳሳተ አመራር ችግር ላይ ወድቃለች ። እንደ አሁኑ አፍሪካ ሚዛናዊ አመለካከት ያላቸው ግልፅ አቅጣጫ የተከተሉ መሪዎች አጥታ አታውቅም ። አገሮቻቸውን ከቅኝ ግዛት አላቀው ሥልጣን የያዙት የመጀመሪያዎቹ ፕሬዚዳንቶች በእርጅና ሞተዋል ። ወይም በመፈንቅለ መንግሥት ተወግደዋል ። የዛሬዎቹ በትምህርትም ፣ በዕድሜም ፣ በብሔራዊ ስሜትም ፣ በሥልጣኔም ያነሱ ናቸው ። አዲሶቹ መሪዎች ያከናወኑት ነገር ቢኖር የሥልጣን ፖለቲካ ብቻ ነው ። ከፓርቲያቸው መስመር የሚመጣውን አሉባልታ ከማዳመጥ በስተቀር የሌላውን ሕዝብ ድምፅ ፀጥ አድርገውታል ። ሥልጣኔን ይቀሙኛል በሚልም የሚተኳቸው ችሎታ ያላቸው ሰዎች አላዘጋጁም ። በዚህም ላዕላይ መዋቅሩን ችሎታ ያለው ሰው የሌለበት ባዶ አድርገው ጉልበት ያለውና ጠመንጃ ያነሳ እንጅ ችሎታ ያለውና የሕዝብ ድጋፍ ያለው ሰው ሥልጣን እንዳይዝ አድርገዋል ።

አገሮች ነፃ ሲወጡ የመጀመሪያዎቹ መሪዎች በሕዝብ በመወደድና በቅኝ ገዢዎች በመመረጥ የተመደቡ ነበሩ ። በነፃነት እንቅስቃሴው ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ወታደሮች ወይም ሲቢሎች ነበሩ ። ከመካከላቸውም እንደ ጋናው ክዋሜ ንክሩማ ያሉ ፣ እንደ አንጐላው አውጐስቲኖ ኔቶ ያሉ የተከበሩ የፖለቲካ ሰዎች ይገኙባቸዋል ። የታወቁት ምሁር የሴኔጋሉ ሊዮፖልድ ሴዳር ሴንጐርም ከሚጠቀሱት ናቸው ። የብዙኃኑ ፓርቲ ዲሞክራሲ በነበረባቸው ሳይቀር ሁኔታው እየተቀየረ ወደ አንድ ፓርቲ ፡ ወደ ባለሙሉ ሥልጣን ፕሬዚዳንትነት፣ ገናና ስም ወደመገንባት መጥፎ ፖለቲካ እያዘቀጡ ሄዱ ። ወዲያውም አፍሪካውያን ቅኝ ገዢዎችን ለማስወገድ ያስቸገራቸውን ያህል የራሳቸውን ጥቁር ፕሬዚዳንቶች ማስወገድ ተሳናቸው ።

ፕሬዚዳንት የሆኑት ሰዎች የሚለወጡት ወይም ሲሞቱ ያለዚያም ሲገለበጡ ብቻ ሆነና በሕዝቡ ነፃ ምርጫ ሥልጣን መያዝና በሕዝቡ ቅሬታ መወገድ የማይታሰብ ሆነ ። በፈቃዳቸው ሥልጣን የሚለቁ ፕሬዚዳንቶች ጠፉ ። በሥልጣን በቆዩ ቁጥር ሕዝባቸውን



የሚንቁ እየሆኑ ሄዱ ። የመቆየታቸው ምሥጢር በዙሪያቸው ያሉትን በጥቅም በመያዝ ፣ እንደነሱው መዝባሪና ለሥልጣናቸው ታማኝ የሆኑ አድርባዮችን በማሰለፍ ነው ።

በኡጋንዳ በኢዲ አሚን ዘመነ መንግሥት አሜሪካን አብራሪዎች የተመደቡበት 707 የተሰኘ አውሮፕላን በየሳምንቱ ማክሰኞ ወደለንደን ይሄድና የተሰፉ ልብሶች ፣ ውስኪ ፣ ሲጃራ ፣ የሚያማምሩ የእጅ ሰዓቶች ፣ ውድ ምግቦች ፣ ልዩ ልዩ የፀሐይ መነፅሮች የመሳሰሉ የቅንጦት ዕቃዎች ያመጣ ነበር ። በዚያን ወቅት የኡጋንዳ ኢኮኖሚ ተንኮታኩቶ መሠረታዊ የሆኑት ስኳርና ወተት ሳይቀር በሰልፍ የሚገዛበት ጊዜ ነበር ።

እነዚህ ከውጭ የሚመጡት የቅንጦት ዕቃዎች ለአሚን ታማኞች የሚከፋፈሉ ነበሩ ። ሲቢሉ ሕዝብ በድህነት ታስሮ የጦር መኮንኖች ኪራይ በማይከፍሉባቸው ዘመናዊ ቪላዎች እንዲኖሩ ይደረግ ነበር ። ከሲቢሉ የተነጠቁ ፔጆና ፊያት መኪናዎች ይሰጣቸዋል ። ከእስያ ነጋዴዎች የተወረሱ ሱቆች ተሰጥተዋቸዋል ። አሚንም ለፖለቲካ ሕልውናቸው ሲሉ ፣ መኮንኖችም ለጥቅማቸው ሲሉ ተደጋግፈው ቀጠሉ ።

ሌሎችም ፕሬዚዳንቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር እንደዚሁ ናቸው ። ሥልጣን የሚሰጡት ከራሳቸው ጎሳ ለሆነው ነው ። የቀድሞው የናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ካራንጃ በሰነዘሩት አስተያየት ፤ “አፍሪካ እንድትለማ ከተፈለገ ተማርሁ የሚሉት ሕሊናቸውን እንደገና መመርመርና የአፍሪካን ሕዝቦች ልዩ ሁኔታና ታሪክ መረዳትና መቀበል አለባቸው ። ሐቀኛ በመሆን የአፍሪካ ሕዝቦች ለነፃነት የተዋጉት ለባሰ ባርነትና ለከፋ ድህነት ያለመሆኑን መገንዘብ አለባቸው ። የአፍሪካ ሕዝብ የመምረጥ መብቱን ማግኘት ያለበት ጊዜ አሁን ነው” ብለዋል ።

ነፃ ምርጫ በአፍሪካ ሕልም ሆኗል ። ተደረጉ የሚባሉት ምርጫዎች ሁሉ የውሸት ናቸው ። ሚልተን ኦቦቴ ከ1962 እስከ 1971 ኡጋንዳን በገዙበት ጊዜ ፓርላማውን በተኑ ፣ የኤኮኖሚ ተቋሞችን ወረሱ ።

ሕገመንግሥቱን እንደገና በማርቀቅ ራሳቸውን የእድሜ ልክ ፕሬዚ
ዳንት አደረጉ ፡ ብሔራዊ ምርጫዎችን አገዱ ፡ በአንድ ፓርቲ ብቻ
የምትመራ ሀገር አደረጓት ፡ ኢዲ አሚንን የጦር አዛዥ አደረጉ ።
በ1980 አቦቴ በታንዛኒያ በስደት ኖረው በአሸናፊነት ሲመለሱ "ከእውን
ወዲያ ማንም ግለሰብ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን በማፈራረስ የሕዝቡን
ፍላጎት እንዲያፍን መፍቀድ የለብንም" በማለት አስጠነቀቁ ። አቦቴ
ሥልጣን እንደያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ የግለሰብ መብት መርገጥና
ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን ማፈራረስ ቀጠሉ ።

በአፍሪካ ማንበብ የማይችለው ሕዝብ አያሌ ስለሆነ የፕሬዚዳን
ቶች የምርጫ ውድድር ለይስሙላ ሲዘጋጅ መራጩ ሕዝብ የሚለይ
በት ምልክት ይኖራቸዋል ። እንደ ሞዛምቢክ ባሉት እጅ በማውጣት
ይካሄዳል ። በ1979 በዛምቢያ የፕሬዚዳንት ምርጫ ኬኔት ዴ.ቪ.ድ ካው
ንዳ ለፓርቲያቸው ምልክት የመረጡት የሚበር አሞራ ነበር ። ተቃዋ
ሚው ተወዳዳሪ የተፈቀደለት ምልክት እባብ ነበር ። ከ1964 ጀምሮ
እስካሁን የሚመረጡት በዚህ ዓይነት ዝግጅትና ሥልቶች የተቃዋሚ
ውን ወገን ተወዳዳሪዎችን በእሥር ቤት እንዲያቆዩአቸው እየተደረገ
ነው ።

በአንዳንድ ሀገሮች የዲሞክራሲ ፍንጭ እየታየ ነው ። በ1977
በጊኒ የገበያውን ቦታ የሚያካሂዱ ሴቶች በማመፃቸው የአህመድ ሴኩ
ቱሬን መንግሥት አንቀጠቀጡት ። በተከታዩ ዓመት ደግሞ በጋና
የሙያተኞች የሥራ ማቆም አድማ ወታደራዊ አገዛዝ እንዲያበቃ
አስገደዱት ። በላይቤሪያም የዋጋ ጭማሪን በመቃወም የተነሳው ሁከት
ፕሬዚዳንት ዊሊያም ቶልበርት የኢኮኖሚ ፕሮግራማቸውን እንዲመ
ረምሩ በማስገደድ በዓመቱ ከሥልጣን ለመወገዳቸው አስተዋጽኦ
አድርጓል ።

በ1983 በናይጀሪያ በሥልጣን ላይ የነበሩ የጦር መኮንኖች
በሕዝብ ለተመረጠ ሲቪል መንግሥት ሥልጣን አስረክበው ወደ
ጦር ካምፓቸው ተመለሱ ። በኬንያና አንጎላ በመጀመሪያዎቹ ፕሬዚ
ዳንቶች ሞት የተተኩት በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተመረጡት ናቸው ።
በታንዛንያና በኬንያ ተሿሚዎቹ የፓርላማ አባላት በአስመራጮች ምርጫ



ከፓርላማ ተሰናብተዋል ። አፍሪካ በእነዚህ የብስለት ምልክቶች ትቅ
ራለች ። ነገር ግን አንድ ዓቢይ ጥያቄ ገና መልስ አላገኘም ። የምዕራብ
ዓይነት ዲሞክራሲ ለአፍሪካ ፍላጎት ተስማሚ ነውን?

አይመስለኝም ፤ ለአሁኑ ጊዜ አይበጅም ። የተበታተኑትንና በት
ግል ላይ ያለችው አፍሪካ ዛሬ የብዙኃን ፓርቲዎች የተቀናቃኝ አመ
ራር ፡ ነፃ ጋዜጦችና ልቅ ክርክር የባሰ ውዝግብ ያስከትላል የሚል
ሥጋት ይታያል ። ብሔራዊ ግቦች በግልጽ ባልተቀመጡባቸው ይህ
ዓይነቱ ነፃነት የተለያዩ አንጃዎች በሕዝቡ ጥቅሞች ኪሣራ ለግል
ጥቅማቸው እንዲሻኮቱ ይገፋፋል ። ብሔራዊ ተቋሞች ይህንን ግፊት
ለመቋቋም ብቃት የላቸውም ። መንግሥታትም ከብሔራዊ ጉዳዮች
ውጭ የሚገፋፉ ኃይሎችን ለመቋቋም የተጠናከሩ አይደሉም ።

ለአሁኑ ጊዜ ብዙ የአፍሪካ አገሮች የሚመሩት በአምባገነኖች
ነው ። ዲሞክራሲ ውሎ አድሮ የሚመጣ ነው ፤ ለዚያውም የሚመጣ
ከሆነ ። የምዕራብ ዲሞክራሲም ቢሆን እንደ ኮምኒዝም ሁሉ የአፍሪ
ካን የፖለቲካ ሕመሞች ሙሉ በሙሉ የሚፈውስ አይመስለኝም ።
አፍሪካ ለግንባታ የሚያስፈልጋት አፍሪካዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት
መፍጠር ነው ። ከምሥራቅም ሆነ ከምዕራብ ያልተገለበጠ ፡ ከካፒታሊ
ዝምም ከሶሺያሊዝም ጠቃሚዎቹን መርጦ ያጣመረና ከአፍሪካ
ታሪክና ባህል ጋር የሚጣጣም ሥርዓት መዘርጋት ። ይህም ዛሬ አፍ
ሪካውያን በስፋት ተቃራኒ ሃሳቦች አድርገው የሚመለከቷቸውን
የኢኮኖሚ ማበረታቻና ማህበራዊ ፍትሕ የሚባሉ ንድፈ ሃሳቦችን
አጣምሮ መያዝ አለበት ።

የሚያሳዝነው የሚበጀውን ሥርዓት ለመምከር የሚሹ ፕሬዚዳን
ቶች የሉም ፤ ምክንያቱም ሥልጣናቸውን የሚቀንስባቸው ስለሚሆን
ነው ። ሀገርን ያህል ነገር ለመምራት ጥበብና እርቆ አስተዋይነቱ
ያላቸው መሪዎች ጥቂት ናቸው ። በዚህም የተነሳ ዛሬ ብዙዎቹ ሀገ
ሮች የሚመሩት ከወሐፊነት የማይዘል ችሎታ ባላቸው ጠመንጃ
ባነሱ ሰዎች ነው ።

እንደ ቦካሳና አሚን ዓይነት ጥፋቶች የሌላቸው መሪዎችን መቀ
ለጃ ማድረግ ይቻላል ። የእነሱ አሳፋሪ ተግባር ግን አፍሪካ አህጉርን

ብቻ ሳይሆን ዓለምንም ለመለወጥ የረዱ የሚደነቁ መሪዎች እንደነበ ሯት ሊያድበሰብስብን አይገባም ። ከእነዚህ ውስጥ ጆሞ ኬንያታ የማይረሱ ናቸው ። በኬንያታ የነፃነት መናፈሻ (ኡሁሩ ፓርክ) ለተሰ በሰበ ሕዝብ በሚያስገመግም ድምፃቸው "ሀራምቤ" (እንተባበር) የሚለውን ቃል በማስተጋባት ነጭ ጭራቸውን ከፍ አይርገው ሲያወ ዛወዙ ግርማ ሞገስ ያላቸው ሰው ነበሩ ። እንደማንኛውም ሰው የሰብ ዓዊ ክብር ፣ የዕድገትና የአንድነት ብሎም የጎሳዎች መፈቃቀር ጠን ካራ ፍላጐት ለአፍሪካ ባዕድ አስተሳሰቦች እንዳልሆኑ አሳይተዋል ።

ለነፃነት በሚታገሉበት ወቅት ኬንያታ "እኛ አውሮፓውያንን ከዚህ አገር ለማስወጣት አንፈልግም ። የምንጠይቀው እንደነጮቹ በእኩልነት እንድንታይ ነው ። እዚህ በሰላምና በደስታ እንድንኖር ከተፈለገ የዘር አድልዎ መወገድ አለበት" በማለት ተናግረው ነበር ።

ኬንያታ በጎ ምኞታቸው እውን ሆኖ ሳያዩት አረፉ ። ከፍተኛ ግምት ይሰጡት የነበረው የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ ኬንያ ፣ ታንዛ ኒያና ኡጋንዳ የነበሩበት ኅብረት በ1977 ፈረሰ ። የአፍሪካ አንድነት መጠናከር ምኞታቸው በርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ በጦርነትና በወሬ ኞች ሽባ ሆኖ ቀረ ። ድንቁርና ፣ ድህነት ፣ በሽታ አብዛኛውን የአህጉሪቱ ክፍል እንደተቆራኘ ቀጠለ ። የራሳቸው አገርም በጎሳ ልዩነት መሻኮት ጀመረች ፤ የተማሩ ጥቂቶች እየበዙና ንብረትና ሥልጣን እያካበቱ በሄዱ ቁጥር የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቅኝት ይሰማ ጀመር ። የራሳቸው ቤተሰቦችና የሚተማመኑባቸው ሰዎች ሳይቀሩ ሌባ ቢሮክራቶች በመ ሆን ከዝሆን ጥርስ እስከ ቡና በኮንትሮባንድ ማጋዝ ጀመሩ ። እን ዲያም ሆኖ ኬንያን ሥልጣን ሲይዙ ከነበረችበት ደረጃ አንስተው የተሻለ ቦታ አድርሰዋት ሄደዋል ። በእሳቸው የአመራር ዘመን የአገ ሪቱ ትውልድ በመረጋጋት ፣ ኑሮውን በማሻሻልና የጎሳ ግንኙነቶችን በመልካም ሁኔታ በመያዝ እንዲኖር በማስቻላቸው ትልቅ ቁምነገር አውርሰዋል ።

ኬንያታ በ1892 በሰሜን ኬንያ ኩኩዩ ጎሳ ተወለዱ ። የገበሬ ልጅ የነበሩት ኬንያታ በከብት እረኝነት ሲያድጉ ፣ በሚሲዮኖች ት/ቤት ማንበብና መፃፍ ተማሩ ። ስማቸውም ካሙ ዋ ፣ ኒጊንጊ ይባል ነበር ።




ጆሞ ኬንያታ

በአሥር ዓመታቸው የጀርባ አከር ካሪ ሕመም ይዟቸው በአቅራቢያ የነበሩ ሚሲዮን ሐኪሞች ቀዶ ሕክ ምና በማድረግ ሕይወታቸውን አተ ረፉት ። ወዲያውም በሚሲዮኖች ተጠመቁና አውሮፓዊ ስም ተሰጣ ቸው ። በቅኝ አገዛዝ በር ከፋች መሆናቸውን በመገንዘብ ሚሲዮ ኖችን መንቀፍ ጀመሩ ። በቤተክር ስቲያን ስብከት ቢያሰሙም በአ ንድ ወቅት በሚሲዮን ስም ስለሚ ሰራው ተንኮል ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል ። "ሚሲዮኖች ሲመጡ እኛ መሬቱን እነሱ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱን ይዘው ነበር ። አይናችንን ጨፍነን እንድንፀልይ አስተማሩን። ዓይናችንን ስንገልጥ እነሱ መሬታችንን ይዘዋል ፤ እኛ ቅዱስ መጽሐፍ ጨብጠን ቀረን ።"

በ1921 በሃያ አንድ ዓመታቸው ኬንያታ ወደ ናይሮቢ ሄዱና በፍርድ ቤት አስተርጓሚነትና በውሃ ቆጣሪ አንባቢነት መሥራት ጀመሩ ። በዚያም እንዳሉ አፍሪካዊ ስም ለወጡ ፤ ጆሞ ፣ ኬንያታ የሚ ለውን ስም ወሰዱ ። ጆሞ ማለት የጋለ ጦር ማለት ሲሆን ፤ ኬንያታ ማለት ደግሞ የማሳይ ጎሳዎች የሚታጠቁት ልዩ ቀበቶ መጠሪያ ነው ።

ኬንያታ ግርማ ሞገስ ያላቸው ፣ ጥሩ ተናጋሪና ብልጥ ስለነበሩ የቅኝ ገዢዎችን መሰናክሎች ተቋቁመው የፖለቲካ ሰው ሆነው ብቅ አሉ ። ለአፍሪካውያን የተሻለ የሥራ ዕድል ፣ ለመሬት ይዞታ መሻሻል ፣ ለተሻለ ትምህርትና ሕክምና ፣ በአጠቃላይ ለተሻለ ሕገመንግሥትዊ ድንጋጌ ለሚታገለው የምሥራቅ አፍሪካ ማህበር የፕሮፓጋንዳ ኃላፊ ሆኑ ። ይህ ማህበር የግዴታ ሥራ እንዲቀር ፣ አፍሪካውያን እንደ መታ ወቂያ የሚሆናቸው የብረት ሜዳልያ ዓይነት መያዝ እንዳይገደዱ ይታ ገል ነበር ።

በ1928 ኬንያታ የኪኩዩ ማዕከላዊ ማህበር ዋና ፀሐፊ በመሆን የጎሳቸውን ለም መሬት ለማስመለስ ትግል ጀመሩ ። በዚያን ዘመን በኬንያ የነበሩ ሕንዶች የገንዘብ ድጋፍና ሕጋዊ ምክር ያደርጉላቸው ነበር ። ወዲያውም ወደ ለንደን ለአቤቱታ ሄደው በዚያው የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ፣ ለጋዜጦች አቤቱታቸውን በማሰማት ፣ አንዳንድ የአውሮፓ አገሮችን በመጐብኘትና የትግል ድጋፍ በመጠየቅ ለአሥራ አምስት ዓመታት በዚያው ኖሩ ። በዚህ ቆይታቸው ለተመሳሳይ ትግል በዚያ ከነበሩ አፍሪካውያንና በኋላ የየሀገሮቻቸው መሪ ከሆኑት ከዋሜ ንክሩማና ካሙዙ ባንዳ ጋር ተገናኝተው ለመላ አፍሪካ መታገል መረጡ ።

በ1946 ወደ ኬንያ ተመልሰው ትግላቸውን ቢቀጥሉም ቅኝ ገዥዎቹ በ1952 ወደ እሥር ቤት ስላወረዷቸው ብዙ መንገላታት ደረሰባቸው ። በ1959 ከእሥር ሲለቀቁ ባደረጉት ንግግር "የዘር ጥላቻ ማክተም አለበት ፤ የጐሣዎች ግጭት ማብቃት አለበት ፣ ያለፈውን መራራ ሕይወትና መጠላላት እንቅበረው ። አዲሲቷን ኬንያ እንገንባ ። ይህን ብሔራዊ ስሜት መፍጠር ከቻልንና ብሔራዊ አቅጣጫችንና መታወቂያችን ካደረግነው ብዙዎቹን የኢኮኖሚ ችግሮቻችንን እንፈታለን" ብለው ነበር ።

ኬንያ በ1963 ነፃነቷን ስትቀዳጅ ኬንያታ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ ፤ በኋላም ፕሬዚዳንት ተባሉ ፣ በዚያን ጊዜ እምነታቸው ሁሉ የጎሳ ልዩነትን አስወግደው ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር ነበር ። ኬንያታ የአፍሪካን ክብር ከፍ በማድረግና ነጮች ከጥቁሮች ጋር በሰላም ለመኖርና ለመስራት እንዲችሉ ያደረጉ ትልቅ ሰው ናቸው ።

ኬንያታ ብዙ መልካም ነገር ቢያከናውኑም ሁለት መሠረታዊ ድክመቶች ታይተውባቸዋል ። አንዱ የራሳቸውን የኪኪዩ ጎሳ የሌላው ጎሳ የበላይ አድርገው በያለበት ሥልጣን በመስጠት ማዳላታቸው ነው ። ሌላው የተዘገበባቸው ድክመት መጠነኛ ተቃውሞ ያነሱባቸውን የሌላ ጎሳ አባል የሆኑ በሳል የፖለቲካ ሰዎች ሁሉ ለእሥራትና ለሞት መዳረጋቸው ነው ። ኦጊንጋ ኦዲንጋ የተባሉ ከሉዎ ጎሳ የተወ



ለዱ በሳል የፖለቲካ ሰውና ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩትን በ1969 አሳሰሩ ። ቶም ፣ ቦያ የተሰኙት ዝነኛና ተስፋ የተጣለባቸው የሉዎ ጎሳ የፖለቲካ ሰው ማን እንዳስገደላቸው ሳይታወቅ በኪኩዩ ጎሳዎች በጥይት ተገደሉ ። ቶምቦያ ለአፍሪካ የሁለተኛው ትውልድ አመራር ሁሉም የተመኘቸው ታላቅ የፖለቲካ ሰው ነበሩ ። በ1975 ጀምስ ካሪኩ የተሰኙ ሌላ በሳል የፖለቲካ ሰው አንዳንድ ድክመቶችን አንስተው ስለተቃወሙ ተገደሉ ። ከ1975—1977 አምስት የሚሆኑ የፓርላማ አባላት አንዳንድ የኬንያታ ድክመቶችን አንስተው እርማት እንዲደረግላቸው በመጠየቃቸው በሰላዮች ታፍነው ታሰሩ ። እነዚህ ስህተቶች በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ካሉት ጭቆናዎች አንፃር ሲታዩ ቀላል ናቸው ቢባልም ታሪክ በስህተትነት ዘግቧቸው ይገኛሉ ።

የጭቁን ሕዝቦች ተስፋ ሆነው በፕሬዚዳንትነት እስከሞት ያገለገሉት የቀድሞው የከብት እረኛ ኬንያታ ሲሞቱ በቀብራቸው ላይ ከስድሳ አገሮች የመጡ መሪዎችና ታላላቅ ሰዎች ተገኝተዋል ። ከእሳቸው ሞት በኋላ የተፈራው የጎሳ ጦርነት አለመነሳቱ ለኬንያ ታላቅ ፀጋና ለብስለታቸው ምልክት ነው ። ኬንያን የብልጽግና ጐዳና እስጨብጠዋት መሄዳቸውን ማረጋገጫ ከአገሪቱ ድንበር ባሻገር ካሉት በብጥብጥና በደም መፋሰስ ላይ ካለችው ኢትዮጵያ ፣ በውድቀት ላይ ካለችው ሶማሊያና በትርምስ ላይ ከምትገኘው ኡጋንዳ ጋር ማነፃፀር ይበቃል ።

ኬንያታ ከሌሎች መሪዎች የተለየ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ብዙ ነው ። ሞቡቱ የከበርቴዎችንና የነጮችን ሀብት በመውረስና በማባረር ሲያስወጡ ኬንያታ ይህን ባለማድረግ የነጮችንና የባለሀብቶችን የቴክኒክ ዕውቀትና የአስተዳደር ጥበብ በመጠቀም አፍሪካውያን አብረዋቸው በመሥራት ከእነሱ እንዲማሩና እንደነሱም እንዲሆኑ አድርገዋል ። ችሎታ ያላቸውን በማባረር አፍሪካውያን ሊተኳቸው የማይችሉትን ቦታዎች ባዶ በማስቀረት የኢኮኖሚ ውድቀት እንዲከሰት አላደረጉም ። ይልቁንም የውጭ ባለሀብቶችና ቱሪስቶች ያለገደብ እንዲጐርፉ በማድረግ የኢኮኖሚ ልማቷን አፋጠኑ ። ኬንያታ ለእርሻው ክፍለ ኤኮኖሚ የተግባር ቅድሚያ ትኩረት ሰጡ ። የዩጋንዳው አሚን

ከዓመታዊ በጀት ግማሹን ለጦርነት በማዋል ለሰባት ዓመት ትምህርት ቤትና ሐኪም ቤት ማሰራታቸውን ሲያቆሙ ኬንያታ ለመከላከል የመደቡት ከበጀታቸው ሰባት በመቶ ብቻ ነው ። ይህም ሌሎች ግንባታዎችን ለማካሄድ በቂ ሀብት ስለተወላቸው ብዙ ማህበራዊ መገልገያዎችን ገነቡ ። እንደ ታንዛኒያ ያሉት አገሮች ሶሻሊዝምን በማፍቀር ፣ ንብረት በመውረስና የኢኮኖሚ ማበረታቻዎችን በመከልከል እድገትን ሲያዳክሙ ኬንያ መዋዕለ ንዋይን በማበረታታት ምርት እንዲያድግ አድርጋለች ።

የሚያስደስተው ነገር ኬንያ ብዙም ቅምጥ ሀብት ሳይኖራትና ለእርሻ ምቹ የሆነው መሬትዋ ከሃያ በመቶ ያነሰ ሆኖ ሳለ በኬንያታ ብልጠት አገሪቱ የሚያዋጣትን በማመን የተሻለ አቅጣጫ መቀየሳቸው ነው ። ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች የኬንያታ ዓይነት መሪ ቢኖራቸው ቢያንስ የኬንያን ያህል እድገት ማሳየት በቻሉ ነበር ።

በሌላው ዓለም ምናልባትም እንደ አፍሪካ የአገሮች ባህርይ በመሪዎች ዓይን አይታይ ይሆናል ። የአገሪቱን ሁኔታና አቅጣጫ የሚወስነው መሪው ነው ። አዲስ መሪ ሥልጣን ሲይዝ የአገሪቱ አቅጣጫ ከቀድሞው ጨርሶ የተለየ ሊሆን ይችላል ። የሀገር መሪዎች እስከአለንበት ዘመን ድረስ የራሳቸውን አመለካከት በሕዝባቸው ላይ የመጫናቸው ጉዳይ ያለ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የፕሬዚዳንቶች ርዕዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ ተጨባጩን ዓለም በሚያጤኑ የፖለቲካ ሰዎች እየተገፋ ተቀባይነት እያጣ ሄዷል ። የንድፈ ሃሳብ ሰዎች ያለሙትና በተጨባጭ የተከሰተው አልጣጣም ሲል ያላሰቡት ግፊት እየመጣባቸውና ራሳቸውንም መለወጥና ግፊቱን መቀበል እየተሳናቸው ታይተዋል ። በታንዛንያ የተፈጠረውም ይኸው ነው ።

በአገራቸው ውስጥ “ሙዋሊሙ” (መምህር) እየተባሉ የሚጠቀሱት ጁሊየስ ኒሬሬ ምሥራቅና ምዕራብ ያደነቃቸው ቀና አመለካከት ያላቸው መሪ ናቸው ። ለሶሻሊዝም ያቀረቡት ንድፍ በሞዴልነት ሲጠቀስ ኖሯል ። ፕሬዚዳንት ሆነው እንኳ ደመወዛቸው በዓመት 6ሺ ዶላር ብቻ ነበር ። ታንዛንያን የእኩልነት ሀገር ለማድረግ ተመኝተው ነበር ። ዋናው ትግል ድህነትን ፣ በሽታንና ድንቁርናን ማጥፋት ነው ብለው ተነስተውም ነበር ። አስተሳሰባቸውና ንግግራቸው ከቀልድ ጨዋታቸው ጋር የሚስብ ነው ።

ይህ ሁሉ መልካም ሰውነት ይኑራቸው እንጅ አንድ ጉልህ ድክመት ነበረባቸው ። የሚሰብኩትን ቁምነገር በተግባር የሚያውሉ አይ



ደሉም ። ስለዚህም በተጨባጭ ያከናወኑት ነገር ለታንዛንያ ያስገኘላት ጥቅም ኢምንት ነው ። አሥራ ሰባት ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝባቸው የእሳቸውን ሶሻሊስታዊ አቅጣጫ በመቀበል ለሃያ ዓመታት ማሰኑ ፤ በመጨረሻም ያገኘው ባዶ ማሰሮ ብቻ ነው ።

የጎረቤት ሀገርን መንግሥት የገለበጠ ሌላ የአፍሪካ መሪ የለም ። ኔሬሬ የሶስት አገሮችን መንግሥታት በመገልበጥ ረድተዋል ። በ1975 የኮሞሮን ፣ በ1977 የሲሼልስን ፣ በ1979 ደግሞ የኡጋንዳን መንግሥት አስገልብጠዋል ። ስድሳ ሺህ የሚሆነውን ጦር ሠራዊታቸው አሚንን ለማስወገድ ተጠቅመውበታል ። ነፃ አውጭ ሠራዊታቸው ግን ወዲያው ወራሪ በመሆን ግድያና ዘረፋውን ተያያዘው ። በኡጋንዳ ሶሻሊዝምን የሚቀበል መንግሥት እንዲመጣ በመሻት ለተለወጡት ፕሬዚዳንቶች ሁሉ አዛዥ በመሆን አልታዘዝ ሲሏቸው ሁለቱን በማስገልበጥ ለውጠዋቸዋል ።

ኔሬሬ በጥቁር አፍሪካም ሆነ በደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች አመራር የሚታየውን ጭቆና ለማውገዝ ቀዳሚ ቢሆኑም እስከ 1979 ድረስ ኒሬሬ ያጐሯቸው እስረኞች በደቡብ አፍሪካ ካለው የእስረኛ ቁጥር ይበልጥ ነበር ። በዚያው ዓመት ለ6ሺ400 እስረኞች ምህረት አደረጉ ፤ 4’436 የሚሆኑትን በተከታዩ ዓመት በነፃ ለቀቋቸው ። የጽሑፍ ነፃነትን በማፈን ሁሉንም ጋዜጦች የመንግሥት አድርገዋል ፣ በዚህም የተቃውሞና ነፃ አስተያየትን ዘግተዋል ። በየጊዜው ለፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የሚቀርቡት ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆነው ነው ።

ከውጭ መንግሥታት ብዙ የገንዘብ ርዳታ ያገኛሉ ። አገራቸው ግን ብዙም አልበለፀገችም ። የእርሻ ምርት እየቀነሰ ነው ። ፋብሪካዎች ከአቅማቸው አርባ በመቶውን ያህል ብቻ ነው የሚያከናውኑት ። የዳሬሰላም ከተማ እየኮሰሰች ሕዝቡም ስሜቱ እየቀዘቀዘ የሄደ ነው ።

በ1961 ታንዛኒያ ነፃ ስትወጣ ኔሬሬ የተረከቧት ሀገር ምንም የሌላት ናት ። ኪቃጫ በስተቀር ሌላ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ አልነበራትም ። ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ዜጎችዋ አንድ መቶ ሃያ ብቻ ነበሩ ። ኔሬሬም በ1967 ጥር ወር የአሩሽያን አዋጅ አወጡ ። ይህም

የቻይና ዓይነት ሶሻሊዝምን ለመዘርጋት መሪ ፕላን ነበር ። የግል ተቋሞችን ወረሱ ። በመቶዎች የሚቆጠሩ “ኡጃማ” (የቤተሰብ) መንደሮች ተመሠረቱ ። ብዙዎቹ ከከተማ በወታደር በታፈሱ ቦዘኔዎች የተሞሉ መንደሮች ናቸው ። ኔሬሬም ለግል ማሰብ ትታችሁ ጠንክራችሁ ከሰራችሁ ለሁሉም የምትሆን ታንዛንያ ትፈጠራለች በማለት መስበክ ጀመሩ ። ሰፊውን ሕዝብ በማንቀሳቀስ ውጤት ማግኘት የሚቻለው አንድ ወጥ የሆነ ሕዝብ ሲኖርና የተነሳለት የጋራ ግብ ሊጨበጥ የሚቻልና ፍሬያማ ነው ብሎ ሲያምን ብቻ ነው ።

ኔሬሬ ያከናወኑት የኤኮኖሚ ማበረታቻዎችን ማጥፋት ነው ። በዓመት ከ30'000 ዶላር በላይ ገቢ ያለው በዘጠና አምስት በመቶ ቀረጥ እንዲከፍል ወሰኑ ። ስለዚህም ማንም ሠርቶ ብዙ ማግኘት የሚፈልግ የለም ። ወደ ዛምቢያ የሚዘልቀው የባቡር መስመር ሃዲድ ይሰናከላል ፣ የሚጠግነው የለም ። ስለዚህ የቻይናን የቴክኒክ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ለጥገና መጥራቱ ግድ ነው ። አገሪቱ በየቀኑ ወደ ድህነት ታሽቆለቁላለች ።



ጁሊየስ ኔሬሬ

እንዲያም ሆኖ ኔሬሬ ለሕዝባቸው ቀናው ጉዳና ያ ፣ የተያያዙት ብቻ እንደሆነ በግትርነት ይሟገታሉ ። በሰላሳ ዓመት አመራራቸው የአመለካከት አቅጣጫቸው ሳይለወጥ ቀጠለ ። የቀረው የአፍሪካ ክፍል ከሕዝብ በመጣ ግፊት የተለያዩ አዲስ ሥርዓቶችን ሲሞክርና ከተጨባጩ ሁኔታ ራሱን ለማጣጣም ሲጣጣር ኔሬሬና ታንዛንያ ያንኑ ሙጭጭ ብለው ቀሩ ።

“ታንዛንያ በኢኮኖሚ ችግሮች ምክንያት የኡጃማ ፖሊሲዋን ትለውጣለች ብለው የሚያስቡ ቢኖሩ ጊዜያቸውን እያጠፉ ነው ። ምንጊዜም አንለውጥም” አሉ ኒሬሬ ። የታንዛንያ ዓይነተኛ ችግርም ይኸው ነው ።



አብዮት የሚለው ቃል በአፍሪካ በጣም የተለመደና የሰለቸ ቃል ነው ። ከሞላ ጎደል እያንዳንዱ ፕሬዚዳንት ወይም አብዮት ፈጣሪ ነኝ ባይ ነው ፤ ያለዚያም አብዮት የወለደኝ ነኝ ማለት ይመርጣል ። ኢዲ አሚን ሳይቀር በኡጋንዳ እየተዘዋወሩ የራሳቸውን ሕዝብ ሲያርዱና ሲገድሉ “አብዮታዊ መሪ እንደመሆኔ ሥራ ስለሚበዛብኝ እረፍት የለኝም” ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል ። ይሁን እንጂ ጠመንጃ ተሸክሞ መዞር አብዮተኛ አያደርግም ። መንግሥት መገልበጥም እንዲሁ ነው ። አብዮታዊ ለመሆን አንድ ሰው የወደፊቱን አርቆ የሚያስተውልና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዕቅድ ለማውጣት የሚችል መሆን አለበት ። ይህ ችሎታ ያላቸው የአፍሪካ መሪዎች ጥቂቶች ናቸው ።

አንዱ አብዮተኛ የሞዛምቢኩ መሪ ሳሞራ ማሼል ናቸው ። እሳቸውም የፖርቹጋልን ቅኝ አገዛዝ በመታገል ሂደት የተፈጠሩ ናቸው። እሳቸውን በቀላሉ መውደድ ወይም ወዲያው መጥላት ይቻል ይሆናል ፤ ቸል ማለት ግን አይቻልም ። ለምሥራቁ ካምፕ የአፍሪካ ውድ ልጅ ናቸው ። ለምዕራቡ ዓለም ደግሞ ኃይለኛና በጀ የማይሉ የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም አክራሪ ናቸው ። ማንም የፈለገውን ስም ቢሰጣቸው ለማሼል ሁለንተናዊ ቁምነገር በአሥሩ ዓመት ፀረ—ቅኝ አገዛዝ ትግል (ከ1964—1974) የተቀረፀውና በመካሄድ ላይ ያለው አብዮት ነው ።

ማሼል በ1933 ከገበሬ ቤተሰብ ተወለዱ ። ፖርቱጋሎችን ለመዋጋት በአልጄሪያና በታንዛኒያ ሥልጠና ወሰዱ ። የታንዛንያን ድንበር አቋርጠው ወደ ሞዛምቢክ በመግባት የነፃነት ትግሉን ከጀመሩት የመጀመሪያዎቹ 250 ተዋጊዎች አንዱ ናቸው ። መስከረም 25 ቀን 1964 ሞዛምቢክ ውስጥ ገብተው የጥበቃ ካምፕ በማጥቃት የነፃነት ትግሉን ጀመሩ ። ወዲያው የደፈጣ ተዋጊው ቡድን አዛዥ ሆኑ ፤ ቀጥሎም የነፃ አውጭ ንቅናቄው ፕሬዚዳንት ተባሉ ። ማሼል በጦር ሜዳም ሆነ በፕሬዚዳንት ቢሮአቸው ጠንካራ ዲሲፕሊን ያላቸው ታታሪ ሰው ሲሆኑ ከሌላውም ሰው ይህንኑ ባህርይ ይፈልጋሉ ።

ከጦርነቱ በኋላ ማሽል ከፖርቱጊዞች'ጋር ስምምነት አድርገው

እንዳበቁ በታንዛንያ እረፍት ማድረግ መረጡ ። ምክንያቱም የተዋጊ ቡድናቸው የፍሬሊሞ ዋና መሥሪያ ቤት በዚያ ስለነበረ ነው ። ሌሎች የነፃነት ንቅናቄ መሪዎችም በዚያ ነበር የሚተላለፉት ። ሆኖም ማሼል በአሥራ አንድ ሰዐት ተኩል ይነሱና ተከታዮቻቸውን ቀስቅሰውና አስከትለው የአሥር ማይልስ ሩጫ ያደርጋሉ ። ከዚያም ይሰበሰቡና ሂስና ግለሂስ ይለዋወጣሉ ። ማታ ደግሞ ከተለያዩ የነፃነት ንቅናቄ መሪዎች ጋር ስለወደፊቱ የሮዴሽያ (ዚምባብዌ) እና የደቡብ አፍሪካ ዕድል ይወያያሉ ። "ማሼል ከድል በኋላም አላረፉም ፣ ድካማችንን ሳና ቃልል በዚህም በዚያም ወጥረውን ስንሯሯጥ ነው የሰነበትነው" አለ አንድ ተከታያቸው ።

ማሼል ከሌሎች የአፍሪካ መሪዎች የሚለዩበት ይኸው ነው ፤ የተግባር ሰው ናቸው ። አሥር ሚሊዮን የሚሆነውን ሕዝባቸውን የሚመሩት በተግባር ነው እንጅ በቃል አይደለም ። የተንደላቀቀ ኑሮና የግል ገናና ስም አይሹም ። ሀብት አያጓጓቸውም ። ስለዚህ በሞዛምቢክ ምዝበራ የለም ። ማሼልም በየጊዜው እየተዘዋወሩ ፋብሪካዎችን ፣ እርሻዎችን ፣ ሆስፒታሎችን ፣ እሥር ቤቶችን ወዘተ በመጐብኘት የሕዝቡን አስተያየት በማስታወሻ ያሰፍራሉ ። "የሕዝቡን የልብ ትርታና የሀገሪቱን ትኩሳት ማወቅ ያስፈልጋል ፤ መለኪያው ቴርሞሜትር ደግሞ ሕዝቡ ራሱ ነው" በማለት ይናገራሉ ።

ጢማቸውን ያንዠረገጉትና ለአምስት ሰዐት ያህል ያለማቋረጥ መናገር የሚችሉት እንደበተ ርቱዕ ሰው ሳሞራ ማሼል ሲጋራና መጠጥ አይወዱም ፣ ዳንስና ፓርቲ በሚወዱ ሰዎችም ያሾፋሉ ፣ ለአብዮቱ ሊመደብ የሚገባውን ጊዜና ጉልበት ማባከን ነው ባይ ናቸው ። በአንድ የሜይ ዴይ (ዓለምአቀፍ የሠራተኞች ቀን) በዐል ላይ ባደረጉት ንግግር ፤ ፀጉራቸውን የሚያሳድጉ ወጣት ወንዶች እንዲላጩና አጣብቂኝ ሱሪና ስስ ሸሚዝ የሚለብሱ ሴቶች ይህን ከማድረግ እንዲታቀቡ ትዕዛዝ ሰጡ ። ይህን የሚያስፈጽሙ "የአብዮቱ ታማኝ ቡድኖች" ተሠማሩ ። የእነዚህ ወጣቶች አለባበስ ከዓላማ የሚያዘናጋና ሌላ የሚያሳስብ ነው በማለት ነቀፉ ። ቤተክርስቲያንም የኢምፔሪያሊስቶቹ መሣሪያ በመሆን ተቃዋሚዎችን የምታፈራና የሃይማኖት ሽፋን



እየሰጠች የምታሠማራ ናት ሲሉ ከሰሱ ። አንድ ቀን የቤተክርስቲያን ሰባኪ ከሆኑት አባታቸው ጋርም በዚሁ ጉዳይ ተጣልተው ማሼል ተናደው በመጮህ በሩን በኃይል በመዝጋት ተቆናጥረው ወጥተው ሄደዋል ። በአፍሪካ ቤተሰብ ውስጥ በታላቆች ላይ ይህን የመሰለ ባህርይ ማሳየት አክብሮት የጐደለውና ያልተለመደ ነው ።

የማሼል ቢሮ ይህን ያህልም ውድ ዕቃዎች የሞሉበት አይደለም ። ጥቂት ወንበሮችና ሁለት መሣሪያ የያዙ ልጆች ፎቶግራፎች ብቻ የሚታዩበት ነው ። ማሼል አጭርና ጡንቻቸው የፈረጠመ ሰው ናቸው ። ለሕዝብ ከሚያደርጉት ያዘው ግደለው ንግግር ውጭ በግል ሲያወጉ ብስለት የሚታይባቸውና ምሁራዊ አመለካከት ያላቸው ናቸው ። በቢሮአቸው ለሚያነጋግራቸው ሰው በርጋታና በተመስጦ ስለአብዮቱ ያወሩለትና የሚያስደንቃቸው ነጥብ ላይ ሲደርሱ ከመቀመጫቸው ፈንጠር ብለው ይነሱና ዞረው መጥተው የእንግዳቸውን ጉልበት በመነካካት ሀሳባቸውን አጠንክረው ያስረዳሉ ።



ሳሞራ ማሼል

"ስለገበሬዎች አምራቾች መንደር የምንዘምረው ዜማ አለ' ይላሉ ። "ረሀብ ድል ስለተመታበት መንደር ፣ ተንኮል ስለሌለበት፣ ወንጀል ስለማይፈጸምበት ፣ በሽታ ድል ስለተነሳበት ፣ ሕይወት የጋርዮሽና ምርታማ ስለሆነበት ፣ ትምህርት ቤቶች ድንቁርናን ፣ ማይምነትንና ኢሳይንሳዊ አስተሳሰብን ስለሚያጠፉበት ፣ አዲሱ ሰው ስለተወለደበት ፣ የሁሉም ጎሳ ሰዎች እውነተ'ኛ አንድነት ስለሚታይበት. . .' በማለት በተመስጦ ይናገራሉ ።

ማሼል አላሚ ናቸው ፤ ሕልማቸውም ትልቅ ነበር ። መላው የሰው ልጅ ነፃ እንዲወጣ ይፈልጋሉ ። ሁሉንም ያነፃነት ንቅናቄዎች ይደግ

ፋሉ ። ሀገራቸው ነፃ ስትወጣ 640,000,000 ዶላር ዕዳ ስለነበረባቱ የተረከቡት በኢኮኖሚ ሽባ የሆነች ሀገር ነበር ። ወዲያውም አዲሱን ሶሻሊስት ሰው ለመፍጠር ፣ የሕዝቡን የፖለቲካ ንቃት ለማሳደግ ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን ለማሟላት ጥረት አደረጉ ። የሞዛምቢክ የሶሻሊዝም ሕልም ይሳካ እንደሆነ ወሳኙ የማሸል ማንነት ነው ። የመንግሥት አመራር መስጠት የደፈጣ ውጊያ እንደማካሄድ አይቀልም ።

ማሸል የሚደነቁበት ብዙ ቁምነገር አለ ። እንደ ሙአመር ጋዳፊ አብዮት ከውጭ አልኮረጁም(አላስመጡም) ። አገራቸው የሚያስፈልጋትን የቅድሚያ ትኩረት ተግባራት ተገንዝበዋል ። ከነፃነት በኋላ የትምህርት ዕድል ያገኙት ወጣቶች ቁጥር በሶስት እጥፍ አድጓል ፤ የሕዝቡ ግማሽ የኮሌራ ክትባት አግኝቷል ፤ ለማኝና ሴተኛ አዳሪ በዋና ከተማዋ ማፑቶ አይታይም ። ማሸል ከደቡብ አፍሪካ ጋር በግልጽ የንግድ ልውውጥ ያደርጋሉ ። ምዕራቡ ስላልተቀበላቸው ከሶቬዬት ጋር በቅርብ ተባብረው ይሠራሉ ፣ ግን የሶቭዬት ጭራም አልሆኑም ። ርዳታ ከሚሰጣቸው ሁሉ ለመቀበል የሚያቅማሙ አልነበሩም ።

ነገር ግን ማሸል ሙጭጭ ብለው የያዙት አንድ እምነት ነበር ። "አንድ መደብ ፍላጐቱን ለማስፈጸም ተጽዕኖ ሲያደርግ ይህን እሻፈረኝ የሚሉት በጀ እንዲሉ መገደድ አለባቸው ። ይህን የሚቃወሙ መጨቆን አለባቸው" ሲሉ ይናገራሉ ።

እንዲህ ዓይነቱ አባባል ለአቋም ማሸጋሸግና ለፖለቲካ መቻቻል ብዙም ቦታ አይሰጥም ። በዚህም ምክንያት አፍሪካን ወደ ሃያ አንደኛው ምዕት ዓመት ለመምራት ከሚችሉ ፕሬዚዳንቶች ውስጥ ሊዳመሩ አይችሉም ። በመጭዎቹ ዘመናት አፍሪካ የበለጠ ልዩነቶችን የማቻቻል ፣ የሕዝብን ፍላጎት የማክበር ሁኔታ ያስፈልጋታል ።

ማሸል ብዙ ቢጥሩም ሞዛምቢክ በ1984 በአስከፊ ሁኔታ ላይ ነበረች ። ማርክሲዝም ዕድገቷን አላፋጠነም ፣ ይልቁንም ልክ እንደታንዛንያ የኋሊት አስሄዳት ። የኢኮኖሚ ማበረታቻ ስለሌለ የሕዝቡ



ምርታማነት ቀነሰ ፣ የዳቦ ሰልፍ እየረዘመ ሄደ ። ከነፃነት በኋላ የእርሻ ምርት ሰባ በመቶ ቀነሰ ፣ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ከአቅማቸው ሰላሣ በመቶ ያህል ብቻ ሆነ ። የቱሪስቶች መቅረትም በዚያ ታገኝ የነበረውን በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ አነጠፈው ።

በተጨማሪም የቁጥጥሮችና የገደቦች መብዛት ሁሉን ነገር አንተተው ፤ ሕዝቡንም አማረረው ። አንድ የሞዛምቢክ ዜጋ መኖሪያውን ለመቀየር ብዙ የፈቃድ ወረቀቶች ከየሥፍራው ማቅረብ አለበት ። ወደ ክፍለሀገር በአውሮፕላን ለመሄድ ቲኬት ለመግዛት ከኢሚግሬሽን የይለፍ ፈቃድ ማስወጣት አለበት ። ይህንንም ለማግኘት ብዙ ይጉላላል ። ሠራተኛ ለመቅጠር አንድ መሥሪያ ቤት ከአምስት የሠራተኞች ኮሚቴዎች ፈቃድ ማግኘት አለበት ። ይህም አሰልቺና አላስፈላጊ ነው ።

"ታሪክ ወደፊት የትውልዳችን መሠረታዊ አስተዋጽኦ አድርጎ የሚዘግብልን የጠመንጃ ትግሉን ወደ አብዮት መለወጥ መቻላችን ነው" በማለት ማሸል ይናገራሉ ። "አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት አዲስ አስተሳሰብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ መገንዘባችንም የሚናቅ አይደለም" ባይ ናቸው ።

ነገር ግን የለውጥን አስፈላጊነት መገንዘብና ያንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥልት ማወቅ የተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች መሆናቸውን ውለው አድረው ሳይረዱት አይቀርም ።

የሱዳንን ሁኔታ ስንመረምር ደግሞ ብዙ አስገራሚ ሁኔታዎች ያጋጥሙናል ። ሰሜን ሱዳን አረባዊ ሲሆን ደቡብ ክርስቲያን ነው ። ደቡቡ ድሀና እጅግ የተረሳ ኋላቀር ነው ። የኢኮኖሚና የባህል ልዩነቶች ብዙ ዘመን እርስ በርስ አቆራቁሰውታል ። የአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ያለመተማመንና ደም መፋሰስ አስከትሏል ። በ1955 የተጀመረው የአሥራ ሰባት ዓመት ጦርነት ለደቡብ የራስ ገዝ መብት አስገኘለት ። ጦርነቱ ብዙ ባይወራለትም የ400,000 ዜጐችን ሕይወት ቀስፏል ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ለስደት ዳርጓል ።

ከታዋቂው የደቡብ ሱዳን ደፈጣ ውጊያ መሪ ከጋራንግ ጋር

በጁባ በሚገኝ የሆቴል በረንዳ ላይ ተቀምጠን ስናወጋ ምሽት ተቃረበች ። በአንድ በኩል አረብኛ የሚነጋገሩ ሰዎች አጠገባችን አሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዲንቃስ በሚል ስም የሚታወቁት አፍሪካውያኑ ከብት አርቢዎች ወደተለመደው የምሽት ስብሰባና ዘፈን እንቅስቃሴያቸው ሲያመሩ ተመለከትን ። ሁለት የተለያዩ ዓለማት ፣ ሁለት የተለያዩ ባህሎች ፣ ሁለት የተለያዩ ሃይማኖቶች በአንድ ሀገር አብረው እንዲኖሩ ተደርገዋል ። አረቦችና አፍሪካውያን አብረው ተቻችለው ለመኖር ችለዋል ። ኒሜሪ ለጊዜው ለደቡቡ የራስ ገዝ መብት በመስጠት እርቀሰላም አወረዱ ፤ በኋላስ?

በአንድ ሰው በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሰላም ዘላቂነት የለውም ። ኒሜሪ ለጊዜው በሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እሥረኞችን ፈቱ ፤ ለተቃዋሚዎቻቸው ሁሉ በውጭ ሀገር ላሉት ሳይቀር ምህረት ማድረጋቸውን አወጁ ።

ኒሜሪ ሌሊት ሌሊት እንቅልፍ ሲያጡ ሊነጋጋ አካባቢ በቤተ መንግሥቱ በጓሮ በር ይወጡና በእግራቸው በሱዳን ዋና ጐዳናዎች መንሸራሸር ይጀምራሉ ። ጥቁር ዓባይና ነጭ አባይ ወደሚገናኙበት ድልድይ ይሄዱና በአረቦች ሥነግጥም ውስጥ "በታሪክ ረጅሙ መሳሳም" በሚል የሚጠቀሰውን የሁለቱ ወንዞች መገናኛ ሥፍራ በአንክሮ ይመለከታሉ ። ከዚያም ሲነጋጋ አንዳንድ ሰዎችን እግረመንገዳቸውን ስለሱዳን ያላቸውን አስተያየት ይጠይቃሉ ።

ኒሜሪ የጀኔራልነት ማዕረግ አላቸው ። ጠላቶቻቸውን ለመከታተል የስለላ መረብ ዘርግተዋል ። በ1975 ሊገለብጧቸው የሞከሩትን በሊቢያ የሰለጠኑ ዘጠና ስምንት ጥቁሮች በፍርድ እንዲገደሉ አዘዙ ። በ1983 በጁባ የአመፁ ወታደሮችን ታማኞቻቸው ድባቅ ከመቱ በኋላ አማፂዎች በስድስት በስድስት እየተወሰዱ በጥይት እንዲደበደቡ አደረጉ ። የአንድ ፓርቲ አመራር ብቻ በሱዳን እንዲኖር በማዘዝ በጋዜጦች በሬዲዮና ቴሌቢዥን ላይ ጥብቅ ቁጥጥር አጠነከሩ ።

ኒሜሪን ከሌሎች የአፍሪካ መሪዎች ልዩ የሚያደርጋቸው አቅጣጫዎችን ለመለዋወጥና ለመሞከር ፈቃደኛ መሆናቸው ነው ። ሌሎች ሥልጣናቸውን ሲያጠናከሩ እሳቸው ለማካፈል ፈቃደኛ



በመሆን ለደቡብ ራስ ገዝ ፈቀዱ ። ሌሎች የአፍሪካ መሪዎች ለችግሮቻቸው ሁሉ ቅኝ ገዢዎችን ሲኮንኑ እሳቸው ግን ብዙው ችግር ከቤታቸው መሆኑን ይቀበላሉ ። በአንድ ወቅት የሶቪዬት አፍቃሪ በመሆን የማምረቻ ተቋሞችን ወረሱ ፤ በኋላ ደግሞ ሶቪየቶች ሊያስገለብጧቸው በ1971 በመሞከራቸው በቶሎ አፈነገጡና የግል ሀብት ማፍራትንና በልማት መሳተፍን ፈቀዱ ። የኢኮኖሚ ተቋሞችን መውረስ ልማትን እንዳዳከመ በመረዳት ከአረቡ ዓለምና ከምዕራቡ ዓለም ባለሀብቶች እየመጡ ያለገደብ ልማት እንዲያካሂዱ አደረጉ ። ይህም ሆኖ ቢሮክራሲው የተንዛዛና ቅልጥፍና የሚጎድለው ፣ እርሻውም ኋላቀር ፣ የደቡቡም ሁኔታ አንድ ቀን ሊፈነዳ የሚችል ሆኖ ቀረ ።

በኋላም ምንም ይምጣ ምንም ኒሜሪ ለሀገራቸው የእርቅን ጥቅም ስላሳዩ ሕዝቡ ይህን ትምህርት በመውሰድ ወደ ማህበራዊ ፍትሕና ዲሞክራሲ ሊያመራ ይችላል ። ይሁን እንጂ አንድ የምዕራብ ጋዜጠኛ አፍሪካ ሲደርስ ማወቅ ያለበት በአፍሪካ ወደፊት እንዲህ ይሆናል ብሎ መተንበይ የማይቻልና ብዙ ጊዜ ያልታሰበው የሚደርስ መሆኑን ነው ። ለማንኛውም ኒሜሪ የእርቅን ጥቅም በማሳየታቸው የሚረሱ አይደሉም ። አፍሪካም የሚያስፈልጋት እንዲህ በእርቅ የሚያምኑ መሪዎች ናቸው ።

ምዕራፍ አራት

# የኢዲ አሚን አሰቃቂ ድርጊቶች

"ሒትለር ስለአይሁዶች ልክ ነበር ፣ ምክንያቱም እሥራ ኤሎች የሚሠሩት በዓለም ሕዝብ ፍላጐት አኳያ አይደለም ፤ ለዚህም ነው እሥራኤሎችን በጀርመን ምድር ከነነፍሳቸው በጋዝ ያቃጠላቸው ።"

ኢዲ አሚን
የቀድሞው የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት

ጥር 25 ቀን 1971 በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን በፕሬዚዳንታቸው በሚልተን አቦቴ ከሥልጣን መወገድ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጥ በሰልፍ ወጥተዋል ። መጠጥ የሚወዱት አምባገነን መሪ አቦቴ አገሪቱ ነፃነቷን ካገኘች ጀምሮ በሥልጣን ላይ ቆይተ ዋል ። የግልበጣው ዋና ተዋናይ በአፍሪካ እንደተለመደው በአንድ ወቅት የፕሬዚዳንቱ የቅርብ ታማኝ የነበሩ ናቸው ። በጦር ሠራዊቱ ውስጥ እድገት እያገኙ የመጡና ከፖለቲካና ከርዕዮተዓለም ራሳቸውን አግልለው የቆዩ መኮንን ናቸው ። ጄኔራሉ ለሀገሪቱ ሕዝብ መጀመሪያ ባደረጉት ንግግር "ወታደር እንጅ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም ፤ ስለ ዚህም ብዙ መናገር አልችልም ፤ በሥራ ዘመኔ ሁሉ ንግግሬ በአጭሩ ነበር" አሉ ። ወዲያውም መንግሥታቸው ባለአደራ መንግሥት እንደ ሆነና ምርጫ እንደተዘጋጀ ሥልጣን ለሲቢል መንግሥት እንደሚያ ስረክቡ ቃል ገቡ ። የኡጋንዳ ሕዝብ ትልቅ እፎይታ ተሰማው ። ጐረ ቤት አገሮችም ዋስትና ተሰጣቸው ። ምዕራቡ ዓለም ተደሰተ ። እነዚህ

አዲስ መሪ ኢዲ አሚን ፊጋ ያሉ ጨዋ ፕሬዚዳንት ይሆናሉ የሚል ስሜት በሁሉም ላይ አደረ ።

ኢዲ አሚን በዚያን ጊዜ የአርባ ስድስት ዓመት እድሜ የነበራቸው ፣ ክምር የሚያክሉ ፣ ቀልዳቸው ሁሉ ድርቅ ያለና የማይጥም ነበረ ። የሁለተኛ ክፍል ትምህርት የነበራቸውና ከጎሳቸው ቋንቋ በስተቀር አውቃለሁ የሚሏቸውን ሌሎች አምስት ቋንቋዎች እያወለጋገዱ የሚንተባተቡ ነበሩ ። በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ቀድሞ አለቃቸው የነበሩት እንግሊዛዊ ኮሎኔል ሮጀርስ የሚያስታውሷቸው ኢዲ አሚን "እምነት የሚጣልባቸው ወታደርና አይከፋሽ ጉልበተኛ ሰው" ነበሩ በሚል ነው ። ሌሎቹ የሚያውቋቸው ደግሞ የሥልጣን ምኞት የሌላቸውና የማያስመስሉ ግልጽ ሰው ብለው ይናገሩላቸዋል ። ሁሉም ያላወቀው ግን ኢዲ አሚን በአፍሪካ አደገኛ መሪ ሊሆኑ የሚችሉበት ተፈጥሮ እንደነበራቸው ነው ። የተፈጥሮ ባህርያቸው በጣም ኋላቀር ፣ ጉቦኛና ግግም ያለ የወታደር ጠባያቸው የሚያይልባቸው ሰው ነበሩ ።

ሥልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ በኡጋንዳ እንግዳ ጉዳዮች መከሰት ጀመሩ ። መጀመሪያ የቅርብ ተፎካካሪያቸው የነበሩት የጦሩ ኤታማዦር ሹም ብርጌዴር ጄኔራል ሱሌይማን ሁሴይን የት እንደ ደረሱ ሳይታወቅ ተወገዱ ። የኡጋንዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቤኔዴክቶ ኪዋኑካ በችሎት ላይ እንዳሉ የአሚን ወታደሮች መጥተው እያዳፉ ወሰዷቸውና ከዚያ በኋላ በሕይወት አልታዩም ። የማካሬሬ ዩኒቨርስቲ ምክትል ቻንስለርም የደረሱበት ሳይታወቅ ቀረ። የአሚን የግል ሐኪም የነበሩት ሰው በዱላ ቀወግረው ሞተው አስከሬናቸው ከመንገድ ዳር ተጥሎ ተገኘ ። የተገደሉ ሰዎች ወደ ነጭ አባይ ወንዝ እየተጣሉ ኖሮ ራቅ ብሎ ማቢራና ናማንቬ ወደሚባሉ ሜካዎች አካባቢ በመቶ የሚቆጠር ሬሳ እየተንሳፈፈ መታየት ጀመረ ። እሥር ቤቶች በእሥረኞች ሞሉና ማሰሪያ ቦታ ስለጠፋ እሥረኞቹ ራሳቸው በተራ ተሰልፈው አንዱ ሌላውን በመዶሻ ቀጥቅጦ እንዲገድል እየታዘዘ ተጨፋጨፉና የመጨረሻው ሰው ሲቀር በጥይት ተገደለ ። አቦቴን ይደግፉ የነበሩ የላንጎና የአኮሊ ጎሳዎች በሙሉ ታረዱ። በየማታው በአሚን ፖሊስ ጣቢያዎች በድብደባ የሚገደሉ ሰዎች



የጣር ድምፅ በአካባቢው የሚኖሩትን ሰዎች እንቅልፍ ነሳ ፤ አሸበራቸውም ። በዚህ ሁኔታ የተቸገሩት የፈረንሣይ አምባሳደር አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰሚ አላገኙም ፤ ባለቤታቸውም ለብዙ ሌሊቶች በተከታታይ እንቅልፍ አጥተው መኖር ስላልቻሉ ወደ ፓሪስ ተመለሱ ። ካቢኔ ሚኒስትሮች ፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ፣ ክርስቲያኖች ፣ አይሁዶች ፣ እስያውያን በሙሉ (የአሚን የቅርብ ወዳጆች ከሆኑ እስላሞችና የካክዋስ ጎሳዎች በስተቀር) በሥልጣን ያበዱ ሰው ባቀጣጠሉት የበቀል እሳት ተለበለቡ ። እኒህ ሰው የተጠናወታቸው በሽታ የኡጋንዳን ምሁራን በሙሉ በመጨረስ አገሪቱን እሳቸው ወደአሉበት ዝቅተኛ ተራ ሰውነት ደረጃ ማውረድ ነበር ።


ኢዲ አሚን ዳዳ

ኡጋንዳውያን ይህን መዐት አሚኒዝም ብለው ሰየሙት ። በ1979 አሚኒዝም ሲያበቃ 300,000 የኡጋንዳ ዜጎች ተገድለዋል ። ተግባሩ የካምቦዲያው ፖልፖት ያደረገው ዓይነት ነው ። በዚህ ሂደት ሞት እየተለመደ ስለሄደ ኡጋንዳውያን በድርጊቱ መሳቀቅ አቁመው ሞትን እንዴት አምልጠው በሕይወት ለመኖር እንደሚችሉ ብቻ ነበር የተማሩት ። በኡጋንዳ የሚኖር አንድ ባለግሮሰሪ እንደነገረኝ "ወንድምህ በፖሊሶች ተወሰደ ከተባለ እንዳለቀለትና እንደማይመለስ ታውቃለህ ፤ ያሳዝናል ብለህ ለጥቂት ቀናት ታዝንና ሥራህን ትቀጥላለህ" በማለት አጫወተኝ ። አንድ አውሬ የሆነ ሰው እንደ ድመት እየተጫወተ ፣ እንደ አንበሳ እየተቅለሰለሰ አሥራ ሶስት ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባትን አገር ገደላት ።

ከስምንት ዓመታት በኋላ አሚን ሲገለበጡ ሕዝቡ ደስታውን ለመግለጥ ዳግም በሰልፍ ወጣ ። የድሮ ጓደኞች በደስታ እየተቃቀፉ "አለህ እንዴ? ተርፈሃል?" እየተባባሉ ተቃቀፉ ። ከቅዠት ዓለም ተገ

ላገሉ ። የፖለቲካ እውቀት ሳይኖራቸው የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት የሆኑት አሚን ፣ የሰለጠነ ወታደር መኮንን ሆነው ተራ ነፍሰ ገዳይ የሆኑት ኢዲ አሚን በታንዛንያ ጦር እየተረዱ በገቡት አማፂያን ተባረው ወደ ሊቢያ ፈረጠጡ ። ደስታቸውን ለመግለፅ በፓርላማው ሕንፃ ዙሪያ እየደነሱና እየዘፈኑ የሚቦርቁትን ኡጋንዳውያን ስመለከት አገሪቱ ዳግም የተወለደች መሰለኝ ። ለዩጋንዳና ለአፍሪካም መልካም ስሜት አደረብኝ ። አንድ አፍሪካዊት ሀገር የግል ምኞትንና የጉሳ ጥርጣሬን ወደጎን የመተው ዕድልና ለዚያም በቂ ምክንያት አግኝታ የትውልድ ቅርስን እንደገና ለመገንባት የምትችል ቢሆን ኖሮ ኡጋንዳ ይህን አጋጣሚ አገኘች ።

ሚያዝያ 11 ቀን 1979 ፀሐይዋ ደመናውን ጥሳ ወጥታለች ። ከፓርላማው ሕንፃ ጥላ ሥር አንድ አዛውንት ብቅ ብለው መነፅራቸውን አወለቁና የተሰበሰበው ሕዝብ በኢዲ አሚን እጅ ለወደቁት የሕሊና ፀሎት እንዲያደርግ በመጠየቅ አንገታቸውን ደፉ ። ሁሉም ፀጥ በማለት የሕሊና ፀሎት አደረሰ ።

ዮሱፍ ሉሌ የሽግግር ፕሬዚዳንት በመሆን ቃለ መሐላ ለመፈጸም እንደተዘጋጁ ሕዝቡን በዓይናቸው ቃኙና በቀስታ መናገር ጀመሩ ፤ ድምፃቸው እየተርገበገበ “አስፈሪው ጊዜ አልፏል” አሉ ። “በአሚን መወገድ የብሔራዊ ዕርቅ ዘመን ተጀምሯል” በማለት አበሰሩ ። በስደት ይኖሩበት ከነበረው ከለንደን የመጡት ሉሌ ንግግራቸውን ጨርሰው ከደረጃው ሲወርዱ ሕዝቡ በደስታ ሲቃ መጮህና መሳሳም ጀመረ ። የታንዛኒያ ወታደሮችን ተሸክመው መቦረቅ ጀመሩ ። ከዚያም አታሞ ድለቃ ተጀመረ ። ወዲያው የቤተክርስቲያን ደወሎች የደስታ ደወል ማንቃጨል ጀመሩ ። በመላ ካምፓላ የደስታ ድምፅ አስተጋባ ። የዩጋንዳ ደፈጣ ተዋጊዎች መሪ ዴቪድ ኦያቴ አጀክ ጠመንጃውን በእጁ ከፍ አድርጎ እንደያዘ ሕዝቡ ተሸክሞት ከአንዱ ትካሻ ወደሌላው ያሸጋግረው ጀመር ። በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ አዲሱን የኡጋንዳ ብሔራዊ መዝሙር ማስተጋባት ጀመረ ። “ኦ ፣ ዩጋንዳ የነፃነት ምድር ፣ ፍቅራችንንና ጉልበታችንን እንሰጥሻለን ...“በማለት ቀጠሉ ።



አንድ የቀድሞ የካምፓላ ማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ራገርድ ካዋዋ እንዲህ አለኝ ። “አሁን አሚንን እዚህ ብናገኘው ጥሬ ሥጋውን ነበር የምንበጫጨቀው ። ሰው በላ ስለነበር የምናደርገው ይገባው ነበር ።”

የአሚን መኖሪያ ቪላ ከፓርላማው አንድ ማይል ርቆ ኮረብታው ላይ ይታያል ። በተከታዩ ቀን ወደዚያ ሄድሁ ። በመኝታ ቤታቸው ግድግዳ ላይ ሕፃን እንደሚያደርገው የጦር አውሮፕላን ለጥፈዋል ። በአሚን አልጋ ሥር በካርቱኖች ሙሉ የእጅ ቦምቦች ታጭቀዋል ። ለቢሮ በሚጠቀሙበት ክፍል ውስጥም ለአባለዘር በሽታ የሚሆኑ ከኒኖች ተቀምጠዋል ። የፋይል ካቢኔታቸው በተገደሉ ሰዎች ፎቶግራፍ ተሞልቷል ። በተደበደቡና አካላቸው በተቆራረጡ ሰዎች ፎቶግራፎች ተሞልቷል ። የተደበደቡና አካላቸው የተቆራረጠ ሰዎች ፎቶግራፎች የሚዘገንኑና ሰው መሆናቸውን ለመለየት የሚያዳግቱ ናቸው ። የአሚን የሐኪም መረጃዎች ወለሉ ላይ ወድቀዋል ። የመጋጠሚያዎች ሕመምና አለመጠን የመወፈር በሽታ እንዳለባቸው ይገልጣሉ ። “ከፍተኛ የአካል እንቅስቃሴ ያስፈልግዎታል” የሚል የሐኪም ምክር ይገኝበታል ። ያልተከፈቱ አያሌ በፖስታ የታሸጉ ደብዳቤዎች ተከምረዋል ። ከተለያዩ መንግሥታትና በውጭ ካሉ ኤምባሲዎቻቸው የተላኩ ናቸው ።

በዋሽንግተን የአሚን አምባሳደር የነበሩት የሕክምና ዶክተር ሶሎሞን አሴያ ሲያጫውቱኝ ፤ “ከሕክምና አኳያ አሚን እብድ ናቸው ማለት ይቻላል ። ባህሪያቸው ዥጉርጉር ነው ። አሁን አንድን ሰው ገድለው በደቂቃ ውስጥ እየሳቁ ጊታራቸውን ይጫወታሉ ። ከደቂቃ በፊት ያደረጉትን አያስታውሱም ። በሕክምና አንፃር ሲታይ ለሰሩት ብዙ ነገር ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ። ታካሚ እንጅ ፕሬዚዳንት መሆን የሚገባቸው አልነበሩም” ብለዋል ።

የኡጋንዳ ደስታ ብዙ አልቆየም ። በሚያሳዝን ሁኔታ ወዲያው አሳዛኝ ሕይወት ቀጠለ ። በምንም ተዓምር በኡጋንዳ እርቅና ግንባታ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ሆነ ። አንድ የቅዠት ዘመን አብቅቶ ሌላው የቅዠት ዘመን ሊጀመር ነው ። ኡጋንዳ አሚን የጀመረውን የጥፋት ተልእኮ ለመቀጠል ቆርጣለች ።

ኡጋንዳን ለማዳን የመጣው የታንዛኒያ ጦር ዘረፋ ጀመረ ። ደመ
ወዝ ያልተከፈላቸው ወታደሮች በጠመንጃ እያስፈራሩ ሕዝቡን መዝ
ረፍ ቀጠሉ ። ወዲያው ሁሉም ወታደር ባለ ሰኮ ሰዐትና ባለሬዲዮ
ሆነ ። ኢኮኖሚው ተንኮታኮተ ፣ የምግብ እህል ጠፋ ፣ ረሀብና ሞት
አንዣበበ ። ደሀና ሰዎች ሁሉ ሌባ ሆኑ ፤ የዩጋንዳ ዱርዬዎች በከተ
ሞች እየተዘዋወሩ በመግደልና በመዝረፍ መኖር ጀመሩ ። ዲፕሎማ
ቶች ሳይቀር ጠመንጃ ፣ ቦምብና አዳኝ ውሾች በማዘጋጀት ከሌቦች
ራሳቸውን መከላከል ያዙ ። ሥርዓት አልበኝነት ስለሰፈነ የቀባበ
ሩት መንግሥታት ተወካይ የነበረው ማትስ ሉንግሬን አውቶማቲክ
ጠመንጃዎች የታጠቁ ዘቦችን ለግቢው ጥበቃ መደብ ። የሮማ ካቶ
ሊክ ቄስ ዮሴፍ ባራጎቴ ምሽግ አስርቶ ስላሳ ስምንት ካሊበር ድግን
መትረየስ አጉርሶ ጥበቃ ጀመረ ።

የማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ማስተማሩን ትተው የሚበላ
ምግብ ፍለጋ ይውሉ ጀመር። ሆስፒታሎች ለሕመምተኞች የሚሰ
ጡት መድኃኒት ጠፋ ፣ ማደንዘዣ ስለሌለ ቀዶ ሕክምና ቆመ ። የእ
ስቾኢይ ርዳታ መድኃኒትና ምግብ ወደ ኡጋንዳ መጉረፍ ጀመረ ።
ነገር ግን በመኪና ለማሠራጨት ሲንቀሳቀሱ ይዘርፉ ጀመር ። በተ
ለይ በሰሜን ዩጋንዳ ድርቅና ረሀብ የፈጃቸው ሕፃናት በየቀኑ ስለሚ
ጣሉ ጅቦች ወፈሩ ፤ አድኖ መብላትም ሆነ በአንድ ሙታን ሥጋ
መጣላት አቆሙ ። በሰሜን ያሉት ካራሞጆንግ የሚባሉት ጐሣ ዎች
ሴቶች ልጆቻቸውን በከብት የመለወጥ ባህል ስላላቸው የተገኘውን
ምግብ ሁሉ የሚሰጡት ለልጃገረዶቹ ሆነና ወንዶቹ በብዛት በረሃብ
ያልቁ ጀመር ።

በሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን ምሁራን ለፕሬዚዳንት ሉሌ
ጥሪ ምላሽ በመስጠት በስደት ከሚኖሩባቸው የአሜሪካና የአውሮፓ
አገሮች በመምጣት ሀገራቸውን ለመገንባት ተነሳሱ ። ግን ሥራው
ከባድ ሆነባቸው ፣ በመጨረሻም ችግሩ አሸነፋቸው ። ሕጋዊነት
የማይታይበት ጫካ በቀል ሥርዓት ኡጋንዳን እንደገና ፅልመት
አጠላባት ። የሀገር ጉዳይ ደበዘዘ ፣ የግል ሩጫ ሰፈነ ፣ ከውጭ የተመ
ለሱት ምሁራንም ሥልጣን በያዙ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ምዝ



በራ ጀመሩ ። ለርዳታ የመጣውን ገንዘብ ይከፋፈሉት ገቡ ። ሁሉም
ሕዝባችን የሚሉትና የሚቆረቆሩለት የኡጋንዳ ሕዝብ ሳይሆን የየ
ጐሳቸው አባላት ብቻ እንደሆኑ በተጨባጭ ታየ ። ሁኔታዎች እየተ
ሻሻሉ ነው የሚል አስተያየት ሲሰጡም የኡጋንዳ ኢኮኖሚ ተጠና
ከረ ማለታቸው ሳይሆን በውጭ የከፈቱት የባንክ ሂሳብ ማደጉን ለመ
ጠቆም ነው ።

ዩጋንዳን ለማዳን ዕድል የነበራቸው ሉሌ ነበሩ ። ታማኝና አዋቂ
ከመሆናቸው ሌላ ዕድሜያቸው ስድሳ ሰባት ስለነበረ የሥልጣን ጉጉት
አልነበራቸውም ። በዚህ ላይ በኡጋንዳ ከትልቁና የተሻለ ከተማረው
ጐሣ ስለሆኑ የብዙኃኑ ተቀባይነት ነበራቸው ። ሰብዓዊነት ያላቸው
ከሚሆኑ ይልቅ አምባገነን ቢሆኑ ኖሮ ምናልባት ይሳካላቸው ነበር ።
ነገር ግን ሉሌ በኡጋንዳ የታንዛኒያው ኒሬሬ የሚፈልጉትን ብቻ እንዲ
ያከናውኑ ታዘዙ ። ሉሌ ካፒታሊስታዊ ጎዳና ለመከተልና ነፃ ሆነው
ለአገራቸው የሚበጀውን መናገር ሲጀምሩ ኒሬሬ ከካምፓላ አስጠር
ተው ዳሬሰላም ውስጥ ቤት አዘግተውባቸው ያለስልክ በቁም እሥር
አስቀመጡና ኡጋንዳ አዲስ ፕሬዚዳንት እንደምትሰይም አስታወቁ ።

አዲሱ ፕሬዚዳንት ጎድፍሬድ ቢኒሳ ይባላሉ ። የሕግ ጠበቃ
ሆነው በኒውዮርክ የኖሩና ከጥቂት የፍች ክርክሮች በስተቀር ሌላ ያላ
ስተናገዱ ነበሩ ። ወደ ዩጋንዳ የተመለሱ ሰሞን የውጭ ጋዜጠኞች
አነጋግረዋቸው ነበር ። እሳቸውም ሲጋራቸውን እያቦነኑ ምን ለመ
ሥራት እንደመጡ ግልፅ ዓላማ እንደሌላቸውና ግን ሥራ እንደማያጡ
ተስፋ እንደሚያደርጉ ይናገሩ ነበር ። በተከታዩ ቀን ሥራ ማግኘታ
ቸውንና የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ለመሆን በኮሚቴ መመረጣቸውን ሲሰሙ
እንደማንኛችንም ገረማቸው ። የመጀመሪያ ሥራቸው ያደረጉት አሜ
ሪካዊ የሕዝብ ግንኙነት ድርጅት በአራት መቶ ሺህ ዶላር ቀጥረው
የቱብላሸውን የኡጋንዳ ዓለምአቀፍ ገፅታና ስም ማደስ ነበር ። "ሁሉ
ንም ችግር እናቃልላለን" በሚል በመተማመን የድርጅቱ ኃላፊ
ከዋሽንግተን ኢንቴቤ ገባ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን ራሱን ነቅንቆ
ኡጋንዳ የሚያስፈልጋት የሚያክማትና የሚያድናት እንጅ የሚያ
ስተዋውቃት አልነበረም በማለት ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ወዲያውም ዙሩን ጨርሰው ቢናይሳ እንደገና በኒሬሬ ትእዛዝ ከሥልጣን ተወግዱና ጦር ኃይሉ ሥልጣን ወሰደ ። ኢዲ አሚንም አጃቢዎቻቸው ከሙአመር ጋዳፊ አጃቢዎች ጋር ስለተታኮሱ ከሊቢያ ተባረው ወደ ሳውዲ ዓረቢያ ሄዱ ። ከሁለት ሚስቶቻቸውና ከሃያ ስስት ልጆቻቸው ጋር ወደ ሳውዲ እንደሄዱ "ለሕዝቤ ደህንነት ስል ወደ ኡጋንዳ ለመመለስ ፈቃደኛ ነኝ" ሲሉ አስታወቁ ። በዚሁ ጊዜ ታንዛኒያ የኖሩት ኦቦቴ ለሁለተኛ ጊዜ የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ ተደረጉ ። ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ በተናገሩት ቃል "ዛሬ ደግሞ የዲሞክራሲን አርማ አንስተን ለሕግ ተገዢነትን እናውጃለን" አሉ።

"ያለፈው አልፏል ፤ አዲስ ተስፋ እንጀምር" ሲሉ ተማፀኑ ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ኦቦቴ የሀገር ምርምር ጽ/ቤት የተሰኘውን የአፈና ድርጅት አቋቋሙ ። በተጨናነቁት እሥር ቤቶች ሰዎችን መግረፍና ማሰቃየት እንደገና የተለመደ ሆነ ። ግለሰቦች የት እንደደረሱ ሳይታወቅ እንደወጡ ይቀሩ ጀመር ። አዲስ የተቋቋሙት ጋዜጦች ተዘጉ ፣ የተለየ አስተያየት ያንፀባረቀ የሚጠብቀው ጥይት ሆነ ። የዓለምአቀፍ ቀይ መስቀልና የምዕራብ ጋዜጦች ወኪሎች ተባረሩ ፤ ኡጋንዳ በእርስ በርስ የጎሳ ጦርነት አፋፍ ላይ ወደቀች ። ከካምፓላ ወጣ ብሎ የባጋንዳ ጎሳ አባላት የሚበዙበት የደፈጣ ተዋጊ ቡድን ተቋቋመ ። ወዲያው በመንግሥት ተቋሞች ላይ ጥቃት በመሰንዘር የኦቦቴን መንግሥት ለመጣል ትግል ተጀመረ ።

በረጅም የቅዥት ዘመን የሀገሪቱ ሕዝብ አጠቃላይ አመለካከትና ሥነልቦና ተለውጦ ይሆን?

"አይደለም" አሉኝ ሲገዛ ካጁቢ የሚባሉት የማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ቻንስለር ። በኋላ ጥቂት አሰቡና "መቼም ኡጋንዳ ሞራሉ ሽባ የሆነ ትውልድ አፍርታለች ለማለት ያዳግተኛል ፤ ነገር ግን በሌላ በኩል . . . "አሉና ዝም በማለት ቃላት ሲመርጡ ከቆዩ በኋላ "በሌላ በኩል አሚን በፈጠሩት የሲቃይ ዓለምና ከዚያም በተከተለው ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ ሳያደርብን አልቀረም ። በጣም አዘቅዝቀን ስለ ወረድን ተመልሰን ወደነበርንበት ለማደግ መቻላችንን እጠራጠራለሁ" አሉ ።



ኡጋንዳ ምን ያህል ወደ አዘቅት እንደወረደች ለማጤን የቀድሞውን ሁኔታዎች እንመልከት ። በአንድ ወቅት ዊንስተን ቸርቺል "የምሥራቅ አፍሪካ እንቁ" በሚል የጠቀሷት ኡጋንዳ በእርግጥም የባህር በር ባይኖራትም በአፍሪካ እጅግ ውብ ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ነበረች ። ለምና ደጋማ አካባቢዎች ያሏት ፤ አረንጓዴ ሸለቆዎች ከቪክቶርያ ሐይቅ እስከ ሰሜን ሞቃታማ አካባቢ የተንጣለሉ ነበሩ ። ቪክቶርያ ሐይቅ የነጭ አባይ መመንጫ ሲሆን ሌሎችም ትናንሽ ከእሳተ ገሞራ ፍንዳታ በኋላ ገደላቸው በውሃ የተሞሉ ኩሬዎች ሲኖሩ የተራሮች ዙሪያ በአማረ እርከን ሥራ ተውቦ ነበር ። ከካምፓላ የአንድ ቀን ጉዞ በመኪና ሲወጡ የሚታየው የዱር አራዊት መንጋ ለጉድ ነበር ።

"የኡጋንዳ ውበት ለማመን የሚያስቸግር የምድር ገነት" በማለት ቸርቺል በ1908 በጎበኙት ወቅት አድናቆታቸውን ገልጠዋል ። "ባቡር ላይ ሆነው ሲመለከቱት የሚያስደንቅ አዲስ ዓለም ነው ፤ አገሩም ሕዝቡም ከቀረው አፍሪካ የተለየ ነው"ብለውታል ።

የቀድሞዎቹ የኡጋንዳ ሕዝቦች ጦረኞችና ገበሬዎች በመሆን በአምስት የነገሥታት ክልሎች ማለትም ቡጋንዳ ፣ ቡንዩርሮ ፣ ቡሶጋ ፣ ቶሮ እና አንኮሌ በተሰኙ ሀብታም አካባቢዎች የሚኖሩ ነበሩ ። በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት አማካይ እስከ 1962 ድረስ በኡጋንዳ ቡጋንዳ የተሰኘው ጎሳ አባላት እየበዙና የበላይነት እየያዙ ሄዱ ። ኩሩ፣ የተማሩና ራሳቸውን ከሌሎች ጐሳዎች ማለትም ከባንቱ ፣ ከኒሎቲክ ፣ ከአኮሊና ከላንጎ የተሻሉ አድርገው የሚገምቱ ናቸው ። በንጉሥ (ካባካ) የሚገዙና ከኡጋንዳ ሕዝብ ሃያ በመቶ የሚሆኑ ነበሩ ።

በ1894 ኡጋንዳ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ዋለች ። የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪዎችም "ከፋፍለህ ግዛ" የተሰኘውን የተንኮል መርሀአቸውን ሥራ ላይ በማዋል ባጋንዳ ለተሰኘው ጎሳ አድልኦ ያሳዩ ጀመር። የቅኝ አገዛዝን ፖሊሲ ለማስፈጸም ቀንደኛ ተዋናይ በመሆን በየመሥሪያ [illegible] ቁልፍ ቦታዎች ተሰጧቸው ። ሌሎች ጐሣዎች ለይስሙላ ያህል እንጅ የሚረባ ሥፍራ አልተሰጣቸውም ። ሌሎች ጐሳዎች በቢሮክራሲውና በንግድ ዘርፍም ሳይቀር እርባና ያለው ቦታ ስላላገኙ

ምርጫው እንደተናቁ እንደተገፉ መቅረት ፤ ያለዚያም ሌላ መንገድ
መፈለግ ነበረ ። ስለዚህም አኮሊ እና ላንጊ የተሰኙ ጎሳዎች በውት
ድርና መሰማራት በመምረጥ በቅኝ ገገርው ጦር ሠራዊት ውስጥ ከፍ
ተኛ ቁጥር ያላቸው ሆኑ ።

እንደ ኬንያና ታንዛንያ ሳይሆን ኡጋንዳ ወደ ነፃነት ያመራችው
ብሔራዊ የትግል ግንባር ሳይኖራት ነው ። እንዲያውም ባጋንዳዎች
ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ የበላይነታቸውን የሚያጡ ከሆነ መገንጠልን እን
ዳማራጭ አስበውት ነበር ። ይህ ማዕከላዊ ሥልጣን የማጣቱ ጉዳይ
ወደኋላ ለፖለቲካ መረጋጋት እንቅፋት መሆኑ አልቀረም ። ነገር ግን
ሚልተን አቦቴ ለባጋንዳዎች የራስ ገዝ አስተዳደር እንደሚሰጡ ቃል
በመግባት የብሔረሰቦች ቅንጅት የላላም ቢሆን ሳይበታተኑ ኡጋ
ንዳ ነፃነቷን እንድታገኝ አደረጉ ። አቦቴ የላንጎ ጎሳ ተወላጅ ሲሆኑ ፣
የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆንና የባጋንዳውን ንጉሥ
ፕሬዚዳንት በማድረግ ሥልጣን ተካፈሉ ።

ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ በዚያ የቀሩ ነጮች 8,800 ያህል ብቻ የነ
በሩ ሲሆን እነሱም የቴክኒክ ሰዎች ፣ አስተዳዳሪዎችና ሌሎች ሞያተ
ኞች ብቻ ነበሩ ። ለዚያውም ከሶስትና ከአራት ዓመታት በኋላ ኮን
ትራታቸውን እየጨረሱ የሚመለሱ ነበሩ ። በኬንያ ግን ነፃነቷን ስት
ቀዳጅ 43,000 ነጮች ነበሩ ። ከነዚህም 5,000 የሚሆኑት በእርሻ
ሥራ በሰሜን ኬንያ ደጋዎች የተሰማሩ ናቸው ። የኡጋንዳ የኢኮኖሚ
እንቅፋት ከዚህ ይጀምራል ። ምንም እንኳን የአውሮፓውያን በዚያ
መኖር የአፍሪካን እርምጃ የሚያንቀት ቢሆንም ለጠንካራ ሥልጣን ፣
ለሕግና ሥርዓት ፣ እንዲሁም ለፖለቲካ መረጋጋት አስተዋፅኦ ነበረው።

ውሎ አድሮ አቦቴ ሥልጣን ማካፈሉን ጠሉ ። ፍጹም የበላይ
ነትን መረጡ ። ለባጋንዳ የሰጡትን የራስ ገዝ የውስጥ አስተዳደር
ሻሩ ። ግጭትና የመገንጠል ዓላማ ተቀሰቀሰ ። በ1966 አቦቴ የጦሩ አዛዥ
የነበሩትን ኢዲ አሚንን ጡሩና አነስተኛ ኃይል በመጠቀም የባጋን
ዳዎችን ትግል እንዲጨፈልቁ አዘዙ ። አሚን ግን የባጋንዳዎችን መሪ
ቤተመንግሥት በታንክ በመናድ አጠቁ ። የባጋንዳው መሪ በአጥር
ዘለው በማምለጥ ወደ ለንደን ሄዱ ። ከአሥራ ስድስተኛው ምዕት



ዓመት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የባጋንዳዎች ንጉሣዊ አመ
ራር (ካባካ) ለአንዴና ለሁሌም ተወገደ ። አቦቴ ፕሬዚዳንት ሆኑ ፤
አሚንም ከአሁን ወዲያ የሚናቁ አልሆኑም ።

የጎሳ ግጭት ፣ የአቦቴ አቅጣጫውን የሳተ አመራር ፣ የማዕድናት
አለመኖር ቢያኮስሳትም ኡጋንዳ ሌሎች የምትኮራባቸው ተቋሞች
ነበሯት ። ማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ የሚደነቅና "የአፍሪካ ሐርቫርድ" እየተ
ባለ የሚጠቀስ ነበር ። በግብርና ላይ የተመሠረተው የሀገሪቱ ኢኮ
ኖሚ በሰባ ሺህ እስያውያን ገበሬዎች እየታገዘ ጤናማ ዕድገት ያሳይ
ነበር ። የቱሪስት ኢንዱስትሪው እየተስፋፋ ነበር ። የጤና አገልግሎቱ
በሶስተኛው ዓለም አሉ ከሚባሉት አንዱ ነበር ። አርባ ስምንት ሆስ
ፒታሎች ፣ በመቶ የሚቆጠሩ ጤና ጣቢያዎችና ዘመናዊ የሆኑ የሥነ
አእምሮ ሕክምና መስጫዎች ነበሩ ። አለምአቀፍ ታዋቂነት የነበረው
የትሮፒካል መድኃኒት ኢንስቲትዩትና በጥቁር አፍሪካ አንደኛ ደረጃ
የሚሰጠው ሙላጎ ሆስፒታል በካምፓላ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጡ
ነበር ። ምቹ ሆቴሎች ፣ የአደን ሥፍራዎች ፣ መዝናኛና አንድ ሺህ
ማይልስ አስፋልት መንገድ ፣ የባቡር መስመሮች ወደተለያዩ የሀገ
ሪቱ ማዕዘናት የተዘረጉ ከመሆኑ ሌላ እስከ ኬንያ የወደብ ከተማ
ሞምባሳ (ስድስት መቶ ማይልስ) የተገናኘ ነበር ። የተሻለ የሰለጠነው
የባጋንዳ ሕዝብም እድገቷን ለማፋጠን ሊያግዝ የሚችል ነበር ።

ለኡጋንዳ ጥፋት በኃላፊነት የሚጠየቁት ኢዲ አሚን በ1925
ከድሃ ገበሬ ቤተሰብ ተወለዱ ። ኢዲ አሚን የእስልምና ሃይማኖት
ተከታይና ኋላቀር የሆነው ካክዋ የተሰኘ ጦረኛ ጎሳ ተወላጅ ናቸው።
አሚን እንደተወለዱ ወላጆቻቸው ስለተፋቱ ከእናታቸው ጋር እንዲያ
ድጉ ሆነ ። ከዚህ የሕፃንነት እድሜያቸው ብዙውን ጊዜ ያሳለፉት እና
ታቸው ያገለግሉበት በነበረው የወታደር ካምፕ ነው ።

በ1946 አሚን በወጥቤት ረዳትነት በእንግሊዞች ጦር ካምፕ
ተቀጠሩ ። እንግሊዞች የእሳቸውን ጎሳ እንደማይወዱ በመገንዘብ
አሚን ያስመዘገቡት የአኮሊ ጎሣ ተወላጅ ነኝ በሚል ነው ። አሚን
በደረታቸው ላይ ስላሉት ሜዳሊያዎች ጉራ ለመንፋት እንደሚቀባ

ጥሩት በሕንድና በበርማ አልተዋጉም ። ይሁን እንጂ በማንኛውም መለኪያ ታዛዥና ደፋር ፣ ጠንካራ ወታደር ነበሩ ። በ1950 በኬንያ የማአ ፣ ማአ ንቅናቄን ለማዳከም ጥሩ ተዋግተዋል ። የመቶ አልቅና ያገኙትም ያን ጊዜ ነበር ። አንድ እንግሊዛዊ የጦር አዛዥ ሲገልጡ "አሚን አስተሳሰባቸው ደካማ ቢሆንም ጥሩ ወታደር ናቸው" ብለዋል።

በ1962 ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ አሚን በኋላ የታወቁበትን ጨካኝ ነታቸውን የሚፈነጥቅ ተግባር አከናወኑ ። የአንድ ባታሊዮን አዛዥ በመሆን በኬንያ ቱርካና ጐሣና በኡጋንዳ ካራሞጆንግ ጐሣ መካከል የተነሳውን ግጭት እንዲያስቆሙ ታዘዙ ። ተልእኮአቸውን በቅፅበት ፈጸሙ ፤ ነገር ግን ከወር በኋላ የአሚን ጦር በአለፈበት አካባቢ የታየው የሚዘገንን ነበር ። በደንብ ያልተቀበሩ ብዙ አስከሬኖች ተገኙ ። ብዙ ነዋሪዎች ተደብድበው ሞተዋል ፤ ከነሕይወታቸው የተቀበሩም እንደነበሩ ተረጋገጠ ። የኬንያ ጠረፍ አውራጃ የቱርካና ምክትል ገዢ ኢዲ አሚን የሚባል ወታደር አንድ መንደር ሕዝብ ስለጨፈጨፈ ለፍርድ ይቅረብ በማለት ያስተላለፈው ሪፖርትም ነበረ ። ነገር ግን በኦቦቴ ጥያቄ ክሱ ቀረላቸው ።

ኦቦቴ ሶሻሊዝምን አፍቃሪ ሰው ነበሩ ። እንዲያውም በአሜሪካ ስለሕግ ለመማር ዕድል ተሰጥቷቸው ቅኝ ገዥዎች ለኡጋንዳ የአሜሪካን ሕግ መማር አይጠቅማትም ብለው መውጫ ቪዛ ስለከለከሏቸው ቀርተዋል ።

በጥር 1971 ኦቦቴ በጋራ ንብረት ሀገሮች ስብሰባ ለመገኘት ወደ ሲንጋፖር ሄዱ ። ከመነሳታቸው በፊት አንድ ስህተት ፈጸሙ ። ኢዲ አሚንና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትን ፌሊክስ ኦናማ ስለባከነ የአራት ሚሊዮን ዶላር የጦሩ ገንዘብና መሣሪያ በፅሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አዝዘው ተጓዙ ። ይህ ጥያቄ የማይቀረውን መፈንቅለ መንግሥት አፋጠነውና ጥር 25 ቀን አሚንና ጓደኞቻቸው ሥልጣን ነጠቁ ። በውጤቱም ለአሥራ ሁለት ዓመት ልጆች ቦምብ ሰጥቶ የሀገር መሪ ሆናችኋል እንደማለት ነበር ።

አሚን ሥልጣን እንደያዙ ኡጋንዳን ከጃፓን የበለጠች ሀብታም እንደሚያደርጉ ጉራ ነፉ ። በ1974 ከአምስቱ ሚስቶቻቸው ሶስቱን



ፈቱ ። የአንደኛዋ የተቆራረጠ አካል አንድ መኪና ላይ ታየ ። መልኩ መልካም የነበረች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን ኤልሳቤጥ ባጋያ ከሥልጣን በማባረር በፓሪስ አውሮፕላን ጣቢያ ሽንት ቤት ውስጥ ወሲብ ስለፈጸመች መሆኑን ገለጡ ።

"የእኔ ችግር" ይላሉ አሚን ፣ "ከጊዜዬ በሃምሳና በመቶ ዓመት ቀድሜ የምገኝ የላቀ አስተሳሰብ ያለኝ መሆኔ ነው ። ስለዚህም ለለውጥ ፈጣን ስለሆንሁ ብዙ ሚኒስትሮች ከለውጡ ባቡር እየተንጠባጠቡ በየመንገዱ መውደቃቸው ግድ ሆነ ።"

በአንድ ወቅት ደግሞ ማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ሄደው ለተማሪዎች ባደረጉት ንግግር፣ "ጥቂት ወቀሳዎች አሉኝ ። ሕዝብን ስለመሠረተ ጤና የማስተማር ኃላፊነት ስላለባችሁ ንፅሕናችሁን መጠበቅ ይገባችኋል። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከፍተኛ የአባለዘር በሽታ እንዳለ ደርሼበታለሁ ። ስትታመሙ ሐኪም ቤት ሄዳችሁ ራሳችሁን ማዳን ካልቻላችሁ ሌላ ውንም ትበክላላችሁ ። እወዳችኋለሁ ። ስለዚህም በጨብጥ በሽታ እንድ ትጠቁ አልፈልግም" በማለት ነቀፉ ።

ሎርድ ስኖውደን ከልዕልት ማርጋሬት ጋር መፋታታቸውን እን ደሰሙ አሚን ለሰውየው በላኩት ደብዳቤ ፣ "በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶችን ከማግባት እንድንጠነቀቅ ለእኛ ለወንዶች የእርስዎ ልምድ ትምህርት ይሰጠናል" የሚል ይገኝበታል ። ዓለም ተሳለቀ ፣ ሌሎች አፍ ሪካውያን አደነቁ ፣ ኡጋንዳውያን ግን በየቀኑ በመቶና በመቶ ሃምሳ እየሞቱ ነበር ።

ከሚኒስትርነት ወደ ገበሬነት የመባረር ዕድል በሁሉም ባለሥ ልጣን ላይ የሚያንዣብብ ነበር ። ምሁር መሆን ፣ ወይም ዝነኛ መሆን ለሞት ለመታጨት በቂ ምልክት ነበር ። የማህበር ስብሰባ ፣ የቤተ ዘመድ ስብሰባ ፣ የመሰሉትን ከማካሄድ መቆጠብ የሚሻል ነበር ። የአሚን ሰላዮች በየሰፈሩ ፣ በየመሥሪያ ቤቱ ፣ በየሱቁ ፣ በየሆቴሉ ፣ በየትምህርት ቤቱና በየታክሲው ውስጥ ስለተመደቡ በሕይወት ለመቆየት አፍን መዝጋት ግድ ነበር ።

የሁለት ልጆች እናት የሆነችው ጁዲት ሀሙሉንዶ አንድ ቀን እንዲህ አለችኝ ። "አንዳንድ ጊዜ ባለቤቴና እኔ አልጋችን ውስጥ ሆነን

በኡጋንዳ ስለሚካሄደው ጭፍጨፋ ቀስ ብለን እንወያያለን ። በልጆ
ቻችን ፊት ግን ስሜታችንንም ሆነ የአሚንን ስም ጠርተን እናው
ቅም ። ትምህርት ቤት ውስጥ ሳት ብሏቸው ቢናገሩ በራችንን መጥቶ
የሚያንኳኳ ይናገራል ። ያ ፣ ማንኳኳት ማለት የሞት ጥሪ ማለት ነው።"

አንድ ሰላይ እንደሚከተለው ያስፈረውን የምሥጢር ሪፖርት
አሚን ቤት ባገኘሁት አንድ ዶኩሜንት ውስጥ ተመለከትሁ ።
"ይህ ሰው በቅርብ የማውቀው ስለሆነ ራሴ እርምጃ ልወስድበት አል
ችልም ፤ ርምጃ መወሰድ ካለበት እኔ መጠቆሜ ሳይታወቅ መሆን ይገ
ባዋል" ይላል ።

አንድ የሕግ ጠበቃ ሲያወጋኝ ወደ ሥራ የሚሄደው በካናቴራ
እንደነበረና ይህን የሚያደርገውም ሀብታም መስሎ በመታየት የአሚ
ንን ተከታዮች ዓይን ላለመሳብ እንደሆነ ገለጠልኝ ። ሌላም ነጋዴ በተ
መሳሳይ ምክንያት ማርቸዲስ መኪናውን እርግፍ አድርጎ ትቶ በቢ
ስክሊት ለሥራ ይዘዋወር እንደነበረ አጫወተኝ ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪ
ዎች ሥራ ለመቀጠር ቃለመጠይቅ ሲቀርብላቸው ከሁለተኛ ደረጃ
ትምህርት ቤት ወድቀው እንደወጡ አስመስለው ይናገሩ ነበር ። ምክ
ንያቱም አሚን የተማሩ ሰዎችን በሙሉ ለማጥፋት ፍላጎት እንዳላ
ቸው ስለሚታወቅ ነው ።

የዓለም ጋዜጦች "ቢግ ዳዲ" እያሉ የሚጠሯቸው አሚን ፣ የሚ
ቃወሟቸውን ሁሉ ብቻ ሳይሆን ፣ ገና ለገና ይቃወሙኝ ይሆናል ወይም
ርምጃዬን አይደግፉም ብለው የሚገምቷቸውን ሰዎች ሁሉ እንደጉ
ንዳን ከመጨፍለቅ አይመለሱም ነበር ። ስለሀገር ፍቅር ፣ ስለብሔ
ራዊ ልማት ፣ ስለሰብአዊ ክብርና መብት ጥሩ ጥሩውን ሁሉ ይናገራሉ፤
በአፋቸው ለማስመሰል እንጅ ተግባራቸው ግን በተፃራሪው ነው ።
ሰባ ሺህ እሲያውያንን ከኡጋንዳ በማባረር ከቤት ከንብረታቸው አፈ
ናቀሏቸው ። አውሮፓውያንን በተለይ እንግሊዞችን በዙፋን አስቀ
ምጠው ተሸከመዋቸው እንዲዞሩ በማድረግ እንደ አሻንጉሊት ተጫ
ወቱባቸው ። ታዲያ ይህን አድራጎታቸውን በአገራቸው ውስጥም ሆነ
ከአፍሪካ መሪዎች ውስጥ የሚያደንቁ ነበሩ ።



ኡጋንዳ ግን ብዙ መስዋዕትነት ከፈለች ። አሚን ራሳቸውን የፍ
ልስፍና ዶክተር ብለው ሰየሙ ። የማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ነኝ
ሲሉ ራሳቸውን ሾሙ ። ዩኒቨርሲቲው ግን በከፊል ብቻ ከማይምነት
የተላቀቁ አላዋቂዎች መናኸሪያ ሆነ ። ከ1976 እስከ 1979 የዩኒቨር
ሲቲው ቤተመፃሕፍት አንድም ተጨማሪ መጽሐፍ አልገዛም (አላስ
መጣም) ። በሀገሪቱ የዋጋ ንረት አንድ ሺህ በመቶ አሻቀበ ። የደመ
ወዝ ጭማሪ ግን በአሚን ዘመን ያደገው ሃምሳ አራት በመቶ ብቻ
ነበር ። አሚን ከሥልጣን ሲባረሩ ዝቅተኛው ደመወዝ በወር ሰላሳ
አራት ዶላር ብቻ ነበረ ።

መንገዶች ፈራረሱ ፣ ፋብሪካዎች ተዘጉ ፣ የዱር አራዊት በወታ
ደሮች እየተገደሉ ተመናመኑ ። አውሬዎችን የሚገድሏቸው ለሥጋ
ቸውና ለዝሆን ጥርስ ሽያጭ ሲሉ ነው ። ዝነኛው የካምፓላ ሙላጎ
ሆስፒታል ተዳከሞ ሽንት ቤቶቹ ተበላሹ ፣ የውሃ ቧንቧዎች ተሰባበሩ፣
የሕሙማን መተኛዎች በበሽተኞች ብዛት ከልክ በላይ ተጨናንቀው
የአይጦች ፣ የበረሮዎች ፣ የቅማል ፣ የቁንጫና የትኋን መፈንጫ ሆኑ ።
ዕውቅ ሐኪሞች ኮበለሉ ፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን ተሰ
ደዱ ፣ የገጠር ክሊኒኮች ተዘጉ ፣ የቱሪስት እንቅስቃሴ ነጠፈ ።

የካምፓላ ከተማ ከአውሮፕላን ላይ ሲመለከቱት የቀድሞ ሕንፃ
ዎችና በመንገዶች ግራና ቀኝ የተተከሉት ዛፎች ውበት ቢሰጡትም
የውስጥ አገልግሎቱ ግን በብዙ ተጓድሏል ። የብዙ ሕንፃዎች አሳን
ሰሮች (ሊፍት) አይሰሩም ፣ የመብራት አገልግሎት ስለተቋረጠ
ነዋሪዎች ደረጃዎችን የሚወጡት በክብሪት ብርሃን እየተጠቀሙ
ነው ። የውሃ ቧንቧዎች ስለተበላሹ ውሃ ከማጠራቀሚያው ወደየክፍሉ
በባልዲ ማጓጓዝ ነበረባቸው ። ትልልቅ የነበሩ ሆቴሎች ከቡናና ዳቦ
በስተቀር ለእንግዶች የሚያቀርቡት አልነበራቸውም ። ትያትር ቤቶች
ሥራ አቆሙ ፣ በነፃነት አደባባይ የቆመው ትልቅ ሰዓት መሥራት
ካቆመ ዓመታት ተቆጠሩ ፣ ሁሉም ነገር ቀጥ አለ ። ቪክቶርያ ሐይቅ
አጠገብ ያለው ቤተ መንግሥት ዳዋ ዋጠው ፣ ሶፋዎቹ በሲጋራ ተነ
ዳድለዋል ፣ መጋረጃዎቹ ተወስደዋል ፣ የቢራ ጠርሙሶች በበረንዳዎቹ
ተዝረከርከዋል ፣ የማብሰያ ቤቱ ወለል በዘይትና ቅባት ተጨማልቋል፣

የቤተ መንግሥቱ ሳሎን ኮርኒስ በአሚን የደስታ ተኩስ በሽጉጥ ጥይት ተበሳስቷል ።

በኡጋንዳ ሁኔታው እየተባባሰ በሄደ ቁጥር ሕዝቡ ራሱን ከችግሩ ጋር እያስማማ መሄድን ብቻ መረጠ ። እህል በከተማ ቢጠፋ ጥራጥሬ ተመግበው ይሰነብታሉ ፣ ስልክ ባይሰራ ጉዳያቸውን በእግር ተዘዋውረው ያከናውናሉ ። ዘመዶቻቸው በፖለቲካ ምክንያት ቢገደሉ ተቃውሞ አቅርቦ አብሮ ከመሞት ዝምታን መረጡ ። ወደ ሥራ የሚሄዱበት ታክሲና አውቶቡስ ቢጠፋ በእግር ይቀጥላሉ ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ሳያማርሩና ቅሬታቸውን ሳይገልጡ ነው ። ይብስ እታም ጣ እያሉ ሕይወትን ለማቆየት ሁሉን ችሎ ዝም ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም ። የሰለጠነው ዓለም ይህንን ደካማነት ወይም ለዘብተኝነት ሊለው ይችላል ። ለአፍሪካውያኑ ግን በሕይወት ለመቆየት የግድ መከተል ያለባቸው ፍጹም ታዛዥነት ነው።

የሚያሳዝነው አፍሪካ አሚንን ልታገልለው ብትችል ኖሮ ይህን ያህል ባልቆየም ነበር ። ምሥራቅና ምዕራቡ ዓለምም የግል ፍላጎታቸውን ብቻ ባያሰላስሉ ኖሮና ለኡጋንዳ ሕዝብ ቢያስቡ ኖሮ ያን ያህል ባልሰነበትም ነበር ። ነገር ግን በተቃራኒው ሊቢያ የአሚንንጦር አሰለጠነች ፤ ወታደራዊ አማካሪዎችም ላከች ፣ ሲቢል የቴክኒክ ባለሙያዎችም አቀረበች ። ሳውዲ አረቢያ አሚን ሊባረሩ አካባቢ በእስላም ወንድማማችነት ስም ሁለት ሚሊዮን ዶላር ለገሰች ። የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት በእሥራኤል ላይ ፀረ—አይሁድ አቋም ለሚያሳዩት አሚን የክብር ዘቦቹን መደበላቸው ። ግብፅ ፣ ፓኪስታንና ባንግላዴሽ ለማካራሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ላኩ ፣ የሕክምና ዶክተሮችና ሌሎች ሙያተኞችም መደቡላቸው ። ሶቪዬት ኅብረት ዘመናዊ ጦር መሣሪያዎች አቀረበች ፣ ምሥራቅ ጀርመን ደግሞ የአሚንን የስለላ ድርጅት አሰለጠነች ።

አሜሪካም አሚን ሊወድቁ እስከተቃረቡ ድረስ የኡጋንዳ ቡና ዋነኛዋ ሸማች ነበረች ። የምዕራብ ኩባንያዎች ነዳጅ በማቅረብ ተባበሩ ። እንግሊዝ ዋናዋ ሸቀጥ አቅራቢ በመሆን ከሬዲዮ እስከ ወታደር ልብስ ስትቸረችርላቸው ኖረች ። እንዲያውም አሚን የአንግሊካን ቤተ



ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስንና ሁለት ነባር ሚኒስትሮችን እስከገደሉና በመኪና አደጋ እንደሞቱ አስመስለው እስካቀረቡ ድረስ ምዕራቡ በሌላው ጭፍጨፋቸው ጠንካራ ተቃውሞ ሳያሰማ ቆይቷል ።

አሚን በሀገር ውስጥም ተቃውሞ እየገጠማቸው መጣ ። በተለይ ሊቀጳጳሱን ከገደሉ በኋላ ጥላቻ እየለባቸው ። የጦር ሠራዊታቸው ተቅበጠበጠ ፤ የጎሳ ጦርነት ተቀጣጠለ ፣ ስለዚህም አሚን ጦራቸውን ሥራ መስጠት ፈለጉ ። በጥቅምት 1978 የኡጋንዳ ጦር ታንዛንያን ወረረ። 710 እስኩየር ማይልስ የሚሆነውን የታንዛኒያ ሰሜናዊ ምዕራብ ግዛት ያለተቀናቃኝ ተቆጣጠረ ። አሚንም ወረራውን "በሃያ አምስት ደቂቃ የተከናወነና የዓለምን ክብረወሰን የሰበረ ፈጣን" በማለት ደነፉ ። ጁሊየስ ኒሬሬ አሚንን ጭንቅላታቸው በቂጥኝ በሽታ ምክንያት የተበላሸ "እባብ" በማለት ነቀፉ ። ወዲያውም ጀኔራሎቻቸውን ጠርተው ወረራውን እንዲያከሽፉ አዘዙ ።

በመጀመሪያው ቀን ታንዛንያውያን በስህተት የራሳቸውን ሶስት የጦር አውሮፕላኖች ጣሉ ። የመሣሪያ ክምችቱን ቦታ ማናቸውም ለማወቅ ስላልቻሉ ከሳምንት በኋላ ጦርነቱ ቆመ ። ስለዚህም የመጀመሪያው ውጤት ጦርነት በዚህ መልክ መደረግ እንደሌለበት ጥናት የተካሄደበት ነበር ሊባል ይቻላል ። አንድ የታንዛንያ ብርጌድ ቆይ የሚለው ትእዛዝ ስላልደረሰው ጉዞ በመቀጠል ሰሜን ኡጋንዳ ለመግባት ሲጋልብ ርዋንዳ ጫካ ውስጥ ገብቶ መመለሻው ጠፋው ። ወደ ኡጋንዳ ለመሄድም ሆነ ወደ ታንዛንያ ለመመለስ መንገዱ ጠፍቶበት ለቀናት ጫካ ለጫካ ሲባዝን ሰነበተ ። ብዙዎቹ የታንዛንያ የወታደር ተሽከርካሪዎች ተሰናከሉ ። ስለዚህም ጀኔራሎች አውቶብስና ካሚዮን ማስመጣት ነበረባቸው ። የተጠየቁት መኪናዎች መጡና ቤንዚን አልቆባቸው ቆሙ ። ወታደሮቹም በእግር ለመቀጠል ተገደዱ።

በመጨረሻ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሁለቱ ተቀናቃኞች ሲጋጠሙ የጦሩ የውጊያ ሞራል ወድቆ ስለነበር ከሩቅ እየተወራወሩ ካምፕ ሰርተው ቁጭ አሉ ። ሆኖም ኔሬሬ አሚንን ለማሸነፍ ቆርጠው ስለነበር የኡጋንዳ ልዩ ልዩ ተቃዋሚ ኃይሎችን ሰብስበው ግንባር አስፈጠሩና ውጊያው እንዲቀጥል አደረጉ ። ሃምሳ ሺህ የሚሆን ሚሊሽያ

ከከተማም ከገጠርም (ወመኔውንና ከብት ጠባቂውን) በመሰብሰብ አቋቋመ ። ሚሊሽያው በደንብ ያልሰለጠነና አለቃና ምንዝር በውል ያልተለየበት ስለነበር ዲሲፕሊን ያለው ጦር ሳይሆን የዘራፊ ቡድን ይመስል ነበር ። እንዲያም ሆኖ ከጥቂት የኡጋንዳ ደፈጣ ተዋጊዎች ጋር በማበር ውጊያ ጀመረ ። የኡጋንዳ ጦር የራሱን መንግሥት በመጥላት ይመስላል ግብግቡን ትርጉም ስላልሰጠው ተኩስ እንደተጀመረ ጡመንጃውን እየጣለ ይሸሽ ጀመር ። ሙአመር ጋዳፊ ወደ መጨረሻው አሚንን ለማዳን የላኩዋቸው ወታደሮቻቸው ካምፓላን ለመከላከል ሥፍራ ከያዙ በኋላ ጥለው ሸሹ ። አሚን በአውሮፕላን ወደ ትሪፖሊ (ሊቢያ) ፈረጠጡ ። ካምፓላ ያለጦርነት ተያዘች ። ዮሴፍ ሉሌ ቤፓርላማው ሕንፃ ዙሪያ ወደተሰበሰበው ሕዝብ ብቅ በማለት ሳይጀመር ስለተቀጨው መልካም አጀማመር ተናገሩ ።

ኡጋንዳ እንደ ሀገር የመቆሟን ጉዳይ ለመናገር የሚያዳግት ሆነ። በዘርና ጎሳ ተከፋፈለች ። ከተሞችዋ መቅኖ አጡ ፥ ለእጅ ሰዐት ብለው ነፍስ በሚቀሙ ወንበዴዎች ሁከት ተዋጡ ። የተቋቋመው መንግሥት ባለሥልጣኖች እዚህ ግቡ የማይባሉ ፥ የተናቁና ችሎታና ምግባር የጎደላቸው ፥ ራሳቸውን ብቻ ለማገልገል የቆሙ ሆኑ ። አሚን ከሥልጣን እንደተወገዱ የአገራቸውን እድገት ለማገዝ በመሻት ከየሀገሩ የተመለሱ ምሁራን እንደገና እየጣሉ ሄዱ ። ኢኮኖሚው ፥ የመንግሥት መዋቅር ፥ የእርቅ መንፈስ ሁሉ ወድሟል ። እንደገና ሊገነባ የሚችል የተረፈ ቅሪት የለም ። ኡጋንዳውያን በብሔራዊ ደረጃ ራሳቸውን ገደሉ። በ1983 የመንግሥት ወታደሮች እንደገና ተቃዋሚ ሆነው ከተነሱት የደፈጣ ቡድኖች ጋር በከፈቱት ጦርነት መንደሮች ተደመሰሱ ፥ ቤተ ክርስቲያኖች ፈራረሱ ፥ ቤቶች ተዘረፉ ፥ የኢዲ አሚንን ዘመን ዳግም የሚያስታውስ አሰቃቂ ሁኔታ ተፈጥሮ በቀን በመቶ የሚቆጠር ሕይወት ይቀሰፍ ጀመር ።

አንድ ቀን አሚን ጅዳ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እያሉ ስልክ ደወልሁላቸውና ኡጋንዳ ከእሳቸው መባረር በኋላ ስለገጠማት ሁኔታ ጠየቅኋቸው ። እንዲህ አሉኝ ። "አንድ ነገር ልንገርህ ፥ እዚህ ከመጣሁ በኋላ ብዙ ነገር አጠናሁ ። ኡጋንዳ ዲሞክራሲ ያስፈልጋ



ታል ። ግን ዲሞክራሲን በቅጽበት በኡጋንዳ ማስፈን አይቻልም ። ሁለትና ሶስት ዓመት ይወስዳል ። ፀጥታው አሁን ጥሩ አይደለም ። ብዙ ችግሮችም አሉ ። ግን እንደ እኔ ዓይነት ወታደራዊ ዕውቀት ያለው ጠንካራ ሰው ሕዝቡን ዲሲፕሊን ማስተማርና ለዲሞክራሲ ማዘጋጀት ይችል ነበር ።

"በኡጋንዳ ለተፈጠረው በኃላፊነት የምጠየቀው እኔ እንዳልሆንሁ አሁን ካለው ሁኔታ ሳትገነዘብ አልቀረህም ። አሁን አቦቴ ሥልጣን ይዟል ። ታዲያ ያን ሁሉ ሰው የሚገድል እሱ ነው ሊባል ይቻላልን ? በፍፁም ! እኔም የዚያው ዓይነት ችግር ውስጥ ነበር የወደቅሁት ።

"የኡጋንዳ ችግሮች ፥ የዘር ፥ የኤኮኖሚ ፥ የራስን መውደድ ስግብግብነት ናቸው ። አቦቴ ከእኔና ከሌሎችም ተቃዋሚዎች ጋር ቁጭ ብሎ የኡጋንዳን ችግሮች መወያየት አንችልነበር ። ግን ይህ አቦቴ የሚባል ሰው በጣም ስለሚፈራኝ በስልክ እንኳን ድምፄን ቢሰማ ይርበተበታል" በማለት ዘረዘሩልኝ ።

የኡጋንዳ ሁኔታ ብዙ አስጨናቂ ጥያቄዎችን ያስነሳል ። የኡጋንዳ ሁኔታ የራስዋ ብቻ ነው ወይስ መላው አፍሪካ ይህን ራስን በራስ የማጥፋት ጐዳና ለመከተል የአርባ ቀን እድሉ ሆኗል ? ኡጋንዳ እንደገና ታገግም ይሆን ? የምዕራቡ ዓለም ሚና ምን ሊሆን ይገባል ? በአንድ ወቅት ወደ ብልፅግና ያመራች አገር ተመልሳ ወደ ድህነትና ኋላቀርነት አዘቅት ስትወድቅ በማየት አፍሪካ ምን ትምህርት ለመቅሰም ችላ ይሆን ?

አንድ በዘረኝነት አስተሳሰብ የተጠመደ ፥ በተሳሳተ አቅጣጫ የተመራ የኋላቀር ሕዝብ ሀገር መጨረሻው እንዴት አስፈሪ ሊሆን እንደሚችል በኡጋንዳ የደረሰው በግልፅ ያሳያል ። ሆኖም ኡጋንዳ ለአፍሪካ የምታስተምረው አየርላንድ ለአውሮፓ ሊያስረዳ ከሚችለው የበለጠ ነው ማለት ተገቢ አይሆንም ። ድክመቱ ከሰው ልጅ ድክመት የሚመነጭ ነው ። ሰው በሰው ላይ ለሚፈጽመው ፍትሕ አልባ ድርጊት ማንም አህጉር ልዩ አመንጪ አይደለም ። አፍሪካ አሚንን አፈራች ፥ አውሮፓ ደግሞ ሂትለርን ሰጠችን ። ለሃያ ዓመ

ታት ብቻ አገር ሆና የቆመችው ኡጋንዳ መቃብሯን ቆፈረች ፣ ከሺህ ዓመት በላይ አለኝ የምትለው ካምቦዲያ በባሰ ሁኔታ ራሷን እንጦሮጦስ አወረደች ። የኡጋንዳ ውድቀት ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጅ ትምህርት የሚሆን ነው ።

ለእርሻ ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ስላላት ኡጋንዳ በውጭ ርዳታ ሊያንሰራራ የሚችል የኤኮኖሚ መሠረት አላት ። ይህ ብቻ እንኳን በአንድና ሁለት ትውልድ ኡጋንዳ እንደምንም ትርጉም ያለው ሀገር ሆና ልትቆም እንደምትችል ተስፋ ያሳድራል ። ይህ ተሃድሶ ሊመጣ የሚችለው ግን አስከፊ መሪዎች ተወግደው ሕዝቡ የወደፊት ዕድሉ ወሳኝ መሆን ሲችል ነው ።

በዚህ አቅጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ የሰላም መከበር ነው ። ትክክለኛና ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ማካሄድ መቻል ነው ። ሕዝቡ ትጥቅ ፈትቶ የኀሳዎችን ሚዛን የጠበቀ ጦር ማደራጀት ሲቻል ነው ። በእኩልነትና በነፃነት ሁሉም አሥራ ሶስት ጎሣዎች በሀገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሕይወት ተገቢ ቦታ እስካላገኙ ድረስ ኡጋንዳ የምትባል የእውነት ሀገር አትኖርም ። ኡጋንዳ ይህ ዕድል በአንድ ወቅት አጋጣሚት ባትጠቀምበትም ሁለተኛው አጋጣሚ ብቅ ሊል ስለሚችል ምርጫው የራስዋ ነው ።

የኡጋንዳ መሪዎች በሥልጣን መባለግና እምባገነን መሆን ሲጀምሩ የምዕራብ ኃያላን ቃል የገቡትን የገንዘብ ርዳታ አቋረጡ ። ይህም ትክክለኛ እሠራር ነበር ። ከእስቸኳይ ጊዜ ምግብና መድሃኒት ሌላ በኡጋንዳ ገንዘብ ማፍሰስ ማበላሸት ነበር ። ያ ፣ ጊዜ በኡጋንዳ ግድብ የሚሰራበትና መንገድ የሚጠገንበት አልነበረም ። የኡጋንዳ ችግር በገንዘብ ይፈታል ብሎ ማሰብ መጠጥ የለመደ ጠጭ ከዚያ መጥፎ ልማዱ እንዲወገድ ጠርሙስ ውስኪ እንደመለገስ ያህል የቂል ሥራ ይሆን ነበር ። ኡጋንዳ ተቆርቋሪ ያጣች ሀገር ስለሆነች ከራሳቸው ከኡጋንዳውያን በስተቀር መልሶ ሊያቋቁማት የሚችል ማንም የለም ። በጠመንጃ ማምለክና ጭካኔ ፣ ስግብግብነትና ለሰው ሕይወት ክብር አለመስጠት ማክተም አለበት ።



<u>ምዕራፍ አምስት</u>

## አንድነትን ፍለጋ

"ስብሰባዎች በከንቱ ጊዜ ማባከኛዎች ናቸው ። በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባዎች ሁሉም እየተነሳ መናገር ብቻ ነው ። እዚያ ተቀምጠው የሁሉንም ንግግር መስማት በንዴት የሚያስጮኸኝ ይመስለኛል ።"

ኤል ሀጂ ኦማር ቦንጎ
የጋቦን ፕሬዚዳንት

በየዓመቱ ክረምት መግቢያ ላይ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሥጋት የተደቀነባቸውን የፖለቲካ ሥራዎች የያዙት ሃምሳ ሰዎች በአንድ የአፍሪካ ከተማ ይሰበሰቡና የአህጉሪቱን ጉዳዮች ይወያያሉ ። ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ የመሪዎች ስብሰባ ለመሪዎቹ እፎይታ የሚሰጥ መድረክ ነው ። ብዙውን ጊዜ ከአገራቸው ግዙፍ ችግሮች ሸሽቶ ለመሰንበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል ። የአፍሪካን ልማት ከሚያንቀው አያሌ ችግሮች ማለትም ከጦርነት ፣ ከድርቅ ፣ ከረሀብ ፣ ከኃያላን ጣልቃገብነት ፣ ከድንበር ግጭቶች ፣ ከኢኮኖሚ ውድቀቶች ፣ ብቃት ከጎደለው አመራር ፣ ከርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ ከሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ፣ ከፖለቲካ አለመረጋጋት ፣ ከወሊድ ቁጥር መናር ሸሽተው የሚሰነባበቱበት ሰሞን ነው ። ስብሰባው የሚጀምረው በወንድማዊ መተቃቀፎችና ስለአንድነት በመማፀን ነው ። ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ፕሬዚዳንቶቹና ጄኔራሎች በመጣደፍ ወደ የሀገሮቻቸው ይመለሳሉ ። በስብሰባው ያከናወኑት ነገር ቢኖር